# የመዝሙር ርእስ


1 አፌን ለምስጋና
2. የብርሃን ጎርፍ ናት
3. ከጌታዬ ፍቅር
4. ምን ሰማህ ዮሐንስ
5. አንደበትን ስጠኝ ጌታዬ
6. የጽድቅ በር ነሽ
7. አለቴ ነህ አንባዬ
8. ኑ በእግዚአብሔር
9. ሰላም ለኪ
10. ባክኛለሁና
11. አማኑኤል ተመስገን
12. አድርገህልኛልና
13. ቅያሜው ይቅርና
14. ሊረዳን መጣ
15. ቋንቋዬ ነሽ
16. ስለማይነገር ስጦታው
17. የአዋጅ ነጋሪት ቃል
18. ውዳሴ ማርያም
19. አምላከ ተክለሃይማኖት
20. እባክህ ወዴት ነህ
21. ግሩም ድንቅ ነህ
22. እኔስ በምግባሬ
23. የሐሰት ዳኝነት
24. ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ
25. እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ
26. በሀዘኔ
27. እግዚአብሔርን ጠራሁት
28. እርዳኝ ዝም አትበል
29. የስሙ ትርጓሜ
30. ድንግል እመቤቴ
31. አልተወኝም ጌታ
32. ኪዳነ ምህረት
33. ጽረ አርያም
34. የጥበብ ሰዎች መጡ
35. ሳር ቅጠሉ ሰርዶ
36. ተወለደ
37. ግነዩ ለእግዚአብሔር
38. እግዚአብሔርን ጠራሁት
39. ሃይልን በሚሰጠኝ
40. እናመስግነው
41. እንደ እግዚአብሔር ያለ
42 በሀዘኔ ደራሽ ነሽ
43. በበጎ ፍቃዱ
44. አንደበቴም ያውጣ

45. እልል በሉ
46. እግዚአብሔር መልካም ነው
47. እግዚአብሔርን አመስግኑ
48. ደስ ይበለን
49 የያሬድ ውብ ዜማ
50 የማያልፍ የለም
51 ለውዳሴሽ ልትጋ
52 የወደደኝ ጌታ
53 እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ
54 ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
55 ደጅ ጠናሁ
56 የይሁዳ ጉዞ
57 ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
58 መቼ ነው ጌታ
59 በመከራ ጽና
60 በደልህን አምነህ
61 የዶኪማስ ጓዳ
62 ወደ አንተ እሰግዳለሁ
63 ዓለምን ዞሬ አየሁት
64 ጎሰቆለ
65 ከወገኔ ጋራ
66 ከካራን ውጡ
67 ያልጠፋነው
68 እያለፈ ነው ዘመኔ
69 ሰላምሽ ዛሬ ነው
70 ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን
71 የጸጸት እሮሮ
72 እስመ ለዓለም
73 የት ይሆን መግቢያዬ
74 ወደ ምስራቅ እዩ
75 አትተወኝ አትጣለኝ
76 እመቤቴ የአምላክ እናት
77 ተክለሃይማኖት ፀሐይ
78 ያሬድ ካህኑ
79 እጹብ ድንቅ ነው
80 የስላሴን መንበር
81 እናመሰግንሃለን
82 ዝም አትበሉ
83 ጠላቴን ጌታዬ
84 በገና አንስተን
85 ለማርያም እንዘምራለን
86 ወይቤሎሙ ሐሩ

87 እርግብየ
88 ስምሽን ጠርቼ
89 አንቺን የያዘ ሰው
90 እዘምራለሁ
91 ሰረገላዎችህ
92 ዛሬም አለሽ
93 ያ ድሃ ተጣራ
94 ርሆቦት
95 ቸርነትህ ነው
96 ሞገድ ሲገፋኝ
97 ሐረገወይን
98 አስፈሪ ነበልባል
99 ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
100 ማርያም አርጋለች
101 ማን አለን
102 መላዕክቱ
103 ገብርኤል
104 ሌላ ምስጋና
105 አንተ ግን አንተ ነህ
106 ሊረዳን መጣ
107 ሃጢአቴ በዛ
108 ምስጉን ነው
109 ገና እንዘምራለን
110 አቤቱ እንዳንተ ማን ነው
111 ዘንዶውን አሸንፏል
112 አንቺ የወይን ሐረግ
113 ባለውለታዬ
114 ድንግል በድንግልና
115 ድንግል ፈጣሪዋን
116 በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና
117 እሰይ ተወለደ
118 ሆሳዕና በሉ
119 በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ
120 ምድረ ቀራኒዮ
121 ወንበዴ ነበርኩኝ
122 ተወልዳለችና
123 ስላሴን አመስግኑ
124 ምስጋናዬን
125 ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
126 አብ ወወልድ
127 እመብርሃን
128 ሞት ነው ርሃብ

129 ይሰመነናል
130 ባለጸጋ እመቤት
131 መንግስተ ስላሴ
132 እንድናለን
133 አ ስሉስ ቅዱስ
134 ገብረ ሕይወት
135 መጠጊያዬ
136 ያዕቆብ ከቤርሳቤት
137 ስላሴ ዘከሃ
138 አወድሰኝ ኤፍሬም
139 እነሆ አዲስ ሰማይ
140 ሰዓሊለነ ቅድስት
141 ፍቅሩን ለገለጸው
142 የሃይማኖት ፍሬ
143 አልፈርድም እኔ
144 እንደ ኤልሳቤጥ
145 እስከ መቼ ነው
146 ስራው ድንቅ ነው
147 በረከትህ ይደር
148 ከንቱ ነኝ
149 ደስ ይበለን
150 ገሊላ እትዊ
151 ተስፋችን ነህ አንተ
152 ምስጋና ነው ስራዬ
153 አበባየሆሽ
154 የዓለምን በደል
155 ወደ ማደሪያው
156 ሐመልማላዊት
157 አ ሚካኤል
158 መመኪያዬ ርስቴ
159 እሰይ እልል በሉ
160 የመስቀሉ ፍቅር
161 ትህትናሽ ግሩም ነው
162 ገድሉ ተዓምራቱ
163 ክብረ ቅዱሳን
164 እመቤቴ ማርያም
165 እቴ ሙሽራዬ
166 ካንተ የሆነው
167 አማላጅ ነው
168 እልፍ አዕላፋት
169 ድንግል መከራሽን
170 ኢትዮጵያ ሆይ
171 ቅዱስ ሚካኤል

172 እንበረታለን ገና
173 በዕምነታቸው
174 እጠበኝ ቆሸሻለሁ
175 ተመስገን እንበል
176 ብርሃኔና መድሃኒቴ ነው
177 በጌቴ ሰማኔ
178 አልፋና ኦሜጋ
179 ጌታዬ ሆነህ
180 በዕጸ መስቀል ላይ
181 የሕያዋን አምላክ
182 የፍቅር እናት
183 በማህጸን ቅኔ
184 ልቤ በእግዚአብሔር ጸና
185 ይበራል በክንፉ
186 ዘምር ዘምር አለኝ
187 አንድ አድርገን
188 በአምላካችን አንጻር
189 ፈተና ወጀብ ቢበዛ
190 ድንግል ትንሳኤሽን
191 የአብ ቃል አክብሮሽ
192 የእቲሳ አንበሳ
193 ገብርኤል ሃያል
194 ጽላት ዘሙሴ
195 ሰዎች ፈረዱብኝ
196 ኪዳነ ምህረት እናቴ
197 እንዲህ እናምናለን
198 ኢትዮጵያዊው ጻድቅ
199 ባርከን ባርከን
200 የአፎሚያ ረዳት
201 የሰላምታሽን ድምፅ
202 ተነሳልን
203 በንጹህ ደሙ
204 ተዋህዶ
205 እረድተሃልና
206 ንቁም
207 ምህረት ከአምላክህ
208 ጻድቃን ሰማዕታት
209 ቤተ ክርስቲያን
210 እምድንግል
211 ማርያም
212 ኧረ እንዴት ነው አቡኤ
213 መድሃኒቴ
214 አማላጄ

215 የመስቀሉ ነገር ሲገባን
216 ይላል እንደቡቴ
217 ድንግል ማርያም
218 አጌጥንበት


አጫጭር መዝሙሮች

219 ዘሰማየ ገብረ
220 ልዑል እግዚአብሔር
221 ንጽሕተ ንጹሓን
222 ኢያቄም ወሐና
223 ይቤላ ሕፃን
224 አውደ ዓመት
225 ተልኮ መጥቶ
226 ማርያም ተአቢ
227 ወረደ
228 መስቀል ብርሃነ
229 ኩሉ ዘፈቀደ
230 ጥልን በመስቀሉ
231 ወሪዶ
232 መስቀል ሃይልነ
233 የመስቀሉ ሃይል
234 በወንጌሉ ያመናችሁ
235 መስቀል ብርሃን
236 መስቀል ሃይልነ
237 አከሊሎሙ አሆ
238 እስጢፋኖስ
239 መንከረ ግርማ
240 በመኑ
241 ሆሣዕና እምርት
242 እም አፈ ደቂቅ
243 ተወልዳለችና


የሠርግ መዝሙሮች

244 መጸዕ መርዓዊ
245 መርዓዊ ሰማያዊ
246 እልል እልል
247 የቃናው ደስታ

248 ሁለቱም አንድ ሆኑ

249 ደመቀ አበራልን

250 ተፈሰሒ ቤተክርስቲያን

251 ሙሽራዬ

252 ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ

253 በሠርጋችን ዕለት

254 አጅቡት በእልልታ

255 እንደ አብርሃም እንደ ሣራ

256 ሙሽራው ሙሽሪት

257 ንጽሕት ድንግል

258 የቤታችን እራስ

259 ዕፁብ ድንቅ ሥራ

260 ድንቅ ነው በጣም

261 አምሮ ሲያበራ

262 ቃና ዘገሊላ

263 ደስ አላቸው

264 ወንድና ሴት

265 ንሴብሆ

# የመዝሙር ርእስ በቀን


1. ኅዳር 4
   - 1.1. ገሊላ እትዊ
   - 1.2. ምስለ ሚካኤል
   - 1.3. አክሊለ ጽጌ
   - 1.4. እስከ ማዕዜኑ
2. ኅዳር 18
   - 2.1. እልፍ አእላፋት
   - 2.2. ገብርኤል ምልዐኒ
   - 2.3. ሐመልማላዊት
   - 2.4. ጽላት ዘሙሴ ጽላት
   - 2.5. ንሴብሆ
3. ኅዳር 25
   - 3.1. ርግብዬ
   - 3.2. ስምህ በሁሉ
   - 3.3. ንጹም ፆመ
   - 3.4. እግዚአብሔር ሀያል ነው
   - 3.5. እስመ አልቦ ነገር
   - 3.6. ሐመልማላዊት
   - 3.7. ተክለ ሀይማኖት
4. ታህሳስ 02
   - 4.1. ልዑል ሠምራ
   - 4.2. እያቄም ወሃና
   - 4.3. ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
5. ታህሳስ 9
   - 5.1. አርሴማ
   - 5.2. ነአምን በአብ
   - 5.3. ይርድዓነ
   - 5.4. አትተወኝ አትጣለኝ
6. ታህሳስ 23
   - 6.1. አባ አቡነ
   - 6.2. የእቲሳ አንበሳ
   - 6.3. ጊዮርጊስ ሀያል
   - 6.4. ገድልከ ግሩም
7. ታህሳስ 30
   - 7.1. ሣር ቅጠሉ ሰርዶው
   - 7.2. እምሰማያት ወረደ
   - 7.3. አይኖቼ ማዳኑን
   - 7.4. በቤተልሔም
8. ጥር 7
   - 8.1. የሥላሴን መንበር
   - 8.2. ሥላሴን አመስግኑ
   - 8.3. ተወልደ
   - 8.4. ዘሰማየ ገብረ
9. ጥር 21
   - 9.1. ሞትሰ
   - 9.2. በሰላም ነዒ
   - 9.3. ወዳጄ ሆይ
   - 9.4. እግዚአብሔር እረኛዬ ነው
   - 9.5. አማኑኤል ጌታዬ
10. ጥር 29
    - 10.1. አማኑኤል ናና
    - 10.2. አድነነ እግዚኦጤና አልባ ፆም
11. የካቲት 5
    - 11.1. ጼና አልባሲሆ
    - 11.2. ንጹም ፆመ
    - 11.3. አድነነ እግዚኦ ፆም
    - 11.4. ገብረ መንፈስ ቅዱስ
    - 11.5. ጾም ጸሎታችን

12. የካቲት 12
12.1. ሕይወቴ ቢመራ
12.2. ጾም ጸሎታችን
12.3. መመኪያዬ አንተ ነህ
12.4. የአብርሃም አምላክ
13. የካቲት 26
13.1. እግዚአብሔር መልካም ነው
13.2. ድንግል የዚያን ጊዜ
13.3. በመከራ ጽና
13.4. እንዘ ይብሉ
13.5. አልፋና ኦሜጋ
14. መጋቢት 3
14.1. እኔስ በምግባሬ
14.2. ዓለምን ለማዳን
15. መጋቢት 10 ደብረ ዘይት
15.1. አቤት የዚያን ጊዜ
15.2. ከመላእክት ጋራ
15.3. ተወልዳለች
15.4. ጌታ ተነስቷል
15.5. አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ
15.6. ቸርነትህ ነው
16. ሚያዚያ 01
16.1. እም አፈ ደቂቅ
16.2. ሰላምሽ ዛሬ
16.3. ሆሳዕና በአርያም
17. ሚያዚያ 6 ስቅለት
17.1. እውነት ስለሆነ
17.2. ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን
17.3. እዩና እመኑ ሰዎች
17.4. ናና የምስጋና ጌታ
17.5. እግዚአብሔርን አመስግኑ
18. ሚያዚያ 16
18.1. ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን
18.2. ትንሳኤከ ለእለ
19. ሚያዚያ 22
19.1. መላከ ሰላምነ
19.2. እውነት በእውነት
20. ሚያዚያ 29
20.1. እምሐና ኢያቄም
20.2. አማን በአማን
20.3. እም እቶነ እሳት
21. ግንቦት 6
21.1. ዝም አትበሉ
21.2. ኃይልየ ሥላሴ
21.3. ሥላሴ ትትረመም
21.4. ማርያም ድንግል
22. ግንቦት13
22.1. ያሬድ ፈልፈለ
22.2. እውነት በእውነት ኃያል ኃያል
22.3. መንክረ ግርማ
22.4. አንትሙሰ
23. ሰኔ 4
23.1. ቀዳሚሁ ቃል
23.2. ጸሀይኑ ንብለከ
24. ሰኔ 15
25. ሰኔ 25
25.1. ደስ ይበለን
25.2. ያከብርዋ ለሰንበት
26. ሀምሌ 2
26.1. ብርሃናተ አለም ጴጥሮስ
26.2. ጴና አልባሲሁ
26.3. ለሀገሪትነ ሰላማ
27. ሐምሌ 9
27.1. እኔስ እዘምራለሁ
27.2. እምኩሉ ይሄይስ
28. ሐምሌ 23
28.1. ጸጋን የተመላሽ
28.2. ጋሻውን ይዞ በፈረስ

29. ሐምሌ 30
  29.1. ማርቆስ ሐዋርያ
30. ነሐሴ 7
  30.1. አአትብ ወእትነሰእ
  30.2. እናት አለኝ
31. ነሐሴ 14
  31.1. ሶበሰ ኪዳንኪ
  31.2. አሀደ ለከ
  31.3. እንዲህ አለው
32. ነሐሴ 21
  32.1. በምን በምን እንመስላት
  32.2. ዜኖኩ ጽድቅከ
  32.3. ማርያም አርጋች
  32.4. አማን በአማን
  32.5. በሰላም ንዒ
33. ነሐሴ 30
  33.1. ጸልይ ሀበ
34. መስከረም 7
  34.1. የዕለት የዓመት
  34.2. ንሴብሆ
35. መስከረም 14
  35.1. መስከረም ጠባ
36. መስከረም 21
37. መስከረም 28
  37.1. በልዎ ለእግዚአብሔር

## 1. አፌ ለምስጋና

አፌ ለምስጋና ለውዳሴ ይከፈት /2/
ድንቅ አድርጎልኛል በአስጨነቁኝ ፊት
አፌ ለምስጋና ይከፈት

ፊቱ ተደፍቼ ነግሬው ምስጢር
ፈጥኖ ፈጸመልኝ የልቤን ነገር
ድንቅ ድንቅ ነገር ለኔ እየሰራ
ሰገነት አቆመኝ ክብሩን እንዳወራ

ያለምኩት እንደጉም ሲጠፋብኝ በኖ
ባዶነት ሲሰማኝ ይረዳኛል ፈጥኖ
የአፌን ልመና ከቶ የማይረሳ
ልቤ ይደሰታል ስሙን እያነሳ

ምንም በሌለበት ተስፋ ሆነኝ ጌታ
ምስጋና አቀረበች ነፍሴም ተደስታ
አይኔ ተመልክቷል ድንቅ ነገር ደግሞ
ሸባን ሲያራምድ አልጋን አሸክሞ

ምስጢሬን ሳወራ ገብቼ መቅደሱ
ሰማኝ በፅሞና የታመነው እርሱ
መጣሁኝ ደስ ብሎኝ እኔም እንደሐና
በፈጣሪዬ ፊት ለማድረስ ምስጋና

## 2. <u>የብርሃን ጎርፍ ናት</u>

የብርሃን ጎርፍ ናት ድንግል እናታችን
ከሰማይ እያበራች ደስ አለው ልባችን
ፍቅርሽን ሰላምሽን ድህነት ይሁነን
ፍጥረት <u>በሙሉ</u>/2/ ፊትሽ ይወድቃሉ
ጸጋሽ <u>ይድረሰን</u>/2/ ይስጠን እያሉ

የኔ ልብ ምን ፅድቅ አለው አንቺን ለማስተናገድ
የሃጢያት ጎተራ ነው የተሞላ በስስት
ኧረ እንዴት/2/ ድንግል ትኑርበት
አትፀየፍም የኔን ልብ ታሰናዳዋለች
ስለሃጢያቴ የኔ እናት ምልጃ ታቀርባለች

ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት
ህሊናቸው ይመለስ እንጸልይ ለዚህ ጥፋት
አምላክን ይዛ ነው የምትመጣው
እርሷን ስንመልስ ጌታን ነው የምናስቀይመው

## 3. ከጌታዬ ፍቅር የሚለየኝ ማነው

ከጌታዬ ፍቅር የሚለየኝ ማነው/2/
መከር ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሰራው/2/
ግንቡ ንጹህ ውሃ መሰረቱ ደም ነው/2/
ሳይነጋ ተራምደን እንጓዝ በጠዋት/2/
በደሙ መስርቶ ከሰራልን ቤት/2/
የውሃ ግድግዳ የደም መሰረት/2/
ይኸው ከዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

## 4. ምን ሰማህ ዮሐንስ

ምን ሰማህ ዮሐንስ በማህፀን ሳለህ/2/
ህጻን ሆነህ ነብይ ለክብር የተጠራህ/2/
እንደ አንበሳ ጥጃ ያዘለለ ደስታ/2/
ምን ዓይነት ድምጽ ነው ምን አይነት ሰላምታ/2/
ከተፈጥሮ በላይ ያሰገደህ ክብር
እንዴት ቢገባህ ነው የአምላክ እናት ፍቅር/2/
ሌላ ድምጽ አልሰማም ከእንግዲህ በኋላ
ለውጦኛል እና የሰላምታ ቃሏ/2/
በረሃ ያስገባህ ለብዙ ዘመናት
ምን ያለ ራዕይ እንዴት ያለ ብስራት/2/
እንደ አዲስ ምስጋና ስልቱ የተዋበ
ተደምጦ የማያውቅ ጭራሽ ያልታሰበ/2/
ከሴት የተገኘ ከደቂቀ አዳም
ድንግል ስለሆነ በሕይወቱ ፍፁም/2/
ከማህፀን ሳለ ተመርጦ በጌታ
ለማዳመጥ በቃ የኪዳን ሰላምታ/2/

## 5. አንደበትን ስጠኝ ጌታዬ

አዳኙ ስምህን ዘወትር ልጠራበት
ቅዱስ ኃያል ህያው ክብር የምልበት
ከሃጢያት የራቀ ሐኬት የሌለበት
ምስጋናህን ብቻ የምናገርበት/2/
አንደበትን ስጠኝ ጌታዬ/4/
ሕይወት የሆነውን ቃልህን ሰባኪ
ገናናነትህን ክብርህን ተራኪ
ለንስሃ ህይወት በጎችህን ጠሪ
እንደ ሐዋሪያት ፍቅርህን መስካሪ/2/
ከከሃድያን ጋር የማይተባበር
ፆምና ጸሎትን የሚያዘወትር
ከጽድቅ ስራ ጋር መልካም ህብረት ያለው
በምድራዊ ምኞት የማይታለለው/2/
ፈተና ሲገጥመኝ በመከራ ጊዜ
የህዘን ጥላ ጋርዶን ሲከበን ትካዜ
ተመስገን የሚል በችግር በደስታ
ርቱዕ አንደበትን ፍጠርልን ጌታ/2/

## 6. የጽድቅ በር ነሽ

የጽድቅ በር ነሽ የሙሴ ጽላት
አክሊለ ሰማዕታት ምዕራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹህ አክሊላችን
ሐመልማለ ሲና እመቤታችን/2/
እመቤታችን የእኛ ምርኩዝ ነሽ እመቤታችን ከለላም ሆንሽን
›› የእሳት ሙዳይ ›› እሳት ታቀፍሽ
›› በብርሃን ተከበሽ ›› ወርቅ ለብሰሽ
›› ከሴቶች ሁሉ ›› አብ መረጠሽ
እመቤታችን ድንግል ሆይ ልጆችሽ እመቤታችን ዘውትር ይጠሩሻል
›› ስምሽን ለልጅ ልጅ ›› ያሳስቡልሻል
›› በተሰጠሽ ጸጋ ›› ባማላጅነትሽ
›› ምህረትን አሰጪን ›› ከመሃሪው ልጅሽ
እመቤታችን ያልታረሰች እርሻ እመቤታችን ዘር ያልተዘራባት
›› የህይወትን ፍሬ ›› ሰጠችን የእኛ እናት
›› የታረደው መሲ ›› እናቱን ወደዳት
›› በቀኙ ቆማለች ›› ድንግል እመቤት ናት
እመቤታችን የእውነት ደመና እመቤታችን ዝናብ የታየባት

›› ወዳናለች ድንግል ›› የታተሙች ገነት
›› ክብር ለሆነችው ›› ኑ እንዘምርላት
›› ደስ ይበልሽ እንበል ›› የብርሃን እናት

## 7. አለቴ ነህ አንባዬ

አለቴ ነህ አንባዬ ጉልበቴ ነህ ጌታዬ/2/
በተከበበ ከተማ ከቶ አትጣለኝ ለብቻዬ/2/
እንደ ወጣ ይቅር አትበለኝ
በንስሀ ቤትህ ምልሰኝ
በመቅደስህ ዓለት አቁመኝ
ማዕበልና ንፋስ ሳይነቅለኝ
የነገን አላውቅም እጣዬን
በቤትህ ጸንቼ መኖሬን
አላምነውምና ከፉ ልቤን
ስፈራው እኖራለሁ የመጪውን
አልመካም እኔ እፈራለሁ
ወድቆ ስላየሁኝ የቆመው ሰው
ባልተሰበረ ልብ በመኖሬ
መቆሜን አላውቅም እስከዛሬ
በወደቀው ጨከኜ ፈርጄ
የደካማው በደል አለ በጄ
ማንም ስላልሾመኝ ፈራጅ አድርጎ
ልቤን መልስልኝ ወደ በጎ

## 8. ኑ በእግዚአብሔር

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን/2/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ሕይወት ላሸጋገረን

ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን/2/
የሰማዩን መንግስት እርስቱን ለሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን
ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል
ከአለት ላይ የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛልህ ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስግነው ከጠዋት እስከማታ

በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛጀት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት
በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን
የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ

## 9. ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ ለኖህ ሐመሩ ሰላም ለኪ የአሮን በትሩ
የቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ ሰላም ለኪ የጌዴዎን ጸምሩ
የሰለሞን መንበረ ክብሩ ሰላም ለኪ ፍሬ ስብሐት መዝሙሩ/2/
እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ/2/
ሰላም ለኪ ሰረገላው ለአሚናዳብ ሰላም ለኪ
መና ያለብሽ ንጹህ መሶብ ሰላም ለኪ
ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ ሰላም ለኪ
የይስሐቅ መዓዛ/2/
እንዘ ንሴብሖ ለበረከትኪ ዘምስለ አምሃ እሰግድ ለኪ/2/
ሰላም ለኪ ህብስተ መና ዘ እስራኤል ሰላም ለኪ
የሰማዕታት ንጹህ አክሊል ሰላም ለኪ
እጸ እጳጦስ ዘሲና ሰላም ለኪ
የኤልያስ መና/2/
እንዘ ንሴብሖ ለበረከትኪ ዘምስለ አምሃ እሰግድ ለኪ/2/

## 10. ባክኛለሁና

ባክኛለሁና በስጋ ፈተና
የዚህ ዓለም ሀዘን ጫፍ የለውምና
ፈጥነሽ ወደእኔ ነይ ከትንሿ ቤቴ
አጽናኚኝ እመአምላክ ድንግል እመቤቴ

ባህሩ ትልቅ ነው ድንግል እመቤቴ
ትንሽ ናት መርከቤ ›› /2/
የመንገዴ መሪ ››
አንቺ ነሽ ወደቤ ›› /2/

በመንገዴ ስዝል ድንግል እመቤቴ
ዓለም ትስቃለች ›› /2/
መመኪያ እመቤቴ ››
ወዴት ነች እያለች ›› /2/

በቀቢጸ ተስፋ ድንግል እመቤቴ
እንዳልወድቅብሽ ›› /2/
በቀንም በሌሊት ››
ተስፋዬ አንቺ ነሽ ›› /2/

የለም ያተረፍኩት ድንግል እመቤቴ
ወጥቼ ወርጄ ›› /2/
ትርፌ አንቺ ብቻ ነሽ ››
ጽዮን አማላጄ ›› /2/

## 11. አማኑኤል ተመስገን

አማን በአማን /2/
አማኑኤል ተመስገን /2/
ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈል /2/
ድብቁን ሃጢያት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ
ለእኔ ሃጢያትስ የለውም ቦታ
በየደቂቃው ሃጢያት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
ምህረትህን ልከህ አድነኸኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በሃጢያት መኖሬ
ዓለም በሃጢያት እየሳበችኝ
በፍቅርህ በደስታ መኖር አቃተኝ
የሃጢያት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

## 12. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሃለሁ እልል እልል
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል /2/
እገዛልሃለሁ መድሃኒዓለም /2/
ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
እረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅክልኝ የልቤን ትካዜ
አምላኬ ጉልበቴ ሐይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቂአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ስጦታ
በቀንም በሌትም ለሚያበራ
መንክር ለባህሪይው እጹብ ለአንተ ስራ
አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለትንሿ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል

## 13. ቅያሜው ይቅርና

ቅያሜው ይቅርና አምላክ ሆይ ታረቀን
አንተ ስለራከን ሞት ነው የከበበን /2/
እስከመቼ ድረስ ህዝብህ ተጎሳቁሎ
በረከሰ መንፈስ በርኩሰት ተጥሎ
ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት
እባክህ አምላኬ ኢትዮጵያን ታረቃት /ሀገሬን/
የዘመኑ ጣዖት ገንዘብ እያሳተን
ይህ ደካማ ስጋ አምላክን አስተወን
ግብዝነት ሞልቶት ፈራሹ አካል
በነፍስ በሽታ ህዝባችን ታሟል /2/
ክንፋችን ተመትቶ መብረር አቅቶናል
በመንፈስ በሽታ ህዝባችን ታውኳል
ራዕይ የሌለው ተራ ሰው ስለሆን
እባክህ ጌታችን በፍትነት ታረቀን /2/
ጸጋህ የተለየን ባዶነት የሞላን
ፍቅር የተነፈግን ሰላም የጎደለን

ሆነን ስለቀረን እግዚአብሔር ታረቀን
ጽድቅን አድለን ጽድቅ እንደተመኘን /2/

## 14. ሊረዳን መጣ

ሊረዳን መጣ ኃያል ሚካኤል
ይጠብቀናል ኃያል ሚካኤል

የሙሴ ጠባቂ ኃያል ሚካኤል
መንገድ የመራኸው ››
የኤርትራን ባህር ››
ከፍለህ ያሻገርከው ››

ክብርህ ከመላእክት ኃያል ሚካኤል
ከፍ ከፍ ያለ ነው ››
ታላቁ አለቃ ››
ከቶ እንዳንተ ማነው ››

ከሃጢያት በረሃ ኃያል ሚካኤል
መጠለያ ሆነን ››
ጠላት በመንገድ ላይ ››
እንዳያስፈራራን ››

## 15. <u>ቋንቋዬ ነሽ ድንግል</u>

ቋንቋዬ ነሽ ድንግል መግባቢያዬ
መልስ የማገኝብሽ ከጌታዬ /2/
ባንቺ ቀርቤአለሁ ከአምላኬ ፊት
ቤቴ ሞልቶልኛል በበረከት /2/
በምን ስራዬ ነው በፊቱ የቆምኩት
መቼ በቅቼ ነው ስሙን የጠራሁት
አስታራቂ እናት አንቺን ስለሰጠኝ
ስለ ቃል ኪዳንሽ አቤት ልጇ በይኝ /2/
ቅድስና ሕይወት ከኔ ተሰውሮ
በውሸት በሃሜት አንደበቴ ታስሮ
በእመ አምላክ ፍቅር አዲስ ሰው ሆኛለሁ
እንደ መላእክቱ ይኸው እዘምራለሁ /2/
ስለ እማምላክ ብሎ ያፈረ የለም
ባንቺ ያልከበረ ሰው አይገኝም
እንደ ባለማዕረግ እኔም ሰው መባሌ
አንቺን አግኝቼ ነው ድንግል መሰላሌ /2/

ሰላም ለኪ ብዬ ስጀምር ሰላምታን
ሐሴት ይሞላዋል መላው ሰውነቴን
እንደ ቅዱስ ኤፍሬም በምስጋናሽ ልጽና
በእጆችሽ ያለው አምላኬ ነውና /2/

## 16. ስለማይነገር ስጦታው

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
    የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ህያው እንድንሆን
    ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
    ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ንፋስን ገልጾ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
    ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
    የምንመካበት ትንሳኤን ሰላምን የሰጠን
    ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ከሲኦል እስራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

## 17. <u>የአዋጅ ነጋሪት ቃል</u>

የአዋጅ ነጋሪት ቃል በበረሃ እያለ
የእግዚአብሔር መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ አስረዳ
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን
የደናግል መመኪያ የነብያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልኝ ድንግል ማርያም /2/
ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመስርት ሁላችን
ማረፊያ እንዲሆነን ለመጪው ሐብታችን
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርህራሄ በእኛ ላይ ይስፋፋ
ስጋና ደምህን በክብር አግኝተናል

ሕይወት እንደሆነን አምላክ ተማጽነናል
ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብሱን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንጻን አደራህን
በክፉ እንዳንጠፋ እኛ ልጆችህ

## 18. ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮሃለሁ
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ

ውዳሴ ማርያም በሰርክ ጸሎት ላይ ውዳሴ ማርያም ዜማ ስናደርስ
›› ድንግል ትመጣለች ›› በቤተ መቅደስ
›› የብርሃን ምንጣፍ ›› ከፊቷ ተነጥፏል
›› ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ ›› ያመሰግናታል
ውዳሴ ማርያም አባ ህርያቆስ ውዳሴ ማርያም ምስጋና ያደርሳል
›› የቅዳሴው ዜማ ›› ልብን ይመስጣል
›› በጎ ነገር ልቤ ›› አወጣ አያለ
›› ዳዊት በገናውን ›› እየደረደረ
ውዳሴ ማርያም የንጽህናችን ውዳሴ ማርያም መሰረት ነሽና
›› አንቺን ለማመስገን ›› ልቦናዬ ይጽና
›› ተፈስሒ ድንግል ›› ኦ ቤተልሔም
›› ካንቺ ተወለደ ›› መድሃኒዓለም
ውዳሴ ማርያም ቅድሳት ሁሉ ውዳሴ ማርያም ዙሪያሽን ከበዋል
›› አባ ጊዮርጊስም ›› ንኢ ድንግል ይላል
›› በወርቅ ዙፋን ላይ ›› ተቀምጠሽ ሳይሽ
›› ልቤ ተሰወረ ›› ድንግል በግርማሽ

## 19. አምላክ ተክለ ሀይማኖት

አምላከ ተክለሀይማኖት ማረን (2)
አምላከ ቅዱሳን ታረቀን (2)
ስለ ቃል ኪዳንህ በቁጣህ አታጥፋን
ሃዋርያው ቅዱስ ተክለ ሀይማኖት
የእቲሳ አንበሳ የእኔ አባት
ቁጣውን አብርደው ተክለሀይማኖት
በምልጃ ተነሳ የኔ አባት
ቁጣውን አብርደው ተክለሀይማኖት

ቤተሰብ ሆነሃል የእኔ አባት
ከሰማይ ካህናት ተክለሀይማኖት
ቤተሰብ ሆነሃል የእኔ አባት
የስላሴን መንበር ተክለሃይማኖት
ለማጠን በቅተሃል የእኔ አባት
ከከርቤ ከሚአ ተክልሀይማኖት
ከሰሊክም በልጧል የእኔ አባት
የጻድቁ ጸሎት ተክልሀይማኖት
በእግዚአብሔር ፊት ሸቷል
ስለቃልኪዳንህ ተክለሃይማኖት
አምላክ ይለመናል የእኔ አባት
ጸሎት ሲደርስ ተክለሀይማኖት
እኛን ይታረቃል የእኔ አባት
ተማጽነንብሃል ተክለ ሃይማኖት
ጌታ ሆይ በስሙ የእኔ አባት

በጻድቁ ጸሎት ተከለሀይማኖት
በሰባራ አጽሙ የእኔ አባት
ኢትዮጵያን በሙሉ ተከለሃይማኖት
አስተምሮ ሲመለስ የእኔ አባት

አጽመ ርስቱ ሆነችህ ተከለሀይማኖት
ደብረ ሊባኖስ የእኔ አባት
የጻድቁ መንፈስ ተከለሀይማኖት
ከቅዱሳን ጋራ የእኔ አባት

ከልባችን ገብተህ ተከለሀይማኖት
ብርሀንን አበራ የእኔ አባት
በጸሎት ስቁም ተከለሀይማኖት
ስምህን ስጠራ የእኔ አባት
ነፍሴ ተደሰተች ተከለሀይማኖት
ሲርቀኝ መከራ የእኔ አባት

## 20. እባክህ ወዴት ነህ

ለመዳኑ ህይወት ለጽድቁ ጠርቼህ
ከዓለም ለይቼ በፍቅሬ መርጬህ
በረከትና ፍቅር ሰላሜን ወርውረህ
ልጁ የምወድህ እባክህ ወዴት ነህ
ይልሃል እግዚአብሔር እባክህ ወዴት ነህ
ከዓለም ጉያ ውስጥ ሽብር ከተሞላው
ከስንጥቅ አለቶች ጎድጓዳ ከሆነው
የአራዊቱ ግርማ የአንበሶቹ ግሳት
የጨለማው ክብደት የፍጥረት ማዛጋት

ከእንዲህ ያለ ስፍራ ተወርውረህ ነወይ
ቀናት ተቆጠሩ አይኖችህን ሳላይ /2/
ከቅዳሴ የወጣ ምስጋና ስቀበል
ጎላ ያለው ድምጽህ ተሰውሮብኛል
በቅድስቱ በኩል በምትቆምበት በቅዳሴ ጊዜ
አይኖቼ ስላጡ ፈልገው ፈልገው ይዞኛል ትካዜ /2/
ልጄ ምን በደልኩህ ምን አጎደልኩብህ
ትተኸኝ የሄድከው እንደዛ ስወድህ
ዘወትር ፊትህን ሳየው ደስ እያለኝ
ደስታዬን በሀዘን ምነው ለወጥክብኝ /2/

## 21. <u>ግሩም ድንቅ ነህ</u>

ግሩም ድንቅ ነህ አምላኬ ግሩም ድንቅ ነህ
ግሩም ድንቅ ነህ ጌታዬ ግሩም ድንቅ ነህ
ሰው የጣለውን ከምድር ከፍ ታደርጋለህ
የተረሳውን አምላኬ ታስታውሳለህ

ከቤተሳይዳ ያነሳል በአልጋ ያለውን
መተመቅ ሽቶ ረዳት ወገን ያጣውን
ከሃጢያተኛ ጋር ይገባል እራት ሊበላ
በቀል አያውቅም ጌታዬ ከፍቅር ሌላ

እንደ አምላካችን <u>ማንም የለም</u> /2/
እንደ እግዝአብሔር <u>ማንም የለም</u> /2/
እንደ ፈጣሪ <u>ማንም የለም</u> /2/
እንደ አማኑኤል <u>ማንም የለም</u> /2/

## 22. እኔስ በምግባሬ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ /2/
እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ /2/
ያንን የእሳት ባህር እንዳላይ አደራ
ድረሽልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ /2/
የዳዊት መሰንቆ የእስራኤል መና
የናሆም መድሃኒት ንኢ በደመና /2/
አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ /2/

አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማጸንሻለሁ በደሌን አውቄ /2/

# 23. <u>የሐሰት ዳኝነት</u>

እውነት ስለሆን እየሱስ ክርስቶስ
ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሐሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ሕይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድን ነው
ከቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑለትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለ በደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል /2/
የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉት
እሩህሩሁን ጌታ አቻኩለው ገደሉት
ሞትን አስወጎዶ ቢሰጣቸው ህይወት /2/
ስለቸርለቱ ስድብን ከፈሉት
ስለርህራሄው የእሾህ አክሊል ሰጡት
ሐሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው
መራራ አስጎነጬት ጨክኖ ልባቸው /2/
ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
ይጮኹ ነበር ይገደል እያሉ /2/

## 24. ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ

ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ /3/
የፍቅርን ሕይወት እንድትለብሱ /2/
ሁሉን በሚችል በአምላክ ጥላ
በእረፍት ውሃ ስር አርፈናልና
ሰላምና ፍቅር ህይወት በሚሰጥ
ወደ ጌታችን እንሂድ እንሩጥ
ምህረትና ፍርድ በእጁ የያዘው
የሰላም አባት ወድሃኒዓለም ነው
ህይወት የሆነን በመስቀል ውሎ
ብርሃን ሰጠን ጨለማን ሽሮ

የሚያስደነግጥ የሚያስጨንቀን
ይጠፋልና እርሱን ተማጽነን
በቀን ከሚበር ፍላጻ ሁሉ
ይታደገናል በቅዱስ ቃሉ
እግርህ በድንጋይ እንዳይመታ
በፈተና ውስጥ እንድትበረታ
መቅሰፍት ከቤትህ እንዲከለከል
ይጠብቅሃል ሌሊትና ቀን
ስሙን ያወቀ ህይወት መሆኑን
ይመላለሳል ከሃይል ወደ ሃይል
ረጅም እድሜ ይጠግባል እርሱ
ብርሃን ይሆናል የጸጋ ልብሱ
አቤቱ አንተ ተስፋ ነህና
የምትመግብ የፍቅር መና
ማዳንህ እኛን አስደስቶናል
እንዲህ ያለ ክብር ከየት ይገኛል

## 25. እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ

እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ቸርነት አድርገህ /2/
እድሜ ለንስሐ እንደ ህዝቅያስ ሰጥተህ
ጠማማውን ልቤን በቃልህ አቃንተህ
አላውቀውም ብሎ ሲጠየቅ ያመጻው
ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሶስት ጊዜ የካደው
የጅረት ወንዝ ነው የሰጠኸው እንባ
ጴጥሮስ ተጸጽቶ ንስሐ እንዲገባ
ጽዋው እንዳይደርሰኝ የይሁዳ እድል
ልጅህ ሆኖ ውሎ ኃላ መኮብለል
ጴጥሮስ እድለኛው አልቅሶ ተማረ
በትዕቢቱ ይሁዳ እንደወጣ ቀረ
ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ
በንስሐ ጠራት ጌታ በገሊላ
ታድሳ ተነሳች በእንባዋ ብዛት
እግሩ ስር ተደፍታ ማርያም መግደላዊት
አመጸኛው ልቤ ዛሬስ መቼ ይተኛል
በሃጢያት በዝሙት በስርቆት ይዋኛል
ወደ ቀድሞ ግብሩ እንዳይመለስ
ፍቅርህ በእኔ ሰርጾ ሃጢያቴን ደምስስ
በደላችን ሁሉ ሳታስብ ትተህ
በምጽአትህ ሰዓት ከጻድቃን ቆጥረህ

ነጭ ልብስን ለብሰን ሆነን ካንተ ጋራ
በሩ ሳይዘጋ አስገባን አደራ

## 26. <u>በሀዘኔ</u>

በሀዘኔ በጭንቀቴ መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ
እመአምላክ አደራ ድንግል እመቤቴ /2/
ለዓለም ተዘርግቶ እጇ ባዶ ሆኗል
የራሴ ላይ አክሊል ተሽቀንጥሮ ወድቋል
ከኤልዛቤል ሸሽቼ መጣሁኝ ወደ አንቺ
የጎሰቆልኩትን እኔን ተመልከቺ
የእግሬ መሰናክል ለዓለም ደስታ ነው
ተስፋ ቢስ መሆኔ ለጠላቴ ድል ነው
የደስታ መመንጫ የኤልሳቤጥ ዘመድ
እንዳልሰናከል ምሪኝ በመንገድ
ምድር ትለኛለች ተስፋ ቢስ ብቸኛ
ሳለቅስ ሳነባ አይታኛለችና
ከቤተመቅደሱ ለእኔስ ዘመድ አለኝ
በሀዘኔ ሰዓት አይዞህ የምትለኝ
ከአመድ የወደቀ ትንሽ ገንዘብ አለሽ
ልብሽ እራርቶልኝ ፈልጊኝ አጥብቀሽ
እምነቴ እንዳይደክም እንዳልጠፋ ልጅሽ
አድጊያለሁና ከደጀ ሰላምሽ

## 27. እግዚአብሔርን ጠራሁት

እግዚአብሔርን ጠራሁት በሀዘኔ ጊዜ
እግዚአብሔርን ጠራሁት በጭንቀቴ ጊዜ
አወጣኝ ከጭንቀት ከሀዘን ከትካዜ /2/

የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና
ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሏልና
በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለሁ /2/
ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና አቀርባለሁ /2/

እንደ ቃልህ መጓዝ መራመድ አቅቶኝ
የሃጢያት መንገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ
ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞ ስጸጸት /2/
አላሳፈረኝም መጣ በምህረት /2/

ኖህን እንዳዳንከው እኛንም አድነን
ከቀስቱ እንድናመልጥ ምልክትን ስጠን
በትርህ ምርኩዝህ እነሱ ያጽናኑኝ /2/
አንተ ከኔ ጋር ነህ አልፈራም ክፉውን /2/

በበዛ ምህረቱ ያለፈውን ትቶ
በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ
ሊቀበለኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ /2/
ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ /2/

## 28. እርዳኝ ዝም አትበል

እርዳኝ ዝም አትበል የሰራዊት ጌታ
ተስፋ እንደሌለው ሰው ልቤ ኢያመንታ
አንተን ለማመስገን የነበረኝ ብርታት
ዛሬስ ተስኖኛል አቅቶኛል መትጋት

ጨንቆኝ እጣራለሁ ጺጋ አጣ ህይወቴ
እባክህ አርመኝ እርዳኝ መድሃኒቴ
ልቤ ድንጋይ ሆኖ ቃልህ አልሰበረው
የእጅህን ስራ ጌታዬ አስተካክለው

የክርስትና ኑሮ ስርዓቱን አፍርሼ
አለቅሳለሁ ጌታ በሃጢያት ተከስሼ
ሰላምና ፍቅር ነበር ክርስትና
እኔ ግን ተናወጽኩ አልጸናሁም ገና

ስራዬና ቃልህ አልገናኝ አሉኝ
በጠማማው ልቤ አንተን አሳዘንኩኝ
ጽኑ መሰረት ነው የህይወት አለት
እየተናወጽኩኝ ኢቃተኝ መጽናት

በእረፍት ውሃ ዘንድ በለመለመው ሳር
በጎችህን ሁሉ በፍቅር የምታኖር
በህይወቴ እንዲታይ የቸርነትህ ክብር
ከደጅህ ተጥዬ ለስምህ ልዘምር

## 29. የስሙ ትርጓሜ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው
የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው
እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው
የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው

ከጉድጓድ ተጥሎ ፍጹም ከሚያስፈራው
ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው
እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን
ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን

የከፉ ሰው ስራው ክፉ ሐሳብ ነውና
በቅንነት መንገድ ከቶ አይሄድምና
የሞቱን ደብዳቤ ለባህራን ሲሰጠው
ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው

ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ
ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምስጋናን ጀምሬ
ጸጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር
የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

## 30. <u>ድንግል እመቤቴ</u>

ድንግል እመቤቴ የህይወቴ ረዳት
የኑሮዬ ጣዕም ዋልታ መሰረት
<u>አለምንሻለሁ</u> /2/ ፍጹም በረከት
ትህትናሽ ሲታሰብ ድንግል እመቤቴ
በሰዎች ልቦና ድንግል እመቤቴ
<u>ግርምትን ይፈጥራል</u> /2/ ልብ ይመስጥና
ጽዮን መጠጊያ ነሽ ድንግል እመቤቴ
የአብርሃም ድንኳን ድንግል እመቤቴ
<u>የታጠረች ተክል</u> /2/ እመብዙሃን
ከሚካኤል ጋራ ድንግል እመቤቴ
ፈጥነሽ ድረሽልኝ ድንግል እመቤቴ
<u>ቅዱስ ገብርኤል ይምጣ</u> /2/ ክብርሽን ያብስረን
ከድንግል ጋር ሆነህ ድንግል እመቤቴ
ኡራኤል ፈጥነህ ና ድንግል እመቤቴ
<u>ሩፋኤል ራጉኤል</u> /2/ ንኡ በደመና
በደማችን ሰርጿል ድንግል እመቤቴ
ፍቅርዋ የማርያም ድንግል እመቤቴ
<u>ምስክር ነን እኛ</u> /2/ እስከ ዘለዓለም
በአባቶች ፋንታ ድንግል እመቤቴ
ልጆችሽ ስላለን ድንግል እመቤቴ
<u>ስምሽን ለልጅ ልጅ</u> /2/ እንዘክራለን

## 31. አልተወኝም ጌታ

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል /2/
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነሽ ይለኛል
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል
በበደል ጉራንጉር በሃጢያት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል /2/
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል /2/
ለስልጣን ለክብሬ ብዬ ስከደው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም /2/
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም /2/
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫ መቃብር ላወጣኝ እኔን
በህይወቴ ሁሉ ፍጽም ለመራኝ /2/
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ /2/

## 32. ኪዳነ ምህረት

ኪዳነ ምህረት እመቤት /2/
ነይልን /2/ ካለንበት
ከሰማያት በላይ ካለው ከማደሪያሽ /2/
ዝማሬን ከሞላው ከዘላለም ቤትሽ
የምድር ፍጥረታት ማርያም ማርያም ሲሉሽ /2/
የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ /2/
ወልዳ ያሳደገች አዝላ የተሰደደች
የጌታችን እናት ድንግል ተንከራታለች
ከእግረ መስቀሉ ከዙፋኑ ከቀኝ ቆማለች /2/
ትላንት ዛሬም ነገም ማርልኝ እያለች /2/

## 33. ጽረ አርያም

ጽረ አርያም ጽረ አርያም /2/
ክብርሽ ገናና ነው ለዘላለም

በመላዕክት ዓለም በሶስቱ ከተማ
በኤረር በኢዮር እንዲሁም በራማ
ውዳሴ ቀረበ ለሰማይ ንግስት
የአምላክን እናት በክብር አየናት

በበረሃ ያሉ ዓለምን የናቁ
ውዳሴሽን ደግመው ስምሽን የሰነቁ
አንቺን ስንጠራ ተላት ገለል ይላል
ማርያም በግርማሽ ከሳሾችን ያፍራል

ከእግሮቿ በታች ጨረቃን ተጫምታ
የክብርን አክሊል በራሶቿ ላይ ደፍታ
በቅዱሳን ሁሉ ትመሰገናለች
ዓለም የዳነባት ድንግል ማርያም ነች

ብርሃንን ለብሳ በንጽህና አጊጣ
ፍጥረትን ስትባርክ በክብር ተገልጣ
ነፍሳት ተቀደሱ በእምነት ከበዋት
ከበሮን አንስተን እንዘምርላት

## 34. <u>የጥበብ ሰዎች መጡ</u>

ሰማይና መሬት የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክትን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ

<u>የጥበብ ሰዎች መጡ</u> /2/ ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደፋና /2/

ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያ የሆንሽ
ካንቺ ተወሰደ የዓለም መድህን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርሰን

ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሀዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት

ሰብአሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእስራኤል ንጉስ ወዴት ነው እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየስርዓቱ
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግስቱ

## 35. <u>ሳር ቅጠሉ ሰርዶ</u>

ሳር ቅጠሉ ሰርዶ ሰንበሌጥ ቄጤማው
በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም የነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተሞልተው
ጌታ መወለዱን የምስራች ሰምተው

እልል በዬ ቤቴልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ /2/
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ /2/

ያ ትሁት እረኛ የትህትና አባት
ብርሃን ለበሰ በእኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ መላዕክት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት

እረኝነት ትንሽ የወረደ ግብር
ብሎ ሰው በግምት ደንግጎ ነበር
የብዙ ሰው ራስ መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ

የተነበዩለት ነብያት በሙሉ
ጌታ ተወለደ የምስራች በሉ
ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉስ
ይኸው ተወለደ እኛን ለመቀደስ

## 36. ተወለደ

ተወለደ ጌታ ተወለደ /2/
ተወለደ አምላክ ተወለደ /2/

አንዲት ብላቴና የ15 ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላዕክት አዋጅ
ፍጹም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የሚያድን የሰዎች አለኝታ

ይህ ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት
እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋህዶ
አየነው አምላክን እንደሰው ተወልዶ

ፍጹም ድንግልና ክብር የተሞላች
እንደምን አምላክን በማህፀን ያዘች
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ
ወለደችው ድንግል የሔዋን አለኝታ

አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም
በምድር ተፈልጎ እንዳንቺ አልተገኘም

በሀሳብ በግብር ንጹህ ስለሆነች
የአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

## 37. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም /2/
እናመሰግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ
የዓለም ቤዛ ነውና የማህፀንሽ ፍሬ /2/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ጽንስ
ለድኩማኖች ብርታት ነው ለህሙማን ፈውስ /2/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /2/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችንን ፋቀ
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን /2/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ /2/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ
በመንግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ /2/
እመቤታችን እናታችን ማርያም
የተማጸነሽ ይኖራል ለዘለዓለም /2/

## 38. እግዚአብሔርን ጠራሁት

እግዚአብሔርን ጠራሁት በሀዘኔ ጊዜ
እግዚአብሔርን ጠራሁት በጭንቀቴ ጊዜ
አወጣኝ ከጭንቀት ከሀዘን ከትካዜ /2/

የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና
ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሏልና
በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለሁ /2/
ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና አቀርባለሁ /2/

እንደ ቃልህ መዓዛ መራመድ አቅቶኝ
የሃጢያቱ መንገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ
ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞ ስፀፀት /2/
አላሳፈረኝም መጣ በምህረት /2/

ኖህን እንዳዳንከው እኛንም አድነን
ከቀስቱ እንድናመልጥ ምልክትን ስጠን
በትርህ ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኝ /2/
አንተ ከኔ ጋር ነህ አልፈራም ክፉውን /2/

በበዛ ምህረቱ ያለፈውን ትቶ
በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ
ሊቀበለኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ /2/
ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ /2/

## 39. <u>ሐይልን በሚሰጠኝ</u>

ሐይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ /2/
መከራም ቢገጥመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፋለሁ /2/
በሰንሰለት አስረው በወህኒ ቢጥሉኝ
መከራን አብዝተው እጅግ ቢያስጨንቁኝ
ለበጎ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌሃለሁ
ይሁን አንተ ያልከው እገዛልሃለሁ
ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተ ነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቱ ሞገስ ሆኖልኛል
ጠላቴ ቢፎክር መቼ ያሸንፈኛል
በመከራው ጽናት ጉልበቴ ደከመ
ትካዜ ከቦኛል ተስፋዬም ጨለመ
ነገር ቢሆን ባይሆን አንተን እንዳከብር
አደለኝ በጸጋህ ጌታ ያንተን ፍቅር
ከሀገር ወጥቼ በዱር መሰደዴ
ከባዕዳን ሀገር እርቄ መሄዴ
ለበጎ ነውና መቼ ይከፋኛል
ፈጽሞ እንዳልጠፋም ክንድህ ይይዘኛል

## 40. እናመስግነው

እናመስግነው እናመስግነው /2/
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው /2/
ከሃጢያት ገደል ከሞት ቤት ጎትቶ
መንግስቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘላለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለን
መቼም የማይተወን ታላቅ አባት አለን
ፍጡራን ቢንቁኝ መጎስቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋ ቢስ ነው ብለው

እውነተኛ ረዳት አምላኬ መቸ ተወኝ
ሁለት እጄን ይዞ ልጄ ተነስ አለኝ
ሞታችንን ሞቶ ህይወቱን ላደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን
ለታላቅ ውለታ ጌታ ለዋለልን
በእልልታ እንቀኝ በአንድነት ሆነን

## 41. እንደ እግዚአብሔር ያለ

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና /2/
እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና /2/
ባህር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ
ፈርአን ወደቀ አልሰራም ትምክህቱ
ደካሞቹም ጸንተው ተራመዱ
ሐይለኞችም ይኸው ተዋረዱ
የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው
ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው
ሐይለኞቹም ቢበረታቱብን
እንጸናለን በእርሱ ተደግፈን
የተወረወረው የጠላታችን ጦር
ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር
ለስላሴ ይድረስ ምስጋናችን
ተሸነፈ አዳኝ ጠላታችን
ባህር ላይ ሲራመድ ሞገስ አለው እርሱ
በግርማው ሲነሳ ጸጥ ይላል ነፋሱ
የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው
ከሐሊ ነው የለም የሚሳነው

## 42. በህዘኔ ደራሽ ነሽ

በህዘኔ ደራሽ ነሽ በጭንቀቴ
በችግሬም ደራሽ ነሽ
የአምላኬ እናት የጌታዬ እናት
ድንግል እመቤቴ ወላዲተ ቃል /2/

| | |
|---|---|
| መልካሚቱ ርግብ | ድንግል እመቤቴ |
| ማርያም እናቴ ነሽ | ›› |
| ከፍጥረታት ሁሉ | ›› |
| ገናና ነው ክብርሽ | ›› |
| የህዘኔ መጽናኛ | ›› |
| እንባዬን አባሽ ነሽ | ›› |

| | |
|---|---|
| ዋሻ መጠለያ | ድንግል እመቤቴ |
| የዘላለም ቤቴ | ›› |
| መንገድ ስሄድ ስንቄ | ›› |
| መጠጤ ነሽ ምግቤ | ›› |
| እመ አምላክ ስጠራሽ | ›› |
| ይጠፋል እርሃቤ | ›› |

| | |
|---|---|
| የእናትነትሽን | ድንግል እመቤቴ |
| ፍቅርሽን አየሁት | ›› |
| ጎጆዬን ስትሞይው | ›› |
| ባዶ የሆነውን | ›› |
| አንቺ እያለሽልኝ | ›› |
| ምን እሆናለሁኝ | ›› |

## 43. በበጎ ፍቃዱ

በበጎ ፍቃዱ ሁሉ በእርሱ ሆነ /2/
ነገር ሁሉ በእርሱ ተከናወነ /2/
ሰማይና ምድር ግብሩን ተናገሩ
ፈጥሮአቸዋልና እንዲገለጥ ክብሩ
በፈጠረው ፍጥረት የሚታወቅ እርሱ
እግዚአብሔር ይመስገን ስሙን አወድሱ
አልሆነም ያለ እርሱ ፍጹም አንዳች ነገር
ብንመረምረው በሰማይ በምድር
ፈቃዱ ነውና መልካምና በጎ
ፈጥሮ አሳይቶናል ሁሉን ውብ አድርጎ
ክረምትና በጋ ሌሊትና ቀን
ሁሉን አሳይቶ ጌታ አስተማረን
ያደደረገው ሁሉ እንከን የሌለው
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምሳሌም የለው
ያዘነውን ያውቃል ደስም ያለውን
ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ስለሚከወን
ችግርና ደስታ ለበጎ ነውና
ይህን ያስተማረን ይድረሰው ምስጋና

## 44. አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋናን ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ይቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከሃጢያት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በሐይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋር

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳኑ ጋር ልዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣኦት እንድንሰግድ ነገስታት ቢያውጁም
ሁሉ ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድሃኒዓለም

## 45. እልል በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩም ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
በሃጢአት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላለን ጠላቶቹ ሳለን
ውለታው ግሩም ነው ክብር ለእርሱ ይሁን /2/
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ስጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድሃኒዓለም /2/
ሕይወቱን የሰዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩ የማይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ /2/
ስራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ /2/

## 46. <u>እግዚአብሔር መልካም ነው</u>

እግዚአብሔር መልካም ነው /2/
በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው /2/
ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሶብን ሳለ በእኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራው ጊዜ ወሸሸጊያ ሆነው /2/
አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት /2/
በሀዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ሀዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ሀዘኔን አስረሳኝ /2/

## 47. እግዚአብሔርን አመስግኑ

እግዚአብሔርን አመስግኑ
ስራው ግሩም ድንቅ ነው በሉት
እግዚአብሔርን አመስግኑት
ስራው ግሩም ድንቅ ነው በሉት
ሰማይን ያለ ምሶሶ
ምድርንም ያለ መሰረት
ያጸናው እርሱ ነው
ስራህ ድንቅ ለው በሉት
የባህርን ጥልቀት የመጠነ
ዳርቻዋን የወሰነ
እግዚአብሔርን አመስግኑ
ስራህ ድንቅ ነው በሉት
ማዕበል ነፋስን የሚገስጽ
ፍጥረቱ ለስሙ የሚታዘዝ

ትጉህ እረኛ ድካም የሌለበት
እግዚአብሔር ስራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት
ንጹህ ባህሪይ ነው ሁሉን የሚገዛ
የነገስታት ንጉስ አልፋና ኦሜጋ
ዘለዓለም እርሱ የማይለወጥ
እግዚአብሔርን ስራህ ድንቅ ለው በሉት
ጥበብን የሚገልጥ ጥበበኛ
ፍርድ የሚያደርግ እውነተኛ ዳኛ
እንደ እርሱ ያለ ከቶ አይገኝም
እግዚአብሔር ግሩም ነው ዘለዓለም

## 48. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን /2/
አምላክ አለ መሀላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምህረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን እድሜ የጨመረልን
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን
ሃጢያትህን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ አጥዕ የጽድቅ ሕይወት
እልል በሉ የጎበኛችሁ
በምህረት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትጸልያለች
ሃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንድ እንዲያደርገን

## 49. <u>የያሬድ ውብ ዜማ</u>

የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ /2/
በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ /2/

ምድርና ሰማይ ታምርሽን ይንገሩ
ፍጥረታት በሙሉ ስላንቺ ይመስክሩ
ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ስራሽ
ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያም የለሽ

ማርያም ድንግል እረዳቴ
የምትደርሽልኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ
ተአምርሽን በዓይኔ አይቻለሁ
ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ

የእግዚአብሔር ጥበቡ ባንቺ ተገለጠ
የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ
የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ
ለፍጥረት ሁሉ መሰላል የሆንሽ

ነገ ባላውቅ እኔን ቢያስፈራኝም
አንቺ ካለሽልኝ በፍፁም አልወድቅም
በፊትሽ እንድቆም ለምስጋና
ማርያም ልበልሽ በትህትና

ትውልዱ በሙሉ ለምስጋና ይቁም
ባንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም
አዳም ከነልጁ በሰማይ በምድር
<u>ማርያም</u> /2/ ይበል ተዓምርሽን ይናገር

ጨለማውም ከፊቴ ተገፈፈ
ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ
ከጎኔ ነይ ስልሽ እጽናናለሁ
እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለሁ

## 50. <u>የማያልፍ የለም</u>

የማያልፍ የለም ሁሉም ያልፋል
ሀዘን መከራም ይታለፋል
የማጣት ዘመን ሁሉም ያልፋል
ሀዘን መከራም ይታለፋል
አንዱን ስሻገር አንዱ ይተካል
ፈታኙ ቀርቦ ፈተና አብዝቷል
ትዕግስት ጽናቱን አድለኝና
ይህም ቀን አልፎ ልይ እንደገና
የማይቻለው በእርሱ ተችሎ
ስንቱ ታለፈ ሁሉ ተጥሎ
በሚያበረታው ጌታ በርትተን
እዚህ ደርሰናል ሁሉንም አልፈን

የማያልፍ መስሎኝ አየሁ አልፌ
የማልችለውን አየሁት ችዬ
ሁሉ ሲያልፍ አየሁ ሁሉን ስትረታ
ምንድነው ዋጋህ ተመስገን ጌታ
ተስፋ ያረኩት ጠፍቷል ከፊቴ
ያስጨንቀኛል ብቸኝነቴ
እኔ አልቻልኩም ጽናት ጎድሎኛል
አልፌ ልየው ያ ይሻለኛል
አይድንም ብሎ ዓለም ወስኖ
ተስፋዬ ጠፍቶ ሁሉ ተከድኖ
በእመ አምላክ ምልጃ አልፌዋለሁ
አስጨናቂውን ድል አድርጌአለሁ

## 51. ለውዳሴሽ ልትጋ

ለውዳሴሽ ልትጋ ስምሽ ግርማ ያለው /2/
እመቤቴ እኸ እመቤቴ ስልሽ እውላለሁ /2/
ከልቤ አቀርባለሁ ምስጋና ለስምሽ
መለመኛዬ ነው ጽኑ ቃል ኪዳንሽ
በሰላምታ ድምፅሽ ያልጸና ማን አለ
ጽንሱ በማህጸን በደስታ ዘለለ
ማርና ወተት ነው የስምሽ ስያሜ
እመቤቴ ስልሽ ይቀላል ሸክሜ
ቅኔ ማህሌቱ ሰዓታት መዝሙሩ
ያመሰግንሻል ምድርና ጠፈሩ
እናቱ ነሽና አንቺ ለአዶናይ
ማለድኩኝ ከፊትሽ ይቅርታውን እንዳይ
ሰዓሊለነ ብዬ ይኸው ተርፌአለሁ
በአንቺ ተደግፌ ነገም እኖራለሁ
ነይ ነይ እልሻለሁ እንደ ካህናቱ
በሰዓታት ጸሎት ቆሜ በሌሊቱ
ዝም አልልም እኔ አወድስሻለሁ
የዓለም መከራ እረሳብሻለሁ

## 52. የወደደኝ ጌታ

የወደደኝ ጌታ ምን አድርጌለት ነው
ብዘምርለትስ ያንስበታል ይኸው

ከውድቀቴ አንስተህ ድካሜን ያገዝከኝ
ሰባራውን ድልድይ ገጥመህ ያሳለፍከኝ
በኢያሪኮ መንገድ ስለምን ቁጭ ብዬ
ብርሃን እጅግ ናፍቆኝ ከሰው ተገልዬ
የብርሃን ጌታ ወደ እኔ መጣና
ዓይኔን አበራልኝ በእጁ ዳሰሰና
ለብዙ ዘመናት አልጋ ላይ ተኝቼ
የሚረዳኝ አጣሁ ጠሉኝ ዘመዶቼ
የእኔ ጌታ አምላኬ ወደ እኔ መጣና
አልጋህን ተሸከም አለኝ ፈወሰና
አሥራ ሁለት ዓመት ደም እየፈሰሰኝ
ምራቅ እየተፉ ሁሉም ሲያንቋሽሿኝ
የጌታዬ ልብሱን ጫፉን ብዳስሰው
ኃይልም ከእርሱ ወጣ ደሜን ቀጥ አረገው
ሰካራም ዘማዊ ወንበዴ ነበርኩኝ
የአመጻኞች መሪ ደምን ያፈሰስኩኝ
ዛሬ ግን ታሪኬን ጌታ ቀይሮታል
ለኃያሉ ጌታ ምስጋና ይገባዋል

## 53. እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ

እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ
ስለስምህ እቃጠላለሁ
ፍቅርህ እኔን ይመስጠኛል
እንደ እግዚአብሔር ከየት ይገኛል

ዓለም ሁሉ በጠላኝ ጊዜ
ስንገላታ ይዞኝ ትካዜ
አንተ ከእኔ አልተለየህም
እግዚአብሔር ሆይ ወደር የለህም

ሳኦል እኔን ሲያሳድደኝ
ጎልያድም ሲዝትብኝ
ግርማ ሆነህ ከፊቴ የቆምክ
እግዚአብሔር ሆይ ስምህ ይባረክ

ሞቷል ብለው ቀብረውኝ ሰዎች
ምስኪን ሆኜ ሳይኖረኝ አንዳች
ከመቃብር ቆፍሮ አወጣኝ
አይዞህ ብሎ አምላኬ አጽናናኝ

ሐሳብህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል
ለዘለዓለም ያበራልሃል
ታማኝ ወዳጅ እርሱ ነውና
ሰላም ይሙላህ ለእርሱ ተውና

## 54. ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል /2/
መታመኛዬ እርሱ ነውና ይገባዋል ክብርና ምስጋና
ፍቅሩን እያሰብን እንቅረብ ወደ እርሱ
ይምረናልና መሃሪ ነው እርሱ
በልባችን ይንገስ ይግባ ከቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን /2/
ከቶ አላገኝም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ሐይል
በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ
ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ /2/
የለመለመ መስክ መሸሸጊያ ነው
በሰላም ወጥቼ ሰላም እገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይጠራኛልና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና
ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና
እኔስ ይሻለኛል መቅረብ ወደ ጌታ
ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ
ስለዚህ እቀርባለሁ አልቀርም ከደጁ
ጠግቤ እኖራለሁ በበረከት እጁ /2/

## 55. ደጅ ጠናሁ

ደጅ ጠናሁ ቆይቼ ኪዳነምህረትን
ተጽናናሁኝ ረሳሁ ሀዘኔን
የአምላክ እናት እመቤታችን /2/
ሞገስ ሁኚኝ ቀሪው ዘመኔን /2/
የመከራው ዘመን አለፈ እንደ ዋዛ
አንቺን ተጠግቼ የዓለሟን ቤዛ
የልጅሽ ቸርነት የአንቺም ደግነት
ባሪያሽን ሰወረኝ ከአስጨናቂው ሞት
እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያ ሁሉ መከራ
እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ
ሰላም ለኪ
ልቤ ባንቺ ጸና ከፍ ከፍም አለ
በጠላቶቼም ላይ አፌ ተናገረ

በማዳንሽ ስራ ባሪያሽ ደስ ብሎኛል
የሐያላኑን ቀስት ልጅሽ ሰብሮልኛል
እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያ ሁሉ መከራ
እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ
ሰላም ለኪ
እጄ ባዶ ሲሆን ወዳጆቼም ሸሹ
በመርገም ምክራቸው ሊለያዩኝ ሲሹ
እርሱ የሰጠኝን እርሱ ወሰደ አልኳቸው
እመቤቴ አለችኝ ብዬ አሳፈርኳቸው
እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያ ሁሉ መከራ
እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ
ሰላም ለኪ
ከአውደ ምህረቱ ሆኜ ስጠራት
ዘንበል ብላ አየችኝ ኪዳነ ምህረት
ሐሳብሽን ምንም የለም የሚመስለው
እረፍት ያገኘሁት እናቴ ባንቺ ነው
እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያ ሁሉ መከራ
እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ
ሰላም ለኪ

## 56. የይሁዳ ጉዞ

የየሁዳ ጉዞ አያዋጣምና
ዴማስ ወደ ህይወት እባክህ ቶሎና /2/
በወንጌል ገበታ መመገብ ጀምረህ
ወንድሜ ተመለስ ወዴት ትሔዳለህ
ይጠራሃልና መስቀሉን ተመልከት
የወንጌል ቡቃያ እውነተኛ ህይወት /2/
ቸርነቱን አይተህ ፍቅሩን ቀምሰኸዋል
በረድኤት ህይወት ደስታ ሞልቶልሃል
ቅዳሴው ዝማሬው እጣኑ ሸቶሃል
ዴማስ ሆይ ተመለስ እውነት ይሻልሃል /2/
ብዙ ክርስትያኖች መንገዱን ጀምረው
የዓለም አሸንክታብ ድምቀት ሲጠራቸው
ፈተናው ሲመጣ ወንጌሉን ወርውረው
ሞትን ይመርጣሉ ህይወትን ሰርዘው /2/
የመስቀሉ ፍቅር ከልብ ሳይጠፋ
በእግዚአብሔር ጉባኤ መስክረህ በይፋ

ልጄ የተባልከው በጥምቀት ቀለበት
እንዴት ትሔዳለህ ተነስተህ ወደ ሞት /2/
የክብር አክሊል ተዘጋጅቶልሃል
አምላክ ለሽልማት ዴማስ ሆይ ይልሃል
ወዴት ትሄዳለህ እባክህ ተመለስ
ክብርህን አትተው ከጫፉ ሳትደርስ /2/

## 57. ሰላም ለኪ

ሠላም ለኪ እምነ ጽዮን
ማርያም ውድስት የሕይወት ብርሃን
ሠላም ለኪ እምነ ጽዮን
ሠላም ልበንሽ ተንበርክኬ
በብጽዕናሽ ተማርኬ
መርከበ ኖህ አዳራሽ
ሠላም ለኪ ልበልሽ
ድንግል የአብርሃም ድንኳን
ሠላም ሠላም ሐረገወይን
ያዕቆብ ያየሽ መሰላል
የሰለሞን ክብር አክሊል
ጽላተ ሙሴ የኦሪት
የአሮን በትር መድሐኒት
የዋህ እርግብ የኢያቄም
የነብያት ተስፋ የአዳም
እሳተ መለኮትን የያዝሽ
ምሉዕ አምላክን የወሰንሽ
ቤተ መቅደስ የልኡል
ሠላም ለኪ እመ ወድንግል

## 58. መቼ ነው ጌታ

መቼ ነው ጌታ ኸረ መቼ ነው /2/ ጌታዬ
እንደ ቃልህ የሚሆን ጉዞዬ
አልተማርኩም አልል አስተምረኸኛል /2/
ቃልህን እንደ ወተት አጠጥተኸኛል /2/
የታል አኗኗሬ አንተን የሚመስለው /2/
በልምድ ሕይወት ነው የምመላለሰው /2/

ይህ አንደበቴማ በቃልህ ሰልጥኗል /2/
ልቦናዬ ከአንተ ከፊትህ ኮብልሏል /2/
አንተን እንደማውቅህ አብዝቼ ባወራ /2/
የተዘራው ሁሉ ፍሬ አላፈራ /2/
እዘንልኝና መንገዴን አቅናልኝ /2/
የአመፅ ስራዬን በደሌን ተውልኝ /2/
ቃልህ እንዳይሰደብ በእኔ ድካም /2/
አርመው እርሻውን መድሐኒዓለም /2/
ከእስራቴ ፈትተህ ነፃነት ስጠኝ /2/
በቀኝ አቁመህ ጌታ ሆይ ባርከኝ /2/

## 59. በመከራ ጽና

በመከራ ጽና በፈተና ጽና /2/
ለጊዜው ነውና ሁሉም ያልፋልና /2/
እዮብ ተጨነቀ በጣም ተማረረ
በመከራው ብዛት ትዕግስትን ተማረ
ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱን
በመከራ ጸና አልካደም አምላኩን
መፈተን መልካም ነው ያነጥራል እንደ ወርቅ
በመጨረሻው ቀን በክብር እንድንጸድቅ
አንዱን ሳትሻገር ሌላ ቢተካብህ
በሕይወት ዘመንህ ፈተና ቢያጠቃህ
ከአምላክህ ተስማማ እራስህን አዋርድ
በቃሉም ተመራ እንደ ፈቃዱም ሂድ
ዋጋህ ከአምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና
በርታ ክርስትያን ሆይ በመከራ ጽና

## 60. በደልህን አምነህ

በደልህን አምነህ ንስሀ ግባና
ወደ አምላክህ አልቅስ ተጸጸትና
አመስግነው ጌታን አክብረው ከልብህ
በጉብዝናህ ወራት በእርሱ ደስ ይበልህ
ስትቸገር አይቶ ንቆ የማይተውህ
አምላክህን ውደድ እርሱ ነው አለኝታህ /2/

የሃጢያትን ኑሮ አቁምና ዛሬ
ለማፍራት ተነሳ የንስሃን ፍሬ
የእግዚአብሔርን ድምፅ አትናቅ ጥሪውን
ተመለስ ይልሃል አስተውል መንገዱን
የጉብዝናህ ወራት ያበቃል ያከትማል
ድካም መሸነፍም መውደቅም ይመጣል
ተስፋህ ይጨልማል ንብረትህም ያልቃል
ወጣትነትህም መቼ ሁሌ ይኖራል
የወደቅህ ለታ ማንም አያይህም
ሁሉም ሲኖርህ ነው ካንተ ጋር የሚኖር
እስከ መቼ ድረስ እንዲህ ትኖራለህ
መለከት ሲነፋ ወዴት ትደርሳለህ
ለካህኑ ነግረህ የሰራኸውን ሃጢያት
ንስህ ተቀበል እንድታገኝ ስርየት
ቤትህን አዘጋጅ ክርስቶስ ይመጣል
ማድጋህን ከፈት እርሱም ይሞላዋል
ተመለስ ወደ እርሱ በደሙ ገዝቶሃል
እርሱም አይቀየም ሊቀበልህ ወጥቷል
አመስግነው ጌታን አክብረው ከልብህ
በጉብዝናህ ወራት በእርሱ ደስ ይበልህ

## 61. <u>የዶኪማስ ጓዳ</u>

የዶኪማስ ጓዳ ሆኖብኛል ቤቴ
ያንቺን ድንቅ ስራ ናፍቃለች ሕይወቴ
ጊዜዬ እንዳያልፍ በዋዛ ፈዛዛ
ያለኝን ሰምቼ ለእርሱ እንድገዛ
የልቦናዬ ጋን ባዶ ሆኗልና
አማልጅኝ ከልጅሽ በቃሉ እንድሞላ /2/
ማነው ውስጡን ያየ የጎደለውን
የዶኪማስን ልብ ያስጨነቀውን
እስኪ እንጠይቀው እድምተኛውን
ወይኑን አጣጥሞ ያደነቀውን /2/
አስቀድሞ ያለኝ መናኛ ነበረ
አሁን ግን ሚስጢሩን ልቤ መረመረ
ያንቺን እናትነት አምኖ ተናገረ
ድንቅ ስራሽንም ለዓለም መሰከረ /2/

## 62. ወደ አንተ እሰግዳለሁ

ወደ አንተ እሰግዳለሁ ሳለሁ በሕይወቴ
ለአንተም እገዛለሁ እስከ እለተ ሞቴ
አንተ ነህና መድሃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ /2/

የነፍስ የስጋዬ የሕይወቴ ቤዛ
አትበለኝ ችላ በደሌ ቢበዛ
አንተን አምኜ እኖራለሁ ወዴት እደርሳለሁ
አንተን አምኜ እኖራለሁ በአንተም እመካለሁ

ሳይመሽብኝ ቀኑ ሳይጨልም ድንገት
በጽድቅ ጎዳና ልጓዝ ወደ ፊት
ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት /2/

## 63. <u>ዓለምን ዞሬ አየሁት</u>

ዓለምን ዞሬ አየሁት ሁሉን በተራ ቀመስኩት
<u>ፈጽሞ የለም</u> /2/ ሠላም እንደ ልጅሽ ቤት
ሀብት ንብረቴን ጨረስኩና
ጉልበቴ ሁሉ ደከመና
<u>ጎስቋላ ሆንኩኝ</u> /2/ ደካማ የሌለው ጤና
ስቃ አሳስቃ ተቀብላ
መልኳን አስውባ ተኳኩላ
<u>ዛሬ ጣለችኝ</u> /2/ ይህች ዓለም አትረባም ብላ
የትላንትና ወዳጆቼ
ዛሬ ሲሆኑ ጠላቶቼ
<u>ባከኜ ቀረሁ</u> /2/ በዓለም ላይ ተንከራትቼ
የአባቴ ቤት ሲናፍቀኝ
ፍቅሩ ምህረቱ ትዝ ሲለኝ
ጎስቋላው ልጅህ ደካማው ልጅህ ጌታ ሆይ ዛሬ መጣሁኝ
እናቴ አንቺን ንቄ ትቼ
የአባቴን ቤት እረስቼ
ተሰቃየሁኝ ተንከራተትኩኝ ልደሰት በዓለም ገብቼ
አባቴ ሲያየኝ ተደስቶ
ጎረቤቶቹን ሁሉ ጠርቶ
<u>ሰርጉን ደገሰ</u> /2/ የበደልኩትን እረስቶ
እስከ አሁን ድረስ በድያለሁ
ዓለም ደህና ሁኚ አብቅቻለሁ
<u>ወደ አባቴ ቤት</u> /2/ ዳግመኛ ተመልሻለሁ

## 64. <u>ኀሰቆለ</u>

የምድራዊ ሕይወቴ ኀሰቆለ /2/

<u>ኀሰቆለ</u> /2/ ድንግል ኀሰቆለ ድንግል

የጌታዬ እናት እመቤት
ልጅሽ እንዳልጠፋብሽ የአምላክ እናት
ከልጅሽ ጋር ነይልኝ አትለይኝ
አጽናኝ መካሪዬ ነሽ አትራቂኝ ቅረቢኝ

የስጋ ምኞቴን እያሳደድኩ
ከአምላኬ ኮበለልኩኝ እረከስኩኝ
የፍጥረት አማላጅ ሆይ እመቤቴ
ዋስ ጠበቃ ሁኝልኝ መድሃኒቴ ለህይወቴ

በልቤ ውስጥ ሳይልኝ አዛኝቷ
ፍቅርና ውለታሽን እንዳልረሳ
ልጅሽ አይሳነውም ሁሉን መስጠት
ያብቃኝ በክብር እንድቆም በሀይማኖት በጽናት

## 65. ከወገኔ ጋር

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁ
በደስታ በሐሴት ስሙን እጠራለሁ
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና
ዘወትር አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና

ህዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት ይሞላል ዝማሬው ይገርማል
ከእጣኑ ጋር ወደ ላይ ይወጣል

ቀሳውስቱ ሌሊት ማህሌት ሲያቀርቡ
ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ
ብርሃኑን ለብሰን በደስታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ህሊና ሲሰውር

ራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደ መላእክቱ
የጽጌው ማህሌት የትንሳኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ

## 66. ከካራን ውጡ

ከካራን ውጡ ከነዓን ግቡ
ወደ ጽድቅ ሕይወት ዛሬ ቅረቡ
ካራን ጣኦት ነው የሚመለከው
የአህዛብ ሀገር የሞት መንደር ነው /2/
እንደ አባታችን እንደ አብርሃም
ወገኖች ውጡ ከካራን ዓለም
የግፍ እንጀራ ይብቃችሁና
ከካራን ውጡ በአምላክ ጎዳና
የጣኦት ምስል ከሚሸጥበት
ዓለም በዝሙት ከሚነድበት
ከሰዶም መንደር ከካራን ውጡ
የሃጢያትን ስር ዛሬ ቁረጡ
የሃጢያት ዓለም ዛሬ ይብቃና
የፍቅርን ሕይወት እንልበስና
ከካራን መንደር በፍጥነት ወጥተን
ከነዓን ገብተን ማደር አለብን
ማርና ወተት ከሚፈልቅበት
ሰዎች በፍቅር ከሚኖሩበት
ከሰማያዊት ኢየሩሳሌም
ዛሬ ብንገባ እናገኛለን የአምላክን ሠላም

## 67. ያልጠፋነው

ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው
ቸርነቱ ከቶ አያልቅምና ርህራሄው ከቶ አያልቅምና
ይገባዋል ክብርና ምስጋና
ፈታኝ ሲያንገላታን በባህር ስንሔድ
ማዕበል ተነስቶ ያ የሥጋ ሞገድ
ሕይወት ስትመዝን ልባችን ሲናወጥ
ለጠላት ሳይሰጠን አደረገልን ጸጥ
ስለሆነ ርህሩህ ፈጥኖ የማይቀየም
ለንስሀ እንቅረብ አንሂድ ወደ ዓለም

ምስክር ነን እኛ አይተናል ማዳኑን
በእርሱ ተማርከናል ቀምሰን ቸርነቱን
በበደልነው በደል ማረን እንላለን
ከአንተ ተለይተን ወዴት እንሄዳለን

ዓለም የማያውቀው የማይመረምረው
በውስጣችን አለ እኛ እምናመልከው
ከእንግዲህ አልፈልግም የሸንጋይ ምላስ
ቃልህ ይቆጣጠረኝ በስጋም በነፍስ
አንተ ካከበርከኝ ማን ያዋርደኛል
ዓይኔን ከሰው አንሳው አሁንስ በቅቶኛል

## 68. <u>እያለፈ ነው ዘመኔ</u>

እያለፈ ነው ዘመኔ ትዕዛዙን ሳልፈፅም ወየው ለእኔ /2/
በጠራኝ ጊዜ ምን እላለሁ ና ብሎ ወደ እኔ /2/
    በወጣትነቴ ሳልሰራ እያየሁ አለፈኝ ብዙ አዝመራ /2/
    ከእንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ከአንተ ጋራ /2/
የማስብበት በየዕለቱ ንጹህ ልብ ስጠኝ አቤቱ /2/
ከትዕዛዝህ ውጪ በመሆን እንዳልቀር በከንቱ /2/
    እንደየስራው ለመክፈል በግርማ መንግስቱ ሲመጣ /2/
    ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ /2/
እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ እየተማራችሁ ከቃሉ /2/
ይመጣሉና በእርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ /2/
    ትዕግስትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻው ጠንክሩ/2/
    ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ /2/

## 69. <u>ሰላምሽ ዛሬ ነው</u>

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም
ወደ አንቺ መጥቷልና <u>አምላክ ዘለዓለም</u> /2/
ሆሳዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ህጻናት በኢየሩሳሌም
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የህዝብሽ ብርሃን <u>መጣልን በግርማ</u> /2/
ሆሳዕና እያሉ አመሰገኑት
በኢየሩሳሌም <u>አዕሩግ ህጻናት</u> /2/
ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙለት
መስቀል ተሸከመ <u>ሊሆነን መድሃኒት</u> /2/
የኢየሱስን ህማም ደናግል አይተው
እያለቀሱለት <u>ሄዱ ተከትለው</u> /2/

## 70. ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ በመስቀል ላይ ሆነህ አባት ሆይ
ድምጽህን በማሰማት አባት ሆይ ነፍስህን ሰጠህ አባት ሆይ
የሰማይ ከዋክብት በሙሉ ረገፉ
ጨረቃና ፀሐይ ደምን አጎረፉ
ብርሃናት ጨለሙ ጠፍተው ተለያዩ
ስጋህን በመስቀል ተገልጦ ስላዩ
ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ
አሰምቶ ጮኸ ተጠማሁ እያለ
ማርና ወተት ለሚመግበው
ሐሞት አመጡለት ይቅመሰው ብለው
አካሉ ሲወጋ ውሃ ደም ፈሰሰ
በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ
የእስራኤል ሴቶች ዋይ ዋይ ሲሉልህ
ለእነርሱ አዘንክ እንጂ ለአንተስ አላሰብክ
እናትህ ስታለቅስ በመስቀል ስር ሆና
ዮሐንስን ሰጠህ ጠብቆ እንዲያጽናና
መላዕክትም ታዩ ኢጋንንትም ሸሹ
የአይሁድ ሰራዊት ፈርተው ተረበሹ

71. <u>የጸጸት እሮሮ</u>

አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ /2/
ለብሰህ የማርያምን ስጋ /2/
ባክኖ የነበረው የአዳም ዘር /2/
ውጤቱ ነበር የሚያሰጋ /2/

በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን /2/
ድህነትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ /2/
ምን የበዛ ነበር ትህትና /2/
ትዕግስትህ የማይለወጥ /2/

የአሾህ አክሊል ደፍተህ /2/
በራስህ ጎንህን ሲወጉ በጦር /2/
አንተ ግን ለእነርሱ ከአባትህ /2/
ምህረትን ትለምን ነበር /2/

ግን መቼ አወቁህ እነርሱ /2/
በሃጢያት ደንድኖ ልባቸው /2/
መድሃኒታቸውን ገረፉት ሰቀሉት /2/
አንተም ሞትክላቸው /2/

በዚያች በደብረ ዘይት ቦታ /2/
ደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ /2/
ከቶ ከየት ይሆን እጣዬ /2/
ያን ጊዜ የእኔ አወዳደቅ /2/

የጸጸት እሮሮ በፊትህ /2/
እንዳያቃጥለኝ እኔን /2/
እርዳኝ ፈጣሪዬ እኔን /2/
አድሰው የዛገው ልቤን /2/

ዳግም ስትመጣ ለፍርድ /2
ከዓለም ፍፃሜ በኃላ /2
ኸረ እንዴት እድለኞች ናቸው /2/
በፊትህ የሚያገኙት ተድላ /2/

## 72. <u>እስመ ለዓለም</u>

እስመ ለዓለም ምህረቱ /2/

ኢያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ /2/

አመስግኑ ጌታን ሁላችሁ በአንድነት /2/
መህሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው /2/
ከገሃነም እሳት እኛን ሊያድን ነው

ከማርያም የነሳው ያ ቅዱስ ስጋው
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው
ለፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ለይቶ

## 73. የት ይሆን መግቢያዬ

በስራዬ የት ይሆን መግቢያዬ /4/
ጨነቀኝ ጠበበኝ ነፍሴ ወዲያልኝ /2/

ተሸክሜ የሃጢያት ክምር /2/
ይመሻል ይነጋል በከንቱ ስዞር /2/
ገሰገሰ ቀኑ ጨለመብኝ /2/
ዋ ለነፍሴ ምንም ስንቅ አልያዝኩኝ /2/
በድያለሁ ወደ አንተ እጮሀለሁ /4/
ይቅር በለኝ እማጸንሀለሁ
ችላ አትበለኝ ከፊትህ ቆሜአለሁ
አለፈብኝ በከንቱ ጊዜዬ /2/
እየጓጓሁ ለዚች ለስጋዬ /2/
በንስሀ ሳላጥበው እድፌን /2/
ልትደርስ ነው ያች የፈተና ቀን /2/

## 74. ወደ ምስራቅ እዩ

ወደ ምስራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መውጫ
ድንግልን ከበቧት እንበል ሃሌ ሉያ
ለአምላክ እናት ለአዛኝት
እልል እንበል እንዘምርላት

    ወገኖች ተነሱ እናታችን መጣች
    ስሟን ስንጠራ መቼ ትቀራለች
    የተከዘን ልታጽናና
    ነይ ስንላት ትመጣለችና

የጽጌው ማህሌት መዝሙር ሲጀመር
ማርያም ትመጣለች በደመና በአየር
ንኢ ስንል በሰዓታት
እሷ አትቀርም ትመጣለች በእውነት

    ፍልሰታ ሲጀመር ቃል ኪዳን ገብታለች
    የሌሊት ውዳሴን ንኢን ትሰማለች
    ህፃናቱን በበረከት
    ልትጎበኝ ትመጣለች በእውነት

በፍጹም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
በአማላጅነትሽ ሁኝልን መከታ
እናታችን አለኝታችን
እንድናለን ድንግል አንቺን ይዘን

    ሃሌ ሃሌ ሉያ /4/ እስመ ዝንቱ ኡራኤል
    እስመ ዝንቱ ለዓለም ብርሃን

## 75. አትተወኝ አትጣለኝ

አትተወኝ አትጣለኝ /2/
ወድቂያለሁ እና ጌታ ሆይ አንሳኝ /2/
ቸሩ መድሃኒቴ የአልአዛር ቤት ራት
የኑሮዬ ጣዕም የሕይወቴ መብራት
በሃጢያት ጭቃ ላይ ወድቂያለሁና
ጌታዬ ሆይ አንሳኝ እጅህን ዘርጋና /2/
የሰጠኸኝ ክብር የልጅነት ስልጣን
እንደ ሶምሶን ሲወድቅ ከደሊላ ጋር
እርቃኔን ቀረሁኝ ተላልፌ ሕግህን
አምላኬ ዘርጋልኝ የምህረት እጅህን
ጌታዬ ዘርጋልኝ የምህረት እጅህን
ዘወትር እየበደልኩ ከህግህ እርቄ
በሃጢያት ጭቃ ላይ ክፉኛ ወድቄ
በበደል እስራት ተይዣለሁና
አባቴ ሆይ ማረኝ መሀሪ ነህና
ጌታዬ ሆይ ማረኝ መሀሪ ነህና

## 76. እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘውትር ነፍሴ /2/
ልቤ ተነሣሣ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍፁም ትህትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመብርሃን
የለመለሙች መስከ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግስት ናትና
ክብር ይገባታል ዘውትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኃላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባህር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

## 77. <u>ተክለሐይማኖት ፀሐይ</u>

ተክለሐይማኖት ፀሐይ የኢትዮጵያ ሲሳይ
<u>ምዕራፈ ቅዱሳን</u> /2/ በነፍስም በሥጋ አትርሳን
የቅዱሳን እርስት የኢትዮጵያው ብርሃን
የጸሎት ባለቤት የነዳያን መድህን
ገና ሳትወለድ አምላክ የመረጠህ
የድውያን ህመም <u>ፈዋሹ አንተ ነህ</u> /2/
ገና በሶስት ቀን በህፃንነትህ
ጌታን አወደሰው ቅዱስ አንደበትህ
ቀድሞም እግዚአብሔር አስቦሃልና
በወጣትነትህ <u>ወጣህ ለምነና</u> /2/
ሌትና ቀን ሳትመርጥ ክረምትና በጋ
ስትፀልይ ውለህ ስትፀልይ አነጋህ
በመቆምህ ምክንያት አንድ እግርህ ቢነሳ
ጸሎትህን ፈጸምክ <u>ለስጋህ ሳትሳሳ</u> /2/
ምንኛ ድንቅ ነው ቅዱስ ያንተ ብርታት
ሰባት ዓመት ሙሉ በአንድ እግርህ ጸሎት
የዓለም ግሳንግሱ ሀብቱ ሳይስብህ
ለኢትዮጵያ ፀለይክ <u>ቆመህ በአንድ እግርህ</u> /2/
የሐይማኖት ተክል የኢትዮጵያ አባት
ምህረትን ከአምላክህ ለሀገርህ አሰጣት
እኛንም አግዘን ጽድቅን እንድንሰራ
በተሰጠህ ስልጣን <u>ጠብቀን አደራ</u> /2/

## 78. ያሬድ ካህኑ

ያሬድ ካህኑ ዘመረ /2/

ዘመረ ያሬድ ዘመረ አምላኩን አመሰገነ /2/

አርያም በማለት ያሬድ ዘመረ
ማህሌት ጀመረ ያሬድ ዘመረ
ዜማውን ከመላዕክት እያስተባበረ

ምስጋና አቀረበ ያሬድ ዘመረ
በዜማ መሣሪያ ያሬድ ዘመረ
ጸናጽል አነሳ ከበሮ መቋሚያ

በግዕዝ በዕዝል ያሬድ ዘመረ
በአራራይ ዜማ ያሬድ ዘመረ
ከብሉይ ከሐዲስ ምስጢር እያስማማ

በዜማው ምልክት ያሬድ ዘመረ
የአምላክን መከራ ያሬድ ዘመረ
የመስቀሉን ነገር የማዳኑን ስራ

ደሙ እየፈሰሰ ያሬድ ዘመረ
በጦር ተወግቶ ያሬድ ዘመረ
ሊቁ ማህሌታይ በመንፈስ ተቃኝቶ

በጥኡም ልሳኑ ያሬድ ዘመረ
በተሰጠው ጸጋ ያሬድ ዘመረ
ለንጉስ እግዚአብሔር ለአልፋ ኦሜጋ

ድጓ ጾመ ድጓ ያሬድ ዘመረ
ምዕራፍ መዋሲት ያሬድ ዘመረ
ምስጢር ተገልጾለት ከሰማይ መላዕክት

የዜማ መሠረት ያሬድ ዘመረ
ፈልፈለ ዝማሬ ያሬድ ዘመረ
የኢትዮጵያ ኩራት የተዋህዶ ፍሬ

## 79. እጹብ ድንቅ ነው

እጹብ ድንቅ ነው ውለታው
እግዚአብሔር ለኛ ያረገው
ከቶ አይጥለንም ለዘለዓለም
እንደ አምላካችን ማንም የለም
ወድቀን ነበረ ተነስተናል
ባህር አሻግሮ አቁሞናል
ድንቅ አደረገ ታምር ሰራ
እያንሳፈፈ ያን ተራራ
የጠፋውን በግ የፈለገ
እራሱን ባዶ አደረገ
መስቀል ታቅፎ ክንዱ ዛለ
ምን ያልሆነልን ነገር አለ
ከአባትም በላይ አባት ነው
የልጆቹ እንባ የሚገደው
የጭንቀታችን ተካፋይ
አዛኝ ጌታ ነው ሁሉን ቻይ
ዳግም እንድንቆም በሕይወት
ጨክኖ ወደደን እስከሞት
ከእንግዲህ አንፈራም እንጸናለን
ለክፉ የማይሰጥ አባት አለን

## 80. የስላሴን መንበር

የስላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሃል ሚካኤልን ከፊት
አእላፍ መላዕክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩ ተመልከቱ የሰማዩን ድምቀት
እዩ ተመልከቱ የሰማዩን አባት

የስላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላዕክት
ካህናተ ሰማይ ስሉስ ቅዱስ ሲሉ
በጽድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ /2/

የቅዱሳን ህብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የስላሴን መንበር
ፍቅርና ርህራሄን የተሞላች ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ /3/

## 81. እናመሰግንሃለን

እናመሰግንሃለን /2/
እንደ አባቶቻችን በማህሌት እንጠራሃለን
እንደ ቅዱሳኑ ለክብርህ እንዘምራለን
ለአምላክ ምስጋና ለፈጣሪ ክብር
ማለዳ ተነስተን ምስጋና ስንጀምር
የአባቶች ዝማሬ ቅኔ መወድሱ
ሲሰማ ደስ ይላል ከቤተ መቅደሱ
ስርዓተ ሰማይ በምድር ተሰርቶ
በአባቶች ሎቦና የአምላክ ጥበብ ሞልቶ
ዝማሬ ፈለቀ ከታላቁ መቅደስ
የያሬድ ጸናጽል መሰንቆ በገናው
የጽዮን ደናግል ለመዝሙር ተነሱ
ስሉስ ቅዱስ በሉ ስሙን አወድሱ
ማህሌቱ ሲቆም ሰዓታት መዝሙሩ
ቅዱሳን መላዕክት አብረው ሲዘምሩ
ፍጹም ተደስተች ነፍሳችን በደስታ
ለምስጋና ስንቆም ከቅዱሳን ተርታ

## 82. . <u>ዝም አትበሉ</u>

ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ /2/

<u>ቅዱስ</u> /3/ ስሉስ ቅዱስ በሉ
መላዕክቱ ሁሉ ምስጋናን ጀምሩ
ቅዱስ ቅዱስ በሉ

የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን አንሽው
በምስጋና መዝሙር እስራኤልን ጥሪው
አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ
ከእኛ ጋር ይሆናል <u>የሠራዊት ጌታ</u> /2/

ፍጥረታትም ጨኹ ሰማያት ዘምሩ
ስለ ቅድስናው ውዳሴ ጀምሩ
ዳዊት ሆይ ተነሣ ስለ ጽዮን ዘምር
ከበሮው ይመታ <u>በገናው ይደርደር</u> /2/

ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር
ውለታው ብዙ ነው ለእኛ ያለው ፍቅር
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ
ለጌታ ለእግዚአብሔር <u>ለሠራዊት ጌታ</u> /2/

ባህሩን አቋርጦ ወንዝ ያሻገራችሁ
ተራራውን ንዶ ያቀለለላችሁ
በአውሎ ነፋስ መሐል መንገድ ላለው ጌታ
ለንጉስ ክርስቶስ <u>እንዘምር በእልልታ</u> /2/

## 83. ጠላቴን ጌታዬ

ጠላቴን ጌታዬ አንበረከከልኝ
እጅግ ተዋረደ በጣሙን ደስ አለኝ
ለዚህ ድንቅ ውለታህ ምን ልክፈልህ ጌታ
ስለ ለወጥክልኝ ሀዘኔን በደስታ

እግዚአብሔር ብርሃኔ መድሃኒቴ ነው
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው
አስጨናቂዎቼ በከበቡኝ ጊዜ
ፈጥኖ ደረሰልኝ ሳለሁ በትካዜ /2/

ይቅርታህ በአይኔ በፊቴ ነውና
ሃጢያቴ ቢበዛም አልተውከኝምና
እግዚአብሔር የሕይወቴ መሸሸጊያዬ ነው
በእርሱም ትመካለች እድል ፈንታዋ ነው /2/

ነፍሴን ሀዘን ከቧት እጅጉን ተጨነቃ
ስትጮህ ወደ አንተ ምህረትህን ናፍቃ
እራርተህ ፈወስካት አነሳሃት ጌታ
መቼም አይረሳም የአንተ ውለታ /2/

አጥንቶቼ ደከመው በለቅሶ በዋይታ
አይኔም በሀዘኔ በእንባ ተሞልታ
ልቤ ታውኮብኝ ሰላሜ ደፍርሶ
አዳነኝ ጌታዬ በምህረቱ ዳሶ /2/

## 84. <u>በገና አንስተን</u>

በገና አንስተን መሰንቆን
እናመስግነው ስምህን
እንደ አምላካችን ማንም የለም /2/
ይክበር ይመስገን ለዘለዓለም /2/

ዓለም ሞኝነት ይመስለዋል
ለአንተ መንበርከክ ይከብደዋል
ፍቅርህን ቀምሰን ዝም  አንልም /2/
እንዘምራለን ለዘለዓለም /2/

ሞኝነት ለኔ መች ሆነና
ፊትህ ያቆመኝ ለምስጋና
እንድቀኝልህ ግድ የሚለኝ /2/
ፍቅርህ ብቻ ነው የማረከኝ /2/

ፈውስን ስትሰጠን ስትባርከን
ፍቅርህን ልከህ ስትጎበኘን
ጉልበት ይጸናል ባንተ ጸጋ /2/
ማነው የሚከፍለው የአንተን ዋጋ /2/

## 85. ለማርያም እንዘምራለን

ለማርያም /2/ እንዘምራለን ለዘለዓለም /2/
የተዘጋጅ በር ለዘለዓለም ህዝቅኤል ብሏል ለዘለዓለም
ንጽህይት ናት በእውነት ›› በፍፁም ድንግል ››
አብነት አድርገን ›› እኛም እርሱን ››
በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን /2/
የዋህት እርግብ ለዘለዓለም ሠላም አብሳሪ ለዘለዓለም
ጨለማ ሕይወቴን ›› ብርሃንን አብሪ ››

እማጸንሻለሁ ›› ድንግል ለነፍሴ ››
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ /2/
እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም ያለኝ ፍቅር ለዘለዓለም
አይወሰንም ›› አይነገርም ››
በእርሷ ደስ ይለኛል ›› ሐሴት አደርጋለሁ ››
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ /2/
ንኢ ንኢ ስላት ለዘለዓለም ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም
አትለየኝም ›› ለእኔስ ቅርቤ ናት ››
እጹብ እጹብ ብለው ›› አመሰገኗት ››
ክብርዋን ሊገልጹ ቢያጥራቸው ቃላት /2/

## 86. ወይቤሎሙ ሐሩ

ወይቤሎሙ ሐሩ ወመሐሩ ለዘየአምን /2/
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /4/
በሕይወታችሁ ስበኩ በኑሮአችሁ
ከጽንፍ እስከ ጽንፍ
በዓለም ዙሪያ አዳርሱ ሳትሰለቹ
ደመና ጠቅሳችሁ እንደወፍ
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /2/
በሃጢያት ገመድ ተይዞ ለታሰረው
በዓለም ጽልመት ለተዋጠው
የእውነቱ መንገድ ብርሃኑ ለጠፋበት
በሁለንተናው ፈንጥቁበት
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /2/
የጽድቅ እንጀራ በማጣት ለተራበው
የሕይወትን ውሃ ለተጠማው
ቀቢጸ ተስፋ በልቡ ላደረበት
የወንጌልን ማዕድ አቅርቡለት
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /2/
አይንተ ወንጌል ካህናት ሊቃውንት
ለተልዕኮ የጠራችሁ
ከእውነተኛው ምንጭ ከጌታ ከባህሩ
የሕይወትን ውሃ የጠጣችሁ
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /2/
ሁለንተናችሁ ይነበብ ፊደል ይሁን
በትዕዛዙ ሔዳችሁ
ስራችሁ ይብራ በዓለም እንደ ሻማ

በሕይወታችሁ ሰብካችሁ
ወንጌለ መንግስተ ሰማያት /2/

## 87. **<u>እርግብየ</u>**

<u>እርግብ</u> /2/ ማርያም እሙ ለእግዚእየ
በቀለመ ወርቅ ጻአፊ ስምየ
በአምደ ብርሃን ጻአፊ ስምየ
በቀለመ ወርቅ ጻአፊ ስምየ
የተመረጥሽ ጌጤ ፈርጤ ሽልማቴ
የክብሬ አክሊል ነሽ ለኔ እመቤቴ እርግብየ
ወደ አንቺ እጮሃለሁ በችግሬ ጊዜ
እንድታርቂልኝ የልቤን ትካዜ እርግብየ
የማትፈርሺ መቅደስ ንጽህት አዳራሽ
የመለኮት እሳት በማህጸንሽ የያዝሽ እርግብየ
የድህነቴ ምክንያት የሕይወቴ ፋና
የችግሬ ደራሽ ርህርህተ ህሊና እርግብየ
ስጠራ ስምሽን ከጠዋት እስከ ማታ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ እንዳልንገላታ እርግብየ
የነቢያት ትንቢት የሰማዕታት አክሊል
ምዕረገ ጸሎት የወርቅ መሰላል
ምርኩዝ መደገፊያ የሐይማኖት በትር
ሆነሽ የተገኘሽ የሕይወት ማህደር እርግብየ
መንገዴ ጨልሞ ወድቄ እንዳልቀር
ደግፈሽ አሻግሪኝ ያን የሃጢያት ባህር እርግብየ

## 88. ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መቼ እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙን መድን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአህዛብ ሀገር ስኖር ተሸጬ

ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ
አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሀሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመ አምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህቺ ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባህሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝም
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝም
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝም
አንቺን መውደዴን ኢያስተዉኝም
በአህዛብ መሃል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ

## 89. አንቺን የያዘ ሰው

አንቺን የያዘ ሰው ምን ይጎድልበታል
በምልጃሽ በረከት ቤቱ ሞልቶለታል
ዘር መከር ባይኖረው ጎተራው ባይሞላ
ሁሉም ይሸፈናል በረድኤትሽ ጥላ /2/

በረከትሽ ብዙ የደናግል ገንዘብ
የምስኪናን እናት የርሁባን ቀለብ
ለሁሉ መጋቢ ጸጋሽ የማይጎድል
ስምሽ ጥዑም ምግብ ከረሃብ የሚያስጥል /2/

አንቺ ብትመጪ ከምስኪኗ ቤቴ
እንደ መጥምቁ እናት በዛልኝ ሐሴቴ
የአዲስ ኪዳን ቁርባን መንበር ጠረጴዛ
ጽድቅን አሸተትን የሕይወትሽን መዓዛ /2/

ልቤ ተጠራጥሮ ኪዳንሽን ካልከዳ
ልመናም አልወርድም አልይዝም አኩፋዳ
ሁሉን እየሞላሽ መመገብ ታውቂያለሽ
ቢዝቁት የማያልቅ ጸጋና ሀብት አለሽ /2/

የእግዚአብሔር ማረፊያ ኮሬባዊት ዋሻ
የሕይወት ውሃ ምንጭ የህግ መፍሰሻ
ነበልባል ተዋህዶሽ ሙሴስ አንቺን አይቷል
ጫማውን አውልቆ በፊትሽ ተደፍቷል /2/

## 90. እዘምራለሁ

እዘምራለሁ ለእግዚአብሔር በፍፁም ደስታ
ላዳነኝ አምላክ ላቆመኝ ከሰዎች ተርታ /2/
እንዳለፈ ውሃ መከራዬን ያስረሳኝ እርሱ ነው
በእጆቹ ደግፎ ለምስጋና ያቆመኝ በጸጋው
መጽናናቴ እያልኩ የምጠራው ውለታው ማርኮኝ ነው
ፍቅሩ አስደነቀኝ ምህረቱ ለእኔ ያደረገው
ኃይልህ በድካሜ እንዲገለጥ  ይህን አድርገሃል
ወጀቡን ገስጸህ ማዕበሉን እኔን አድነሃል
በጠላቴ ፊት በዘይቱ ራሴን ቀብቶኛል
ወደቀ ሲሉ ጠላቶቼ ሐይሌን አድሶታል
በሃጢያት ብረክስም በምህረቱ እኔን ጎብኝቶኛል
ፈፅሞ እንዳልጠፋ በመዳፉ በእጆቹ ቀርጾኛል
ተስፋ ያደረግኩት ምንም የለም ጌታ ካንተ በቀር
ወጥመዴን ስበር ሰንሰለቴን የሃጢያቴን ቀንበር
በሁሉ አንተ ጌታ እንደሆንክ አሁን አውቂያለሁ
ሐይልህ በድካሜ ተገለጠ ሁሉን አልፌአለሁ
ይሁን ያልከውን በሕይወቴ ፈፀምክ በፍቅርህ
ዳግመኛ በእጅህ ተሰራሁኝ በበጎ ፈቃድህ

## 91. ሰረገላዎችህ

ሰረገላዎችህ የእሳት ናቸው
የሌጌዎን ጭፍሮች ማይችሏቸው
የገሐነም ደጆች ማይችሏቸው
አንተ ብቻ ቅዱስ ሐያል ጌታ
ሳመልክህ እኖራለሁ ጠዋት ማታ /2/
በእሳት ሰረገላ ታጥሯል መንገዳችን
ግያዝ ሆይ አትፍራ አለ ፈጣሪያችን
የጠላትን ምሽግ በቃሉ ይቆርጣል
ከእኛ ጋራ ያለው ከእነርሱ ይበልጣል

ከቴማን ተራራ ከፋራን ሲወርድ
ጠላት ይጨነቃል በድምጹ ሞገድ
ጦረኛ አያበዛም ሞአብን ሲመታ
በአህያ መንጋጋ ሺውን ጥሏል ጌታ
የጥልቁን መሠረት በነፋስ አስሮታል
ከሰማያት በላይ ዙፋኑን ዘርግቷል
ዘንባባ ይዛችሁ ግቡ ከመቅደሱ
በምስጋናው እሳት እንድትቀደሱ
ወደረኞቻችን ከቁጥር ቢበዙ
እንደ ቃየል ልጆች ሾተል አንመዝም
እንጀራ መግበን እንሰዳቸዋለን
በቀልና ፍርድን ለአምላካችን ትተን

## 92. ዛሬም አለሽ

ዛሬም አለሽ በልቤ /3/
ድንግል ሆይ ውለታሽ አይጠፋም ከሃሳቤ
እንደ ሃጢአቴ ብዛት እንደ በደሌማ
የጥልቁ ሰንሰለት ሲያንሰኝ ነው ጨለማ
ግን ያንቺ ሆንኩና ሁሉንም አለፍኩት
ያንን የሞት ባህር በምልጃሽ ቀዘፍኩት
አርፏል ልቤ ባንቺ ባዛኝቷ ማርያም
ውስጤ እየፈሰሰ ፍቅርና ሠላም
ህመሜን ቢያስረሳኝ የውዳሴሽ ቃና
እመቤቴ እላለሁ ዛሬም እንደ ገና
እናታችን ጽዮን ሰው ሁሉ ይልሻል
ዳዊት በበገና ያመሰግንሻል
የሐሴቦን ነገስታት ለክብርሽ ዘመሩ
የማትፈርሽው መቅደስ የእግዚአብሔር ሀገሩ
እጅግ ብዙ ነገር አድርገሽልኛል
ይቅር ባይም ልጅሽ በፍቅር አይቶኛል
እኔስ እኖራለሁ ድንግል ባንቺ ጥላ
ጨለማን አላይም ከእንግዲህ በኃላ

## 93. ያ ድሃ ተጣራ

ያ ድሃ ተጣራ እግዚአብሔርም ሰማው
ደርሶ ስላንኳኳ ከጸባኦት እንባው
አምላክ በቸርነት በምህረት ጎበኘው
ባለቀሰ ጊዜ ግራ የገባው ሰው

መሻትህ ብቻ ነው የሚፈለግብህ
እግዚአብሔርን ጥራ እመን ትድናለህ /2/
ንገረው ችግርህን የውስጥህን ብሶት
ይሽረዋልና አስፈሪውን ሕይወት
ግራ የተጋባው የተከፋው ገጽህ
ይበራል በጸሎት አምላክህን ጠርተህ
ለወገን ለዘመድ ያስቸገረው መላ
ሲቀል ታየዋለህ ካነባህ በኋላ
ሳግና ንዴትህ ይቀራል ይሻራል
በእርሱ ፈንታ ልብህ ሰላም ይሞላዋል
በከንቱ መጨነቅ እራስን መጥላቱ
ነውና የአጋንንት መግቢያ ምልክቱ
ሀዘን በህሊናህ በፈሰሰ ጊዜ
ንገረው ለአምላክህ የልብህን ትካዜ

## 94. <u>ርሆቦት</u>

ርሆቦት እያልን እንዘምር በእልልታ
ጌታ አብዝቶናል ውሎልናል ውለታ
የዝማሬ ነው የምስጋና ሰዓቱ
የእግዚአብሔር ልጆች ክንዳችሁን አበርቱ
ቃኝተነዋል በገና መሰንቆውን
ላናቋርጥ በፊቱ ምስጋናውን
በዕጣኑ ጢስ ታጅቧል ውዳሴያችን
ይሰማናል ያበዛል አምላካችን
ለአገልግሎት ስንወጣ ጥቂት ነበርን
በረሃውን ስንጓዝ በዛ ዘመን
ለመለምን በፍቅሩ እንደ ዋርካ
ለዚህ ቀን አስቦናል ጌታ ለካ
ሁሉም ሆኗል በጊዜው በፈቃዱ
እንቅፋቱም ተነስቷል ከመንገዱ
ያነሳሳን ያበረታናል ገና
ዓለምን እንከድናለን በምስጋና
ስናመሰግን ውለን እናድራለን
ያለድካም በፊቱ እንቆማለን
እንኳን በምድር በሰማይ በበጉ ፊት
ዝማሪያችን ይሰማል እንደ ዳዊት

## 95. ቸርነትህ ነው

ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከ ዛሬ
ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከ ዛሬ
ላመስግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ /2/
መከሊቱን ቀብሬ ባሳዝንህ
መብራቱንም ይዤ ባልጠብቅህ
በታላቅ ይቅርታህ እንዳትረሳኝ
በፍቅርህ ኀብኝተህ ከሞት አውጣኝ
ከቤትህ እርቄ መች ጠገብኩኝ
በርሃብ በርዛት ተቸገርኩኝ
አምናለሁ አምላኬ እንድትምረኝ
ለይቅርታህ መጣሁ ተቀበለኝ
አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ
ባንተ ቸርነት ግን እመካለሁ
የከበደው ሸክሜ ይቀለኛል
ይቅርታህ ለባሪያህ ይደርሰኛል
በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር
ስራህን ለትውልድ ለመመስከር
እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ
አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ
በሰው እጅ መመካት አቁሚያለሁ
እረዳቴ አንተ ነህ አውቂያለሁ
አንተ ከጠበቅከኝ በሕይወቴ
ቅጥሬ አይደፈርም መድሃኒቴ
የእኔን ስራ ተወው ተግባሬን
የመስቀሉን ነገር መርሳቴን

## 96. ሞገድ ሲገፋኝ

ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ
ማን ያድነዋል ሁሉም ሲሉ
በሰላም አለፍኩ በፀጥታ /2/
ሁሉ ተቻሎ ላንተ ጌታ /2/
በአንተስ ቁስል ተፈወስኩኝ
ጌታ በፍቅርህ ተማረኩኝ

ሞቴን ሽረኸው ባንተ ሞት /2/
ይኸው አቆምከኝ በሕይወት /2/
ደጅ ስጠናህ ስማጸንህ
መቼ ጨከነ ጌታ ልብህ
እንደ ቀራጩ አመሰገንኩ /2/
ምህረት ጸጋህን ከእጅህ ለበስኩ /2/
ዘውትር እልል ብል ብዘምር
ስለገባኝ ነው ያንተ ፍቅር
ጌታ እምጠራው ስምህን /2/
ለውጠኸው ነው ታሪኬን /2/
አይኖቼ አያዩም ካንተ በቀር
የምትወደድ የምትፈቀር
ዘመድ ወገኔ ሆነኸኛል /2/
እኔን የሚችል የት ይገኛል /2/

## 97. ሐረገወይን

ሐረገወይን ነሽ ድንግል
የወልድ እናቱ
ብጽእት ይሉሻል እመአምላክ /2/
አንቺን ትውልድ ሁሉ
ስምሽ ልዩ ነው ለኛ ቤዛዊተ ኩሉ
የያዕቆብ መሰላል የሙሴ በትር
የእሳትን ባህር የምታሻግር
እመ ብዙሃን ናት የተሰጠች ለእኛ
ጥላ ከለላ ናት ከጥፋት መዳኛ /2/
ፍቅርና ሠላም የተገለጠባት
ሐረገ እግዚአብሔር ድንግል እመቤት ናት
የታጠረች ተክል የተዘጋች ደጃፍ
ለድንግል ምስጋና ይድረስ ከአጥናፍ አጥናፍ /2/
እጹብ ድንቅ ነገር ለእኛ ተሰጥቶናል
ሕይወት የምትለምን እናት አግኝተናል
እስከ ቀራንዮ ከጸና ጉዟችን
ድንግል ትገኛለች ያደራ እናታችን /2/

## 98. አስፈሪ ነበልባል

አስፈሪ ነበልባል ሁሉንም አልፌ
ይኸው በአምላኬ ቆምኩኝ ተደግፌ
ምስጋና አቀርባለሁ ሁሉን ቻይ ለሆነው
እንድዘምርለት ልቤን ለከፈተው

ለሰው ያልነገርኩት በውስጤ የቀረ
ያሳለፍኩት ስቃይ መከራ ነበረ
ወደ አንተ አልቅሼ ፈታህልኝ አምላክ
አይተህ ቸል አላልከኝ በባሪያህ አልጨከንክ

አምላክህ የት አለ ሲሉኝ ጠላቶቼ
አጥምደው ይዘውኝ እጃቸው ገብቼ
ሀዘን ነፍሴን ከቧት መድረሻ ጠፍቶኝ
ፈጥነህ ደረስክና ከሞት አዳንከኝ

ከእንግዲህ ወዲህ እኔ ተስፋ አልቆርጥም
ስራህን አይቼ ከቶ አልናወጥም
ወድቄ እንዳልቀር አስተምረኸኛል
ወጥመዱን ሰባብረህ ለዚህ አብቅተኸኛል

## 99. <u>ስምህ በሁሉ ተመሰገነ</u>

ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማወደስ ያስደስተናል
ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል

አምላክ ተመስገን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከህጻናት አፍ ምስጋና ይውጣ /2/
አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ እጣ /2/

በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማህሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም /2/
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም /2/

ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣ
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነትህን እንጠብቃለን /2/
ከአንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን /2/

## 100. ማርያም አርጋለች

ማርያም አርጋለች ወደ ገነት /4/
የሰማይ መላዕክት እያረዳዷት /2/
እሷም እንደ ልጅዋ ተነስታለች /2/
የአባትዋ ዳዊትን ትንቢት ልትፈፅም
ወርቁን ተጎናጽፋ በቀኙ ልትቆም
ወደ አምላክ ማደሪያ ወደ ሰማያት
አረገች በእልልታ ድንግል የእኛ እናት
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
ሰማያት ይከፈት ደመናም ይዘርጋ
ዝምታም አይኖርም እመ አምላክ አርጋ
አንደበት ይከፈት ማርያምን ያመስግን
ከዘለዓለም ጥፋት በምልጃዋ እንድንድን
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
የአምላክ ማደሪያ የ ቅዱስ ስጋሽ
አምላክን ያቀፉት እነዛ እጆችሽ
ሙስና መቃብር ይዞ አላስቀረሽም
ተነስተዋል በክብር በእምነት አየናቸው
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
ሐዋርያት አበው እንኳን ደስ አላችሁ
በክብር አረገች ማርያም ሞገሳችሁ
ወደ ዓለምም ውጡ ስበኗን ይዛችሁ
የድንግል እርገቷን ንገሩ ተግታችሁ
አርጋለች ማርያም ተነስታለች

## 101. ማን አለን

ማን አለን ጌታ ሆይ ካንተ በቀር /2/
በሰማይ ሆነ በዚህ ምድር
ማን  አለን ከአንተ በቀር
ዛሬ ወዳጅ ነገ ጠላት
ይለወጣል የሰው ሕይወት
ያመናቸው ገፍተው ጣሉን
አንተ ብቻ አትለየን
ሕይወታችን መልኩ ወይቦ
መንገዳችን በሾህ ተከቦ
ጠላት በዝቶ ስንሰቃይ
ታገልክልን ነህ ኤልሻዳይ

ባይደላንም የምድር ኑሮ
ብናሰማም ለቅሶና ሮሮ
ባይሳካ ውጥናችን
ባንተ ያምራል ፍጻሜያችን
እንኳን ጮኸን ሳንለምን
አፍሮ አይገባም ባዶ እጃችን
ስቦ ማውጣት እስኪያቅተን
በዓሳ ይመላል መረባችን

## 102. መላዕክቱ

መላዕክቱ በፊቱ ይቆማሉ
ሠራዊቱ በፊቱ ይሰግዳሉ
ሐያል አምላክ እግዚአብሔር እያሉ /2/
በክብረ መንግስቱ በነጭ ዙፋን ላይ
ዘለዓለም ይኖራል ከሰማያት በላይ
ለሚታዘዙለት እጁን ይዘረጋል
ጨለማውን በሰላም ያነጋል
መብረቅ ነጎድጓዱ የምስጋናው ጅረት
ዘወትር ይፈሳል በቀንና ሌሊት
የእሳት መጋረጃው ይነዳል ከፊቱ
ተቀኙለት ሊቀ መላዕክቱ
ትናንትናም ዛሬም እርሱ ህያው ነው
ሞትን አሸንፎ በአባቱ ቀኝ ያለው
ዳግመኛ ሲመጣ እርሱን ለመቀበል
በደመና እንነጠቃለን
በወርቅ ፅና ላይ ብዙ ዕጣን ጨምረው
ዙፋኑን ያጥናሉ በበጉ ፊት ቆመው
አዲሱን ምስጋና አዲሱን ውዳሴ
ያቀርባሉ ለቅድስት ስላሴ

## 103. <u>ገብርኤል</u>

ገብርኤል /2/ ስለው ሰምቶ
መጣ ወደኔ ፈጥኖ
ሰንሰለቴን በጠሰው የአንበሶቹን አፍ ዘግቶ
ገብርኤል ስጋዬ ሳይረግፍ በአናብስቱ ጥፍር
›› ታድጎኛል ምልጃው የመልአኩ ክብር

›› በረሀብ ለነደዱ አናብስት ሲጥሉኝ
›› አንተ አለኸኝና ክንፎችህ ከለሉኝ
ገብርኤል ከአፎቱ ሲመዘዝ የጠላቴ ሰይፍ
›› አጽንቶ ይዞኛል ፍሬዬ ሳይረግፍ
›› አደገድጋለሁ አለኝና ፍቅሩ
›› በእሳት ክንፍ ታጥሯል የደጇ ድንበሩ
ገብርኤል በሰይፍ ተመትርዋል የከፉዎች ክህደት
›› ሐብሉ ተበጥሷል የአመጹ ሰንሰለት
›› ከቅዱሱ ድንጋይ ሕይወት የሚያፈልቀው
›› እንዳልለይ እረዳኝ ክብሬን ከፍ አደረገው
ገብርኤል አለው ልዩ ስልጣን ከአምላክ የተሰጠው
›› ይመጣል ወደ እኛ እሳቱን ሊያጠፋው
›› እኛም እናምናለን ሰምተናል አይተናል
›› የመላዕክት አለቃ ከአምላክ ያማልዳል

## 104. ሌላ ምስጋና

እመቤቴ ሆይ ሀብቴ ነሽና
ሳመሰግንሽ ዲያቢሎስ ቢቀና
ገና አለኝ ገና አዲስ ምስጋና
ገና አለኝ ላንቺ አዲስ ምስጋና
ድልድይ ሆነሽን ተሻግረናል እኛ
አንወሰድም አንሞትም ዳግመኛ
እናት አለችን በላይ በሰማይ
አማላጃችን እሙ ለአዶናይ
ግዮን ከቦታል የርስትሽን ሀገር
ጣፋጭ ተአምርሽ ይኖራል ሲነገር
ዋሻው ያበራል ሜዳው ሳር ቅጠሉ
መለኮሳቱ ንኢ ንኢ ሲሉ
ተፍገመገመ ራደ ጠላታችን
የልጅሽ ሞገስ ሰፍኖ በላያችን
ሞገዱም ይጩህ ዲያቢሎስም ያውራ
ከእሳቱ አንወድቅም ሳለን ካንቺ ጋራ
ቤትሽ አድገናል በአማረው እልፍኝሽ
የንጉሱ እናት እመ ብዙሃን ነሽ
የራማው መላዕክት ክንፎቹን ዘርግቷል
ወደ ገሊላ ምስጋና ተሰምቷል

## 105. <u>አንተ ግን አንተ ነህ</u>

አንተ ግን አንተ ነህ በፀባኦት ያለህ
ዘለዓለም የምትኖር ሁሉን አሳልፈህ
የሁሉ ባለቤት አንተ ግን አንተ ነህ
ደመናት ባይኖሩ ዝናብም ባይሰጡ
ጨረቃና ፀሐይ ብርሃን ባያወጡ
የፍጥረታት ፀባይ ሁሉም ቢቀያየር
አንተ ግን አንተ ነህ ህያው እግዚአብሔር
የምድር ሐያላን ትላንት የነበሩ
በጉልበት በስልጣን እጅግ የተፈሩ
ቦታውን ለቀዋል በጊዜአቸው አልፈው
አንተ ግን አንተ ነህ መንግስትህ ህያው ነው
ሁሉን ስትለውጥ የማትለወጥ
እንደየስራው የእጁን የምትሰጥ
ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ስምህ
ቀናት የመይቆጥሩት አንተ ብቻ ነህ
አመድ ሲሆኑ አየን የግሪክ አማልክት
በወርቅ እና በብር በእጅ የተሰሩት
ዘመን የማይሽርህ እንዲህ እነደዋዛ
አንተ ግን አንተ ነህ ፈጥረህ የምትገዛ

## 106. ሊረዳኝ መጣ

ሊረዳኝ መጣ ሃያል ሚካኤል
ይጠብቀኛል ሃያል ቅዱስ ሚካኤል
የሙሴ ጠባቂ ሃያል ሚካኤል
መንገድ የመራኸው ሃያል ቅዱስ ሚካኤል
የኤርትራን ባህር ሃያል ሚካኤል
ከፍለህ ያሻገርከው ሃያል ቅዱስ ሚካኤል
ክብርህ ከመላዕክት ሃያል ሚካኤል
ከፍ ከፍ ያለ ነው ሃያል ቅዱስ ሚካኤል
ታላቁ አለቃ ሃያል ሚካኤል
ከቶ እንዳንተ ማነው ሃያል ሚካኤል
በሃጢያት በረሃ ሃያል ሚካኤል
መጠለያ ሁነን ሃያል ቅዱስ ሚካኤል
ጠላት በመንገድ ላይ ሃያል ሚካኤል
እንዳያስፈራራን ሃያል ቅዱስ ሚካኤል

## 107. <u>ሃጢያቴ በዛ</u>

ሃጢያቴ በዛ እመቤቴ
ምህረት ላኪልኝ ለሕይወቴ
የፈጣሪ እናት አዛኝት /2/
ባንቺ ነው ማግኘት የጽድቅ ሕይወት /2/
ከሲኦል አውጪኝ አዛኝት
የጻድቃን ውበት እመቤት
ሠላማዊ እናት ሀገረ እግዚአብሔር /2/
ባንቺ ነው መውጣት ከሃጢያት ቀንበር /2/
የሚሰግዱልሽ ጻድቃን ሰማዕታት
የሚላኩልሽ ቅዱሳን መላዕክት
ከእነርሱ ጋር ነይ እመቤቴ /2/
እንዲታረቀኝ ሰማያዊ አባቴ /2/
አስታርቂኝ እኔን ከልጅሽ
እማልላለሁ ከፊትሽ
ስምሽን ጠርቶ ያፈረ ማነው /2/
የአዳም ተስፋ ስራሽ ድንቅ ነው /2/
የፍቅር እናት እመቤታችን
አማልጅን እኛን ከጌታችን
ዘወትር ነይልኝ እናቴ ማርያም /2/
ላንቺ ቅርብ ነው መድሃኒዓለም /2/

## 108. <u>ምስጉን ነው</u>

ምስጉን ነው የተመሰገነ
ባሪያውን እኔን ይቅር ያለ
ይመስገን ይመስገንልኝ
ጎጆዬን አምላክ ሞላልኝ

እጅህ ሰፊ እንደሆነ አውቃለሁ ጌታዬ
የጎደለው ሞልቷል ይድረስ ምስጋናዬ
የጣሁትን ከአንተ አገኝቻለሁ
ሁሉን ነገር ለበጎ ብያለሁ

ማቄን የቀደደው ደስታ አስታጠቀኝ
ባዶ የነበርኩት ሁሉ ተሰጠኝ
ሰጭም ነሺም እግዚአብሔር ብቻ ነው
የሰው ድርሻ በር ማንኳኳት ነው

እገፋለሁ እንጂ እኔ አልጨነቅም
መሰረቴ አንተ ነህ ከቶ አልናወጥም
ስትሰጠኝ የሚታየውን
እንዳትነሳኝ የዘለዓለሙን

ቢሰጥ አያልቅበት ለጋስ ክቡር ጌታ
ሁሉን ከወነልኝ በልዩ ችሮታ
ድሆች ስንሆን ሁሉ አለንና
አምላካችን ይድረሰው ምስጋና

## 109. <u>ገና እንዘምራለን</u>

ገና እንዘምራለን /4/
አንደ መላዕክቱ ብርሃንን ለብሰህ
ገና እንዘምራለን

ወላዲት አምላክን ከፊት አስቀድመን
በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን
ለስላሴ ክብር ገና እንዘምራለን
ገና እንዘምራለን

በምስጋና ስራ ከሰለጠኑት ጋር
ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን
ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና
ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና
ገና እንዘምራለን

በትንቢት ሳይሆን በታላቅ ትህትና
በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና
ስራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና
ገና እንዘምራለን

ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም
ሜልኮል በዝማሬው ብትስቅበትም
አምላክ ከወደደ እንዲያመሰግነው
በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ምን ነው
ገና እንዘምራለን

## 110. አቤቱ እንዳንተ ማን ነው

አቤቱ እንዳንተ ማነው
በፍቅርህ ቤቴን ባረከው

እንደሳምራዊው ዘይቱን አፍስሶ
አዳነኝ ጌታ ምህረቱን አስታውሶ
መገፋቴን አይተህ ለእኔ ራራህልኝ
ስድቤን አስወግደህ ሞገስን ሰጠኸኝ
ጥንት እንደሰማሁህ አየሁህ በአይኖቼ
እቀኝልሃለሁ መቅደስህ ገብቼ /3/
ከመሰዊያው ስፍራ ብርቅም ከቤትህ
መጣህ ልትፈልገኝ ይገርማል ምህረትህ
ወዴት ነው ያለኸው ብለህ ጠርተሸኛል
ግሩም ነህ አምላኬ ማዳንህ ይደንቃል /3/
ዓይንህ አይታኛለች ከላይ ከሰማያት
ነፍሴን ታድገሃል የድሃ አደግ አባት
ከፊት እየወጣህ መንገዴን መራኸኝ
ጨለማዬ በርቷል አምላክ ስለሆንከኝ /3/
የሕይወቴ መዝገብ ሲገለጥ መፅሐፉ
ቀርጾኝ አይቻለሁ እኔን በመዳፉ
ምስክሩ እኔ ነኝ ፈጽሞ አላፍርበት
ያደረገልኝን የውዴን ቸርነት /3/

## 111. ዘንዶውን አሸንፏል

ሚካኤል ስለው ስሙን ስጠራ
የአምላኬ ብርሃን በላዬ በራ
አዛኝ ነው በእውነት ፍጹም አዛኝ
የሚጠብቀኝ የሚያጽናናኝ /2/
ከአለቆች ጋራ ህዝቡን የመራ
የሚመላለስ በእሳት ተራራ
ባህሩም ሸሸ ከማደሪያው
የጌታ መላዕክ ሲያናውጸው
ዘንዶውን አሸንፏል ስሙን በክብር ጽፏል /2/
ከባዱ ጋራ ሜዳ ሆኖኛል
የወህኒው መዝጊያ ተከፍቶልኛል
አልናወጥም ከቶም አልፈራ
የጌታ መላዕክ ነው ከእኔ ጋራ
ዘንዶውን አሸንፏል ስሙን በክብር ጽፏል /2/
ትዕቢተኛውን አሸንፎታል
ዲያብሎስ አሁን ዝናሩን ፈቷል
ታላቅ ጸጥታ በሠማይ ሆነ

እግዚአብሔር ብቻ ስሙ ገነነ
ዘንዶውን አሸንፏል ስሙን በክብር ጽፏል /2/
ሚካኤል ሲቆም ፈጥኖ ደራሹ
የሚቃወሙን አጥብቀው ሸሹ
ታላቁ መላዕክ ከፊት ቀደመ
ታሪክ ተሰራ እንባችን ቆመ
ዘንዶውን አሸንፏል ስሙን በክብር ጽፏል /2/

## 112. <u>አንቺ የወይን ሐረግ</u>

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ /2/
<u>ምግብ ሆኖ</u> /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ /2/
ባንቺ ሰማይነት ድንግል የወጣ ፀሐይ /2/
<u>ብርሃን ነው</u> /2/ ለጻድቃን ስሙም አዶናይ /2/
ፊደል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ /2/
<u>ለመላዕክት</u> /2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ /2/
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ መገኛ /2/
በስጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለእኛ/2/

## 113. <u>ባለውለታዬ</u>

<u>ባለውለታዬ</u> /2/ ከአመድ ያነሳኸኝ
ከትቢያ ተጥዬ ተመስገን ጌታዬ
በሩን ቢዘጋብኝ ስምኦን ጨክኖ
ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ
እንድቀርብ ወደ እርሱ አዘዘ ጌታዬ
እግሩን አጥበዋለሁ ወድቄ በእንባዬ /2/
የቀራጭ አለቃ ቢሆንም ስራዬ
እንድወርድ ከዛፉ አዘዘ ጌታዬ
ማዕረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ
ቤቴ ተባረከ በኢየሱስ ክርስቶስ /2/
ድንጋይ የጨበጡ ፈራጆች ከበውኝ
ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ
ፈረደችባቸው ሃጢያትም በእነርሱ
በሰላም ሂጅ ብሎ ምሮኛል ንጉሱ /2/
የማምነውን አምላክ አውቀዋለሁ እኔ
በሰራልኝ ስራ በእድሜ በዘመኔ

ፍቅሩን ተሸክሚል የልቤ ትከሻ
ልለየው አልችልም እስከመጨሻ /2/

## 114. ድንግል በድንግልና

ድንግል በድንግልና ጸንሳ
በድንግልና ትወልዳለች
ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች
ገና ሳይጸነስ ዘመኑ ሳይገባ
ገረድ መሆን ሻተች ትንቢቱን አንብባ
ልታያት ናፈቀች ያችን ቅድስት እናት
ለክብርዋ ተገዝታ ውሃ ልትቀዳለት
ባርያ ልሁን አለች ዝቅ አድርጋ ራሷን
መች አወቀችና እናቱ መሆኗን
ጥቂት ለሚሻ ሰው ያውቃል ብዙ መስጠት
በማህጸኗ መቅደስ ሲቀድስ ኖረበት
ሀር ወርቁን ስትፈትል በቤተ መቅደሱ
ማደርያው እንድትሆን መረጣት ንጉሱ
በህሊናው ተስላ የነበረች ምናብ
መሰላል ሆነችው ለአዳም ድህነት ርካብ
በጎ መዓዛዋን ውበቷን ወደደ
በማህፀኗ ሊያድር እግዚአብሔር ወረደ
ከኪሩቤል ይልቅ ጀርባዋ ተመቸው
ንጽህይት ናትና የማትቆረቁረው
የተዘጋጀ መቅደስ ከቶ እማትከፈት
ታትማ የኖረች የክብሩ ሰገነት
ማንም አይከፍታትም ጥበብ አላትና
የእስራኤል ቅዱስ ገብቶባታልና
በረቀቀ ጥበብ ድንግል ተደነቀች
በሆዷ ቅዳሴን እያስተናገደች
ጎንበስ አለች ማርያም ውዳሴ ልትሰማ
ከቅኔያት ሀገር ከሆዷ ከተማ

## 115. <u>ድንግል ፈጣሪዋን</u>

ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው
በመጠቅለያም ጠቀለለችው
የለምና ስፍራ ለእንግዶች ማረፊያ
ግርግም አስተኛችው በከብቶች ማደሪያ

ጨነቃት ጠበባት የዳዊት ከተማ
የጌታ መወለድ ታምሩ ሲሰማ
ወረደ መልአኩ ምስራች ሊያወራ
የህጻኑም ክብር በምድር አበራ

ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ከቶ ማይነገር /2/
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር /2/

ሰባ ሰገል መጡ ከሩቅ ምስራቅ ሀገር
ወርቅ እጣን ከርቤውን ለእርሱ ለመገበር
በእናቱም እቅፍ አገኙት ህጻኑን
ለዓለም ተናገሩ ንጉስ መወለዱን

ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ከቶ ማይነገር /2/
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር /2/

የይሁዳ ምድር ምስጋና ተመላች
ንጉስ መጥቷልና ከናዝሬት ገሊላ
ታምሩን ትናገር ቤቴልሔም ታውራ
ዝማሬ ሲውጣት ተረስቶ ቆጠራ

ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ከቶ ማይነገር /2/
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር /2/

የማይታይ ታየ ተዳሰሰ እንደ ሰው
በጠባቡ ደረት አዳምን መሰለው
ገረማት ጥበቡ ታናሿን ሙሽራ
ተዋህዷልና ቃል ከስጋ ጋራ

ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ከቶ ማይነገር /2/
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር /2/

## 116. በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና
በምድርም ለሰው ልጅ ሰላም /2/
ተወልዷልና መድሃኒዓለም /2/
የሞቱ ዘመን ማብቂያው ሲቃረብ
መቋጫው ሲደርስ አስፈሪው ወጀብ
ከድንግል ማርያም ጌታ ተወለደ
የጠብ ግድግዳ በክንዱ ተናደ
ሰላም ታወጀ ነፃነት ሕይወት
ተወልዷልን የዓለም መድሃኒት

የሰማይ ዜማ ተሰማ በምድር
ባአፈ መላዕክት ለእግዚአብሔር
ቃሉን አልረሳም የምህረት ኪዳኑን
የማዳኑን ቃል ከአፉ የወጣውን
መሐላው ጽኑ ጸጸት የሌለበት
ላዳነን አምላክ እልል እንበልለት
አጽናኙን ድምጹን ሰማን በኤፍራታ
በዱር አየነው የፍጥረትን ጌታ
በሚቆምበር በሚያድርበት ስፍራ
እንሰግዳለን በጽዮን ተራራ

## 117. እሰይ ተወለደ

እሰይ ተወለደ የዓለም መድሃኒት /3/
ይኸው ተወለደ የዓለም መድሃኒት /3/
በሶሪያ ታየ ፈጣሪ እንደ እንግዳ /3/
ብስራተ ልደቱን ለሁሉ ሲያስረዳ /3/
ትንቢት ተናገሩ ነብያቱ ሁሉ /3/
የእስራኤል ንጉስ ተወልዷል እያሉ /3/
ሰባ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ /3/
አምላክ ቀዳማዊ ተወልዷል እያሉ /3/
ሰባሰገል መጡ ይዘው እጅ መንሻ /3/
ወርቅ እጣን ከርቤውን ለማርያም እጅ መንሻ /3/
ህጻናት አደሩ ከልደቱ ቤት /3/
ውሃው ሆኗልና ማርና ወተት /3/

## 118. ሆሣዕና በሉ

ሆሳዕና በአርያም ሆሳዕና
ሆሳዕና ብለን እናቅርብ ምስጋና
ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና
ለወልደ ዳዊት ››
ትህትናን ያሣየን ››
ስሙ ይባረክ ››
ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና
ለሰማይ ንጉስ ››

ግርማን ለብሶ መጣ ››
እኛን ሊቀድስ ››
ሆሣዕና በሉ ሆሣዕና
ለአምላክ ምህረት ››
ተወልዶ ከድንግል ››
እንደ ሕጻናት ››
እረኞች በዋሻ ሆሣዕና
የሰገዱለት ››
የአዳም ልጆች ሁሉ ››
ደግሞም መላዕክት ››

## 119. <u>በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ</u>

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ /2/
የተባረከ ነው ቅዱስ /2/
ሠላምን የሚያውጅልን
ፍቅር አንድነትን የሚያጸናልን
እውነተኛ መካር የሆነ
ለህዝቦች ሠላም የቆመ
ከሞአብ ምድር የሚያወጣን
ከጠላት ወጥመድ የተቤዠን
የሕይወት እንጀራ የሆነው
በእግዚአብሔር ስም የመጣው
ለኢየሩሳሌም የሚያነባ
ቤተ መቅደስን የሚያጸና
ለተገፉት ሁሉ መጠጊያቸው
የመጽናናት አባት አለኝታቸው
አዕምሮን የሚያልፍ ሰላም ያለው
በጥዑም ቃሉ የሚያጽናናው
ነፍሴም እርሱን ወዳ ዘመረች
ሆሣዕና በአርያም እያለች

## 120. ምድረ ቀራንዮ

ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጎለጎታ /2/
መድሃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ
የዓለም መድሃኒት በአንቺ ተንገላታ

መስከሪ አንቺ ምድር ጉኡዚቷ ስፍራ /2/
መድሃኒት ክርስቶስ ያየብሽ መከራ /2/

የእሾህ አክሊል ጉንጉን ደፍቶ በራሱ ላይ /2/
ደሙ እነደ ውሃ ሲፈስ በመስቀሉ ላይ /2/

እጅና እግሮቹ በችንካር ተመተው /2/
ይቅርታን አድርጎ ለዚያ ለሃጢያታቸው /2/
ሁሉን ማድረግ ሲችል ስልጣን ሲኖረው /2/
በቀራንዮ መስቀል ፍቅሩን ገለጸው /2/

መከራ በተራ ሲፈራረቁበት /2/
በደልም አልሰራም ምንም አይነት ስህተት /2/
ከሰማያት ወርዶ እንዲህ መዋረዱ /2/
የእኛን በደል ሃጢያት ክርስቶስ መወሰዱ /2/

ፀሐይ ከለከለች ለመስጠት ብርሃን /2/
ለመሸፈን ብላ የአምላኳን እርቃን /2/
በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ እያለ /2/
ተገርፎ ተሰቅሎ ቀራንዮ ዋለ /2/

በቆረስከው ስጋ ባፈሰስከው ደም /2/
አቤቱ ተራዳን እስከ ዘለዓለም /2/
ቸሩ መድሃኒዓለም እባክህ ማረን /2/
ደካሞች ነንና ወድቀን እንዳንቀር
ደካሞች ነንና ጠፍተን እንዳንቀር

## 121. <u>ወንበዴ ነበርኩኝ</u>

ወንበዴ ነበርኩኝ ሀገር ያሰለቸው
በመስቀል ላይ ሆኖ ታሪኬን ለወጠው
አስበኝ ስላልኩት በኋላ ስትመጣ
ገነትን ለማየት የመጀመሪያ ሰው ሆንኩኝ ባለ ዕጣ

አቤት ፍቅሩ <u>የእግዚአብሔር</u> /2/
ግሩም ፍቅሩ <u>የእግዚአብሔር</u> /2/
ኃያል ፍቅሩ <u>የእግዚአብሔር</u> /2/

አስበኝ ስላልኩት አሰበኝ ጌታዬ
ወንበዴ ነበርኩኝ ስርቆት ነው ስራዬ
በመስቀል ላይ ሆኖ ህዝቡን ያስብ ነበር
<u>እኔስ አላየሁም</u> /2/ እንዲህ ያለ ፍቅር

አልታይም ብዬ ሃጢያትን ስሰራ
ተመለስ ይለኛል ስሜን እየጠራ

እንዳልሞትበት ነው በሃጢያት ታስሬ
<u>ፍቅሩን አልዘልቀውም</u> /2/ እንደዚህ ዘርዝሬ

መከራ ሲከበኝ መጥቶ ያጽናናኛል
በሀዘኔ ጊዜ እግዚአብሔርም ያዝናል
ዓይኑ ከእኔ አይርቅም ጥበቃው አይጠፋም
<u>ስሙን እጠራለሁ</u> /2/ በጌታዬ አላፍርም

## 122. ተወልዳለችና

ተወልዳለችና የጌታ እናት መድሃኒት /2/
እናመስግናት እናወድሳት እንውደዳት /2/
የአዳምን ሕይወት
 አዳም ሲሰደድ ከጥንት ርስቱ
 ፊቱን ሸፈነው ጭንቀት ፍርሃቱ
 እያለቀሰ ገነትን ሲያጣ
 ተስፋ አንቺ ሆንሽው የመዳኑ ዕጣ
ሊባኖስ ተራራ ተሰማ ዜና
ምስራቅ ወለዱ እያቄም ወሐና
ዳግማዊት ሔዋን ምክንያት ድህነት
ልደቷን ሰማን በቅድስት እለት
 የልደትሽ ቀን ልደታችን ነው
 በአንቺ ነውና ልጅ የተባልነው
 ፉሪን የተባልሽ ቅድስት ተራራ
 በአንቺ መወለድ ዓለሙ በራ

## 123. ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመስግኑ /2/

የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ /2/

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ምስጋና ይገባል ከምንም በፊት
ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ
ምስጋና ይገባል ከጧት እስከ ማታ

ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑህ
መላዕክት በሰማይ የሚዘምሩልህ
እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን
በሰማይ በምድር እንጠረሃለን

ብራብ በስላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ
ስላሴ አምባዬ ክብሬም ናቸውና
ሁሌም ይመሩኛል በሕይወት ጎዳና

## 124. ምስጋናዬን

ምስጋናዬን ለአምላኬ አቀርባለሁ
በማደሪያው ገብቼ እሰግድለታለሁ
ኤልሻዳይ ነው ጌታ  ሁሉን ቻይ
ይፈጸማል አምናለሁ የልቤ ጉዳይ
ዘንባባዬን ይዤ እንደ ህጻንቱ
ሆሣዕና ልበለው ሰግጄ በፊቱ
ምንም ባዶ ብሆን እውቀት ቢጎድለኝ
ለስሙ ልዘምር ከልካይም የለኝ /2/
አምላኬ በፊትህ ቃል አለብኝ እኔ
ቋንቋዬ  መዝሙር ነው ያንተ እንደ መሆኔ
በአሚናዳብ ደጃፍ በቅድመ ታቦቱ
ያ የክብርህ ኡደት ጠራኝ ማህሌቱ /2/
የሕይወት ትርጉሜ አንተ ነህ ደስታዬ
ስምህን ማገልገል ክብሬ ነው ስራዬ
ለታመነው ጌታ ምስክር የሆኑ
ከብረው ተመለሱ ለበረከት ሆኑ /2/
መነሻዬ አንተ ነህ ጉልበቴና ክብሬ
መድረሻዬም አንተ መደምደሚያ ቅጥሬ
በጽዮን ተራራ ስትገለጥ ያኔ
ነጩን ልብስ አልብሰህ አስለሳኝ ለቅኔ /2/

## 125. ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና

ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና /2/
እግዚአብሔር ይመስገን /2/
ምህረቱ አይኖቼን ከእንባ ከሀዘን ታድጓል
›› በዘመኔ ሁሉ መጽናናት ሆኖኛል
›› ከቁጥርም በዝቷል ከአዕምሮም በላይ ነው
›› ዘመን የማይሽረው ዘለዓለማዊ ነው
ምህረቱ ከነገስታት ማዕድ ዕድል ፈንታ ስጠኝ
›› ከተረሳሁበት እኔን አስታወሰኝ
›› ትንሽዋን ጸሎቴን ከትጋት ቆጥሮልኝ
›› ከሰላሙ መንደር ከነዓን አገባኝ
ምህረቱ ይታደጋል ከሞት ከጥልቅ ለተጣሉ
›› ምስራች ይሆናል በሞት ጥላ ላሉ
›› የሃጢያትን ክምር ከላያችን ንዶ
›› ደስታን ያለብሰናል ማቃችን ቀዶ
ምህረቱ ለጠላት ዘለፋ እኛን መቼ ተወን
›› በደልን ደምስሶ ልጆቹ አደረገን
›› እስከ ሽበት ድረስ አስከ ሽምግልና
›› በዘመኔ ሁሉ ይረዳኛል ገና

## 126. አብ ወወልድ

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስን /2/
አመሰግናለሁ በየዘመን /2/
አንድ ጌታ አንድ አምላክ አንድ አገዛዝ ስልጣን
ከዚህ በቀር ሌላ ምንም አይጨመር
ሦስትነታቸውን በስም በአካል በግብር
ከነዚህ በስተቀር ምንም አይጨመር
በሰማያት ያሉ እልፍ አእላፋት
መናብርት ስልጣናት ሃያላት ሊቃናት
ያመሰግናሉ እያሉ በፍቅር
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር
አመሰግናለሁ የተቻለኝን
እኔም እንደነርሱ ባልመጣጠን
አመድና ትቢያ ስሆን አከበረኝ
ስምህን ለመጥራት ይኸው አበቃኸኝ
ይኸው በዚህ ሰዓት በፊትህ ቆሚያለሁ
በመቅደስህ ዙሪያ ስምህን እጠራለሁ
መንበረ ጸባኦት ትድረስ ምስጋናዬ
ያመሰገንኩትም ትቅረብ በጌታዬ

## 127. <u>እመብርሃን</u>

ትምክህቴ መድሃኒቴ አንቺው ነሽ /2/
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን
ሽክም የከበደኝ ደካማ ነኝ እኔ
እረዳትም የለኝ ካንቺ በቀር ለእኔ

አመ አምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን
የሃጢያትን ቋጥኝ በጀርባዬ አዝዬ
እቅበዘበዛለሁ ተገፎ ጸጋዬ
በአንቺ እማጸናለሁ ነፍሴን በእጅሽ ጥዬ
ምርኩዝ መሰላሌ ጥላ ከለላዬ
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን
ልዩነሽ እናቴ ማርያም ድንግል
ማን አዛኝ እንዳንቺ ግራ ቀኝ ቢባል
በአንቺ ላይ አረፈ ልቤ ተረጋጋ
የሕይወቴ ተስፋ በአንቺ ተዘረጋ
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን
ፈጽሞ አርቂልኝ የእኔን ክፉ ሽታ
በሽቱሽ መዓዛ አድይኝ እርካታ
የኪሩቤል አክናፍ የነፍሴ ዋስትና
ነይ ነይ እመቤቴ ምርኩዜ ነሽና
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን
ከፍቅርሽ ምስጋና ዝም እንዳልል ድንግል
አንደበቴን ፍችው ህሊናዬም ይቁሰል
የፍቅርሽ ማዕበል ይፍሰስ በሕይወቴ
በእቅፍሽ አድርጊኝ እንደ ልጅነቴ
<u>እመብርሃን</u> /4/ ምርኩዛችን

## 128. ሞት ነው ርሃብ

ሞት ነው ርሃብ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ /2/
ኃይሉ በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ጸጋው በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ከአንተ ርቀው ሸሽተው እየሄዱ
ጠፋባቸው የጽድቅ መንገዱ
ለስጋዊ ጥበብ ሲፈልጉ
በመታለል ስንቶቹ አንተን አጡ
በተዋህዶ የከበርከው ጌታ
መድሃኒዓለም ሆንከልን መከታ
ስነደክም ሞኞት ሲፈትነን
ሃይልን ሰጥተህ በእጆችህ አዳንከን
የዓለም ሰይፍ በእኛ ላይ ተስሏል
ስጋችንን ሊቆርጠው አድብቷል

ሃይልን ስጠን እንድናሸንፈው
ጸጋህ ለእኛ የዕምነት ጋሻችን ነው
ሐዋርያት ጸጋ በዝቶላቸው
ስለ ፍቅር ፈሰሰ ደማቸው
ዛሬም ለእኛ ጸጋህን አብዛልን
እንዳንደክም ፈተና ሲገጥመን
ጋሻ ሆነህ እንድትመክትልን
ቸር አምላክ ሆይ ወደ አንተ እንጮሃለን
ቢገጥመንም ችግር ወይ መከራ
አትለየን ጌታ ከእኛ ጋራ

## 129. ይለመነናል

ይለመነናል አምላክ አብርሃም
　　ይታደገናል መድሃኒዓለም
　　ለፍጥረታት ሁሉ እጁን የዘረጋ /2/
　　ቸር እረኛ ነው አልፋና ኦሜጋ /2/
አብርሃም ይስሐቅን ያዕቆብን አስበህ
የማልክላቸውን ቃል ኪዳን አስታውሰህ
ደካማ ለሆነው ስጋ ሰልጥኖብን
አትመልስ ጌታ የምህረት ዓይንህን
　　ከሰማየ ሰማይ ይድረስ ጩኸታችን /2/
　　እንዘን እናልቅስ ስለበደላችን /2/
ባይመለከተን አምላክ አብርሃም
በምህረት ዓይኖቹ መድሃኒዓለም
ባይዘረጋልን አምላክ አብርሃም
የፍቅር እጆቹ መድሃኒዓለም
　　ሕዝበ እስራኤል ሁሉ ለአምላክ ዘምሩ /2/
　　አድኖናልና በሚያስደንቅ ፍቅሩ /2/
ምንም እንኳን ክህደት ቅጥፈት ቢበረታ
ስለ አብርሃም ብለህ አልተውከንም ጌታ
ለቅዱሳን ያለህ ቃል ኪዳን ሲጸና
ቀስተ ደመናህን አይተነዋልና
　　የእስራኤል አምላክ የማታንቀላፋ /2/
　　በፍደቅርህ ታደገን በሞት ሳንጠፋ /2/
ቃል ኪዳኑ ግሩም አምላክ አብርሃም
ምህረቱ የበዛ መድሃኒዓለም
ርስት ጉልታችን አምላክ አብርሃም
የህይወታችን ቤዛ መድሃኒዓለም

ሳይጸየፍ ጌታ ያደፈ ሃጢያቴን /2/
ከማጥ ውስጥ አወጣኝ ታደጋት ሕይወቴን /2/

## 130. ባለጸጋ እመቤት

ባለጸጋ እመቤት ባለጸጋ እናት
አፍሰናል ከደጅሽ ብዙ በረከት
ወጀቡን ቀዝፈናል ብለን ማርያም
እንዘምራለን እስከ ዘለዓለም

ሰው በሌለበት ከተማ ሞት በከበበው ጨለማ
ሞገስ ገንዘቤ ዘመዴ በምልጃሽ ቀንቷል መንገዴ
ፋና ሆነሽኝ መብራቴ በክብርሽ ደምቆልኝ ቤቴ
ሐሴት አረኩኝ ደስታ ያዘነው ገጼ ተፈታ

እንደኔ ሃጢአት በደል ይገባኝ ነበር መስቀል
ጽኑ ኪዳኗ ጋረደኝ እምባ ጸሎቷ ታደገኝ
እስኪ ልናገር ስራዋን የምህረት እናት መሆኗን
ጽዮን እጆቿን ዘርግታ አስታርቃኛለች ከጌታ

የክብር ሰንደቅ አርማዬ ወደ መቅደሱ መግቢያዬ
አንቺን ይዤአለሁ ጠባቃ የሞቴ ታሪክ አበቃ
እልል እላለሁ ከልቤ ልቅሶዬ ሰምሮ ሃሳቤ
ድንግል ፍቅር ናት ሰላም ለክብሯ ይስገድ ዓለም

የእልፍኜ ማማር ውበቴ ትሩፋቴ ነሽ ሙላቴ
ስምሽ መቀነት ሆኖኛል የዛለው ክንዴ በርትቷል
ባማረው ቤትሽ አድጌ በልጅሽ ፀጋ በልጽጌ
በእናትነትሽ በረከት ይኸው ቆሜያለሁ በሕይወት

## 131. <u>መንግስተ ሥላሴ</u>

አማን አማን /2/

መንግስተ ሥላሴ ዘለዓለም /2/

ንግበር ሰብዓ ብለው አማን በአማን
አዳምን ፈጥረውት አማን በአማን
በቸርነትና በፍቅር ጎበኙት
ሁሉን በእጁ አርገው ሁሉን አስገዙለት

የፍቅር የደስታ አማን በአማን
የበረከት አባት አማን በአማን
መንግስቱ ዘለዓለም ህልፈት የሌለበት
በአፈ መላዕክት የሚመሰገኑት

የዛን የደግ አባት አማን በአማን
የአብርሃምን ቤት አማን በአማን
እንደባረኩለት የእኛንም ባርኩልን
የቤታችን ዋልታ መሰረት ሁኑልን

በመከራ ጊዜ አማን በአማን
ከጭንቅ የሚያወጣ አማን በአማን
ስምህን ሳመሰግን ትረካለች ነፍሴ
የነሙሴ አባት የአብርሃሙ ስላሴ

## 132. <u>እንድናለን</u>

እንድናለን እኛስ እንድናለን /2/
እንድናለን ድንግል እንቺን ይዘን
በፍጹም ቸርነት እንድናለን
ስለ ወደደን ››
እንዳንጠፋበት ››
ድንግልን ሰጠን ››
የልባችን ደስታ እንድናለን
እኛስ አግኝተናል ››
በአማላጅነቷ ››
ፈጣሪ ምሮናል ››
ምርኩዝ እንቺን ይዘን እንድናለን
ስንቃችን ሰንቀን ››
በድንግል መሪነት ››
ጽድቅን እንወርሳለን ››
የምታማልደን እንድናለን
ድንግልን ሰጥቶናል ››
የእሳቱን ባህር ››
በእርሷ ተሻግረናል ››
የልባችን ደስታ እንድናለን
እኛስ አግኝተናል ››
በአማላጅነቷ ››
ፈጣሪ ምሮናል ››

## 133. አ ሥሉስ ቅዱስ

አ ሥሉስ ቅዱስ ተመስገን /2/
ዓለማትን የፈጠርከ እግዚአብሔር ተመስገን /2/

አዳም ሳይፈጠር በዙፋንህ ነበርክ
በአንድነት ሦስትነት እየተመሰገንክ
መላዕክትን ፈጠርከ ስምህን ሊጠሩ
በምስጋና ጸንተው ካነተ ጋር ሊኖሩ /2/
የሰውን ልጅ ፈጠርከ ክብርህን እንዲወርስ
አንተን በማመስገን ሕይወቱ እንዲቀደስ
እኛም ልንጠራህ ባይገባን እንኳን
ለምስጋና ቆመን ደጅህን አንኳኳን /2/
የዓለም ሁሉ ንጉስ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ
ፍጥረትን በሙሉ አውሎ አሳዳሪ
ስላሴን ላወድስ ስሉስ ቅዱስ ልበል
በዓለም ከመክበር በቤታችሁ ልጣል /2/
ዮርዳኖስን ልሁን ሥላሴን ልያቸው
በአንድነት ሦስትነት ቅዱስ ልበላቸው
ትባረክ ትቀደስ ነፍሴ በስላሴ
በአባቶቼ አምላክ በአብርሃም  በሙሴ /2/

## 134. <u>ገብረሕይወት</u>

<u>ገብረሕይወት</u> /3/ ከኢቲሳ መጣ ሊባርካት
ኢትዮጵያ መጣ ሊጠለልባት
ገብረሕይወት በዝቋላ ገዳም ገብረሕይወት መቶ ዓመት ጸለየ
›› አባታችን ለእኛ ›› ጌታን ተማጸነ
›› በባህር ውስጥ ጠልቀህ ›› ማርልኝ ብለሃል
›› ለኢትዮጵያውያን ›› ምህረት ለምነሃል
ገብረሕይወት አንበሳና ነብር ገብረሕይወት ይከታተሉሃል
›› በጸጋህ ተማርከው ›› ለአንተ ተገዝተዋል
›› የቅዱሳን እራስ ›› ገብረ መንፈስ ቅዱስ
›› ቃል ኪዳን ተሰጠህ ›› ምድረ ከብድ ስትደርስ
ገብረሕይወትየእናት ጡት ሳትቀምስ ገብረሕይወት የኖርከ በበርሃ
›› ልብስህ ጸጉር ብቻ ›› ግሩም የአምላክ ስራ
›› እንማፀናለን ›› ሁላችን በአንድነት
›› ጸሎትህ እንዲያወጣን ›› ከሃጢያት ከመቅሰፍት

## 135. መጠጊያዬ

መጠጊያዬ ክብሬ ትምክህቴ
ማረፊያዬ የዘላለም ቤቴ
እናቴ ነሽ ዋሴ ለሕይወቴ

በዓለም ፍቅር ተስቤ ስማረክ
ከጽድቅ ተለይቼ ብቻዬን ስለጉድ
ፍጻሜዬ ሁሉ ላያምር
ለማይጠቅመኝ ነገር እንዲሁ ስኖር
ሽቶ መዓዛዬ በአንቺ ነው የሚያምር
የልቤን ታውቂያለሽ ያሰብኩትን
ምኞቴን በሙሉ በነብስ ያለምኩትን
በልቤ ውስጥ ይድረስ በረከትሽ
ባንቺ ተመክቼ እንዳልጠፋ ልጅሽ
በብርሃነ መስቀል ልዳሰስ በእጅሽ
ወደ እርሱ ለመቅረብ ተስኖኛል
ሃጢያቴ ድጥ ሆኖ ዘወትር ይጥለኛል
እስከ መቼ ድረስ ከእርሱ ልለይ
መድሃኒት ከሌላ ከየትም አላገኝ
ድንግል ንጽህናሽ ለእኔ ሆኖ ይገኝ
እናቴ ርህሩህ ነሽ እጅግ አዛኝ
በአማላጅነትሽ በኪዳንሽ ልዳኝ
በዛች በፍርድ ሰዓት ፈጣሪዬ
ከእኔ ራቂ እንዳይል አዝኖብኝ ጌታዬ
ድጋፍ አንቺ ሁኚኝ መከታዬ

## 136. ያዕቆብ ከቤርሳቤት

ያዕቆብ ከቤርሳቤት ወደ ካራን ሲሄድ
የለውም ነበረ አማካሪ ዘመድ
ፀሐይ ጠልቃ ነበር ከዛ እንደ ደረሰ
ከእርሱም በታች ድንጋይ ተንተራሰ
ህልምንም ዓለመ ታላቁን ራዕይ
መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ
ሲወጡ ሲወርዱ መላዕክት በእርሱ ላይ
እግዚአብሔርም ቆሞ ከላይ ከጫፉ ላይ
የአባቶችህ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ
ይህን ምድር ለርስትህ እሰጥሃለሁኝ
ዘርህ እንደ አሸዋ በምድር ይበዛል
በአራቱም ማዕዘን ህዝብህም ይዘራል
አበው በምሳሌ እንደተናገሩት
ከምድር እስከ ሰማይ አምላክ የዘረጋው
በላይዋ ተቀምጦ በግልፅ የታየባት
የያዕቆብ መሰላል እመቤታችን ናት
ሰማይና ምድር የሚታረቁባት
ወልደ እገዋለ እምያው የተወለደባት

መላዕክት ከሰማይ በአንድ የዘመሩባት
ታካቋ መሰላል እመቤታችን ናት

## 137. ስላሴ ዘከሃ

ስላሴ ዘከሃ ስላሴ ዘዝየ /2/
ሁልጊዜ እለዋለሁ አምላኬ አምላኬየ
ዓይኔን ወደ ተራራው አነሳለሁና
እረዳቴ የኔ ስላሴ ነውና
አምባ መጠጊያዬ እኔ በአንተ አላፍርም
የማዳንህ ስራ ዛሬም ቢዘገይም
የጠላት ፍላጻን ሰብሮ ታድጎኛል
ማን እንደ ስላሴ እረዳት ሆኖኛል
ወዶኛል አዳነኝ እግዚአብሔር ክፍሌ ነው
ቀብቶኛልና እኔ አመልከዋለው
እረኛዬ እግዚአብሔር እኔን ቀብቶኛል
በለመለመ መስክ ሁሌ ያሰማራኛል
ከነጣቂ ተኩላ ይኸው ሰውሮኛል
ለማመስገን በቃሁ እርሱ ፈቅዶልኝ
አንተ ለእኔ ጌታ መሸሸጊያዬ ነህ
ከጣርም ከጭንቀትም ትጠብቀኛለህ
እንዲታደጋችሁ ስላሴን ፈልጉት
ስሙንም በአንድነት ከፍ ከፍ አድርጉት

## 138. <u>አወድሰኝ ኤፍሬም</u>

አወድሰኝ ኤፍሬም ብላ ጠየቀችው ድንግል እናታችን
ባርከኒ ብሎ ወገቡን ታጠቀ ኤፍሬም አባታችን
የልጇ በረከት ይደርብህ ብላው ጀመረ ምስጋና
ወደ ብርሃን ድንኳን ወደ ተከበረው ደረሰው ገባና

ልቡ ያዘነ አዳምን ሊያድን ጌታ ወደደ
ዳግማዊት ሰማይ ማደሪያው ልትሆን እርሱ ፈቀደ
የሰማይ ምስጢር በማህጸንሽ ተከናወነ
ከዘሩ ቀርተሽ በንጽህናሽ የሰው ዘር ዳነ

ሰዓሊለነ /2/

አዕምሮውን ልቡን ሳይብን አሳድሪብን
ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሳን ለምኝልን
በሔዋን ምክንያት በለስዋን በልተን ገነት ቢዘጋ
በአንቺ አማላጅነት ደግሞ ተዛመድን ከአምላካችን ጋር

ትውልድ ሁሉ በክብር አመሰገነ
የሲኦል ቀንበር በላያችን ላይ ስላልተጫነ

ሰዓሊለነ /2/

ሙሴ በሲና ሳትቃጠይ ያየሽ ሐመልማል
እግዚአብሔር መርጦሽ በማህፀንሽ ዙፋኑን ተክሏል
የዲያቢሎስን ጥበብ እንዲያፈርስ አምላክ ሰው ሆነ
በልጅሽ መሞት መዳናችንም ተከናወነ

ሰዓሊለነ /2/

## 139. እነሆ አዲስ ሰማይ

እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ /2/
ፊተኛው አልፎ በዚያ እኖራለሁ /2/
የተሸከመችው መኖሪያ ቤቴ
ያጌጠችው ድንኳን መከበሪያ ሀብቴ
እግዚአብሔር ለልጁ ለእኔ ያዘጋጃት
አዲሲቱ ሰማይ ኢየሩሳሌም ናት /2/
ዓለም ሳይፈጠር ጌታ ያሰናዳት
ማርና ወተት ያልተቋረጠባት
የጎደለ ነገር እንከን የሌለባት
የዘላለም ቤቴ ኢየሩሳሌም ናት /2/
ምንም አልጨነቅ ለሚቀረው ነገር
ልክ እንደ ትላንቱ ነገንም ለማይኖር
ሁሉም ከንቱ ሲሆን ከፀሐይ በታች
የእግዚአብሔር ክንድ ግን ሁሌም የሚመች /2/
አስራ ሁለት ደጆች የተሰሩላት
የሐዋርያት ስሞች የተጻፉባት
መቅደሷ በጉ ነው ሁሉን የሚገዛ
የዘለዓለም ንጉስ ምህረቱን ያበዛ /2/

## 140. ሰዓሊ ለነ ቅድስት

ሰዓሊለነ ቅድስት እንልሻለን /2/
እንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን
ለምኝልን እመቤታችን /2/
ተስፋ አንቺ ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከ ዘለዓለም

ሃጢያታቸው ተደምስሶላቸው
በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው /2/
ስምሽም ስልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃል ኪዳን ገባልሽ ልጆችሽን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ /2/
ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትደክም ሲከባት ሃጢያት
መንገድ ጠፍቶን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን /2/
የልባችን ሀዘን እጅግ ከብዶብናል
ከበለሱ በታች በፍርሃት ወድቀናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደ ዘመድሽ
ደስ አሰኝን ይሰማን ድምፅሽ /2/

## 141. ፍቅሩን ለገለጸው

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለጸው
ምን ስጦታ አለን ለእርሱ የምንከፍለው
ምስጋና ነውና ከእኛ የሚፈልገው
ቸር አምላካችንን ተመስገን እንበለው
ዓለም እስኪደነቅ ድንቅ አድርጎልናል
እንዲሁ ያለዋጋ ጸጋውን ሰጥቶናል
ትናንት ለእስራኤል ሞገስ የሆናቸው
ስሙን እናመስግን ዛሬም ከእኛ ጋር ነው
አፋችን ይሞላ በታላቅ ምስጋና
ከሃጢያቱ ባህር ተሻግረናልና
ክቡር ምስጉን አምላክ ቅዱስ እንበለው
ኢሳይያስም በክብር በራዕይ እንዳየው
ከቶ ለእግዚአብሔር ምን ይከፈለዋል
ሁሉም የራሱ ነው ማን ምን ይሰጠዋል
አመስጋኝ ቢቀኝም ክብር ለራሱ ነው
እርሱ በባህሪው ዘለዓለም ምስጉን ነው
ሙሴም ዝም አላለ ዳዊትም አልተኛ
በጎቹ ዘመሩ ለመልካሙ እረኛ
ያሬድ ተመሰጠ ወደ ሰማይ ዓለም
እኛም ከእርሱ ጋር እንዘምር ዘለዓለም

## 142. የሐይማኖት ፍሬ

ተነግሮ የማያልቅ ነው ጸጋህ /2/
በጸሎት የተጋህ የሐይማኖት ፍሬ
ተክለሃይማኖት የዕምነቱ ገበሬ
በወንጌል ብርሃን ህዝብህን የመራህ
የሃጢያትን ባህር ከፍለህ ያሻገርከ
ኢትዮጵያዊው ሙሴ በመስቀልህ ባርከን
ፍሬ እንድናፈራ ንፁህ ዘር አድርገን
ሐዲስ ሐዋርያ አባ ተክለሃይማኖት
ወንጌልን ያስተማርከን ለክርስቶስ መንግስት
ጸበልህ እንዲምረን ውረድ አባታችን
በዕጣንህ መዓዛ ይፈወስ ደዌያችን
ለማጠን የበቃህ የስላሴን መንበር
ሰይጣን ከቶ የማይደርስ በሄድክበት ሀገር
ለህሙማን ሁሉ የሆንካቸው ፈውስ
ጠብቀን ተክልዬ በስጋም በነፍስ
በጣሙን የበዛ ትሩፋት ምግባርህ
ጸሎትህን ያልተውከ ቢቆረጥ አንድ እግርህ
ምዕራፈ ቅዱሳን የወንጌል ገበሬ
እኛንም አድነን ከዚህ ዓለም አውሬ

## 143. <u>አልፈርድም እኔ</u>

አልፈርድም እኔ በማንም በደል በማንም ሃጢያት
በፈረድኩበት እንዳልመዘን ጌተ ሲመጣ በሃይል በስልጣን
በቸርነቱ አምላክ ባይተወው በደሌን ሁሉ
ውስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ህግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰው እፈርዳለሁ ዓይኔን አቅንቼ
በደሌ በዝቶ ለራሴ ሳላውቅ ለሃጢያት ሞቼ
ይልቅ የአንዱን ሸክም ሌላው ሰው አዝሎ መዳዝ ይችላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰው አይድን ሁሉም በድሏል
ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አህዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ
ክርስትያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኝችን በጸብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስትያን ሆነን በአህዛብ መሃል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀሉን ዓላማ ትተን
መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን

በጽድቅ ስራ ላይ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጅ
ማን ነው የሾመን በወንድሞች ላይ አርጎ ፈራጅ

## 144. እንደ ኤልሣቤጥ

እንደ ኤልሳቤጥ ላመስግንሽ
ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት የእኛ አማላጅ
አዛኝ ነሽ ከልብ ፍጹም የዋህት
እርህራሄሽ ያስደስተኛል
ስለ ሃጢያቴ ምልጃሽ ይቀድማል
የሰላምታሽ ድምፅ ደስ ያሰኘኛል
ከትካዜዬም ያሳርፈኛል
ድምጽሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል
ሀዘኔ ቀርቶ ፊቴ ይፈካል
በእናትነት አንቺን ለሰጠኝ
ቸሩ አምላካችን ይክበር ይመስገን
የሁሉ እመቤት የሁሉ አጽናኝ
የአበው መድሃኒት ከአምላክ አገናኝ
ዛሬም በልቤ ደስት ጨምረሽ
እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ
ከሴቶች መካከል መርጦ ቀድሶሻል
ትውልድ ሁሉ ብጽኢት ይልሻል
በልዩ ውዳሴ ያመሰግኑሻል
ድንግል እናታችን በቀኙ ቆመሻል
የሰላምታሽን ድምፅ ልቤ ሲሰማ
ነፍሴ ደስ አላት ቀለለ ሸክሟ
ድንግል ለክብርሽ ስንበረከክ
እጅሽ ይዘርጋ ለመባረክ

145. **እስከ መቼ ነው**

እስከ መቼ ነው የማልለወጠው
ባልተሰበረ ልብ የምመላለሰው /2/
በሰጠኸኝ ጸጋ ድካሜ ተከድኖ
ዓለም ይከበኛል አልቆና አግኖ
ይህን ከንቱ ወጥመድ ጣለው ከኋላዬ
ትንሽ ሰው መሆኔን ይወቅ ህሊናዬ
ፀሐይ ስትጨልም ከዋክብት ሲረግፉ
ለገናናው ክብርህ ፈቅደው ሲሸነፉ

ለሁለት ሲከፈል ድንጋያማው ዓለት
የእኔ ልብ መቼ ይሆን የሚሸነፍለት
ቃልህን ስሰማ ልቤን ይነካዋል
ጽድቅን አስባለሁ ሀዘን ይሰማኛል
ወዲያው ተመልሼ ሁሉን እረሳለሁ
ለዚህ ዓለም ስብከት ልቤን እከፍታለሁ
መኖርን እሻለሁ ልቤ ተለውጦ
አንተን እንዲያከብርህ ከሁሉ አብልጦ
ዓለት አይሁን ይቅር ይሰበር ከፊትህ
ደንግጬ እነድመለስ ሲገስጸኝ ድምፅህ

## 146. ስራው ድንቅ ነው

እግዚአብሔር ስራው ድንቅ ነው /2/
ለእኔ ያደረገው ብዙ ነው /2/
እግዚአብሔር ስራው ድንቅ ነው /2/
ለእኔ ያረገልኝ ብዙ ነው /2/

እረዳቴ እርሱ ነው ከሰማያት
እግዚአብሔር ጠባቂ ለእኔ ሕይወት
ብርሃኑን በፊቴ የሚያበራ
አምላኬ ድንቅ ነው የእርሱ ስራ

በመንገዴ ሁሉ የሚመራኝ
ስነሳም ስወድቅም የሚያስበኝ
ማንም አልመጣልኝ ከወገኔ
ከሁሉም ይበልጣል እርሱ ለእኔ

የዕዳዬን ደብዳቤ ውድቅ አድርጎ
ሕይወቴን መራልኝ ወደ በጎ
ኸረ እንደ እግዚአብሔር ማን ይሆናል
እርሱን ለሚፈሩት ይታመናል

አንድ ቀን አስቤ ተጨንቄ
ለመኖር አልቻልኩም ተጠንቅቄ
ሁሉን ነገር ለእርሱ ትቼዋለሁ
በምህረቱ ጥላ እኖራለሁ

## 147. <u>በረከትህ ይደር</u>

<u>በረከትህ ይደር</u> /2/ በሁላችን
የዝማሬ ጸጋህ ዳዊት አባታችን
ምስጋና እንድንሰዋ እኛም ለአምላካችን

በገና የያዙበት እጆቹ ጠንክረው
ጎልያድን ጣሉት ጠጠርን ወርውረው
ከበሮ የመታበት ክንዶቹ በርትተው
አንበሳን ገድለዋል ግልገል ከአፉ ነጥቀው
ክፉ መንፈስ ከሰው የሚያስወግደው
የሳኦልን ህመም የሚፈውሰው
የበገና ምስጢር የዝማሬ ቃና
በእኛም ይደርብን ልጆችህ ነንና

<u>እልል</u> /2/ በሉ እንድታሸንፉ
ድምጽንም አሰሙ ቅጽሩን እንድታልፉ
የመዝሙር ነጎድጓድ ወህኒውን ይከፍታል
ብርሃናዊው መላዕክ ከሰማይ ይመጣል

## 148. ከንቱ ነኝ

ከንቱ ነኝ የከንቱ ከንቱ ነኝ
ዋስትና መከታ እግዚአብሔር ካልሆነኝ
ተስፋዬ የሚሆነኝ ሕይወት የሚሰጠኝ
እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያስተማምነኝ
አምላኬ ብቻ ነው የሚያስተማምነኝ
እኔ ንጉስ ነበርኩ በክብር ያጌጥኩኝ
ሁሉን በምድር ላይ በጥበብ ፈፀምኩኝ
የዚህ ዓለም ደስታ ምንም አላዋጣኝ
በመጨረሻ ግን በሞት ተወሰድኩኝ /2/
ከጸሐይቱ በታች አዲስ ነገር የለም
ሰዎች ይደክማሉ እስከ ዘለዓለም
ጥበብን ፍለጋ ደክሜ ነበረ
ሁሉም ከንቱ ሆኖ በመቃብር ቀረ /2/
ከእኔ አስቀድመው የከበሩ ሁሉ
አፈር ተጭኗቸው ከመቃብር አሉ
እብደትና እውቀት ሁሉን አወቅኳቸው
ምንም ቋሚ የለም ሁሉም ከንቱ ናቸው /2/
ልቤን የሰጠሁት ተስፋ ያደረኩት
አልጨበጥ ብሎኝ አለሁኝ ስታክት
የጥበብም ብዛት ለትካዜ ሰጠኝ
እኔ በዚህ ዓለም እጅግ ጎስቋላ ነኝ /2/
ልቤንም ፈተንኩት በደስታ ብዛት
የዚህን ዓለም ለውጥ ጣዕሙን አቀመስኩት

ሳቅም በልቤ ውስጥ ይፍለቀለቅ ነበር
ሁሉም ከንቱ ሆኖ ገብቶ ከመቃብር /2/

## 149. <u>ደስ ይበለን</u>

ደስ ይበለን <u>እልል በሉ</u> /2/
አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ /2/
በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ /2/
ምን ቢተባበሩ <u>ምቀኞች ቢጥሩ</u> /2/
ቅዱስ መስቀሉንም ሸሽገው <u>ቢሰውሩ</u> /2/
አልቻሉም ሊያጠፉት ምን ቢተባበሩ /2/
በተራራ ተሰውሮ <u>ለዘመናት</u> /2/
ተጥሎ በተንኮል ተደብቆ <u>ከኖረበት</u> /2/
ተገለጠ እነሆ በደመና እሳት /2/
ኢሌኒ ናት ይህን መስቀል <u>ያስገኘችው</u> /2/
ደመራን በጥበብ በቦታው <u>ያስቆመችው</u> /2/
የተንኮልን ተራራ ያስቆፈረችው /2/
ታሪካዊ የክርስቶስ <u>ህያው መስቀል</u> /2/
ይኸው ተገለጸ በክብር <u>በግሩም ኃይል</u> /2/
ምንጊዜም ሲያበራ እንዲህ ይኖራል /2/

150. <u>ገሊላ እትዊ</u>

እመቤቴ እስከ መቼ ባዕድ ሀገር ትኖሪያለሽ /2/
<u>ገሊላ ግቢ</u> /4/ ሀገርሽ ገሊላ ግቢ /2/
<u>ገሊላ ግቢ</u> /4/ ሀገርኪ ገሊላ እትዊ /2/

እመቤቴ ማርያም ገሊላ እትዊ ስደቱ ይበቃሻል ገሊላ እትዊ
ሔሮድስ ምቷል ብሎ » ገብርኤል ነግሮሻል »
በእሳት ሰረገላ » ዑራኤል ይመራሻል »

የዝናቡ ጌታ ገሊላ እትዊ እናት ሆነሽ ሳለ ገሊላእትዊ
ሰይጣን በሰው አድሮ » እያስከለከለ »
ውሃ ጥም ጸንቶብሽ » አፍሽ ደርቆ ዋለ »

ይበቃል እናቴ ገሊላ እትዊ ርሃብ ጥማትሽ ገሊላ እትዊ
ሒጂ ወደ ገሊላ » ወደ ዘመዶችሽ »

የሰማዕታት አክሊል » የጻድቃን እናት »
ባርከሽ ሰጠሻቸው » መከራ ስደት »
እኛም ይታደለን » የአንቺው በረከት »

ገጽሽ ብሩህ መልካም ገሊላ እትዊ ልክ እንደ ፀሐይገሊላእትዊ
እግዝትነ ማርያም » እሙ ለአዶናይ »
አይገባም ለአንቺ » መከራ ስቃይ »

## 151. <u>ተስፋችን ነህ አንተ</u>

ተስፋችን ነህ አንተ እስከ ዘለዓለም /2/
የድንግል ማርያም ልጅ <u>መድሃኒዓለም</u> /2/
ደምህን አፍስሰህ <u>ስጋህን ቆርሰህ</u> /2/
ብሉ ጠጡ ብለህ <u>ለዓለም ሰጠህ</u> /2/
የዘለዓለም ሕይወት እንድናገኝ ሆነ /2/
በመድሃኒዓለም <u>ሁሉም ተከወነ</u> /2/
ደሙን የረጨኸው ቅዱስ ዑራኤል /2/
ኢትዮጵያን ቅረባት ትሁን ባለሚል /2/
በደሙ ተባርካ በዑራኤል እጅ /2/
ዛሬም ከእርሷ ጋር ነው ሆኗት አማላጅ /2/
ጸሎትህ ኢትዮጵያን እጅግ ቀደሣት /2/
ሃያሉ ዑራኤል <u>መቼም አይተዋት</u> /2/
የሰው ልጅ ችግር ከሚያስወግድ መላክ /2/
አንዱ ዑራኤል ነው ምድራችንን ይባርክ /2/
ይመስገን ቸር አምላክ
<u>አሜን</u> /2/ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ /2/
ሰላምን ለግሣት ለኢትዮጵያ /2/

## 152. ምስጋና ነው ስራዬ

ምስጋና ነው ስራዬ በዘመኔ በእድሜዬ
ለዋለልኝ ውለታ ምን ልከፈለው ለጌታ
ትላንትና ጥልቁ ነበረ መኖሪያዬ
የማዳኑ ቀኑ ደረሰ የጌታዬ
እራቁቴን ሸፍኖልኛል በብርሃኑ
ምግቤ ሆኗል ስሙን ማወደስ በየቀኑ

አልተራብኩም አልተጠማሁም በዘመኔ
ምግበ ስጋ ምግበ ነፍስ ነው ጌታ ለእኔ
ተበጥሷል የእሳቱ ገመድ ሰንሰለት
አልረሳውም የእርሱን ውለታ ብድራት
ማን ያፈቅራል እስከ ሞት ድረስ ዋጋ ከፍሎ
ማን ያድናል ባለስልጣኑን ሞትን ገድሎ
አማኑኤል በፍቅሩ ጸዳል ምድርን ከድኖ
ስው አድርጎኛል የማይሆኑትን ሁሉ ሆኖ
እንዴት ብዬ ፍቅሩን ልግለጸው እንዴት ብዬ
ስለ እጆቹ በእንባ ጨቀየ መኝታዬ
በእርሱ ቁስል ነፍሴ ወጥታለች ከመከራ
በዝማሬ ስሙን ማክበር ነው የእኔ ስራ

153. <u>አበባየሆሽ</u>

እሰይ <u>ደስ ደስ ይበላችሁ</u> /2/
ቅዱስ ዩሐንስ መጣላችሁ
ደስ ደስ ይበላችሁ

ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን /2/
ጌታ አለ ብለን
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን /2/
ድንግል አለች ብለን

አበባየሆሽ ቅድስት /2/
ባልንጀሮቼ ››
ቁሙ በተራ ››
በጎ ምግባርን ››
በዕምነት እንስራ ››
ዛሬ ነው ቀኑ ››
መመለሻችን ››
ይቅር እንዲለን ››
ቸሩ አምላካችን ››

አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ አበራ /2/

ድንግል ማርያምን ቅድስት
እንለምናት ››
ምህረት የሚሰጥ ››
ቃል ኪዳን አላት ››
ጭንቀት ይርቃል ››
ይቀርባል ሰላም ››

ስሟ ሲጠራ ››
የድንግል ማርያም ››

አደይ የብርሃን ጮራ በኢትዮጵያ አበራ /2/

በህገ ልቦና ጥንቱን
ፈጣሪን አውቀሽ ››
ህገ ነብያትን ከዓለም
ቀድመሽ ተቀበልሽ ››
በብሉይ ኪዳን ለጌታ
መስዋዕት አቀረብሽ ››
ተስፋ ካረጉት ከአይሁድ
ህገ ወንጌልን በፊት
ይዘሽ ተገኘሽ በፊት

ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ ትልቅ ጸጋ አለሽ /2/

## 154. <u>የዓለምን በደል</u>

የዓለም በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክት ትቶ
ጽድቅን ለመፈፀም በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
የሰማያት ሰማይ የማይችለው ንጉስ
ተወለደ ተጠመቀ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
ባህር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደ ተናገረ ዳዊት በትንቢቱ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ

## 155. ወደ ማደሪያው

ወደ ማደሪያው ገብቼ ልስገድ ለእግዚአብሔር
ምስጋናን ላቅርብ ስለ ስሙ ክብር
አድርጎልኛልና አመሰግነዋለሁ
በአፀደ መቅደሱም እሰግድለታለሁ
ከፊቱ ለመቆም ማልጄ እነሳለሁ /2/
በመከራዬ ቀን ሆኖኛል መከታ
ቤቱም ተገኝቼ በፍጹም ደስታ
የከንፈርን ፍሬ ልሰዋ በእልልታ /2/
አስር አውታር ባለው በበገና
በመላዕክቱ ፊት ለማቅረብ ምስጋና
የአፌንም ነገር ሰምተኸኛልና /2/
ለስሙ ልንበርከክ ለእርሱ እንደሚገባ
ስዕለትን ልፈጽም ላቅርብለት መባ
ወደ አደባባዩ በምስጋና ልግባ /2/
አሸበሽባለሁ ድምፄን አሰምቼ
በቤተመቅደሱ ሌሊት ተገኝቼ
እንደ ካህናቱ እጆቼን ዘርግቼ /2/

## 156. ሐመልማላዊት

ሐመልማላዊት እጽ ሐመልማላዊት /2/
ሙሴ ዘሪያ ዘደብረሲና /2/
ማርያም ተወለደች /2/
የለመለመች እጽ የለመለመች /2/
ሙሴ ያያት በደብረሲና /2/
ማርያም ተወለደች ዛሬ /2/

## 157. አ ሚካኤል

አ ሚካኤል /2/ ሊቀ መላዕክት
በሃጢያት እንዳንወድቅ እንዳንሞት
ፈጥነህ ተራዳን አጽናን በዕምነት
ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል ለእስራኤል ሚካኤል
ጠባቂያቸው ነህ ›› መላከ ኃይል ››

ፍቅር አድለን ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት /2/
ነጸብራቃዊ ሚካኤል ተከህኖ ልብስህ ሚካኤል
ሐመልማለ ወርቅ ›› ዓይኑ ዘርግብ ››
ፍቅርን አድለን ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት /2/
በስዕልህ ፊት ሚካኤል እሰግዳለሁ ሚካኤል
ፈጥነህ አረጋጋኝ ›› አለሁ በለኝ ››
ፍቅርን አድለኝ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት /2/

## 158. መመኪያዬ ርስቴ

መመኪያዬ ርስቴ የሆነች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴ ነች
እናቴ ነች /3/

ስማጸናት ትመጣለች እናቴ ነች
ወዳጄ ሆይ ትለኛለች ››
መድሃኒቴ ስለሆነች ››
የድህነት ምክንያት ነች ››

የመስቀል ስር ስጦታዬ እናቴ ነች
እመቤቴ ከለላዬ ››
ወልደ አምላክ ምህረት ይዛ ››
መጣችልኝ የእኔ ቤዛ ››

በጌታ ቀኝ የምትቆመው እናቴ ነች
ላመናት የምትቀርበው ››
ንጽህት ቅድስት የሆነች ››
የዓለም ንግስት እናቴ ነች ››

ድንግል ማርያም መመኪያዬ እናቴ ነች
አክሊሌ ነች አለኝታዬ ››
መንግስተ ሠማይ መግቢያዬ ››
የምቀርበው ከጌታዬ ››
ባንቺ እኮ ነው እመቤቴ ››

## 159. <u>እሠይ እልል በሉ</u>

እሠይ እልል በሉ ተገኘ መስቀሉ /2/

| | | | |
|---|---|---|---|
| የጥል ግድግዳ | አበባ | የፈረሰበት | አበባ |
| ሰው ከእግዚአብሔር ጋር | ›› | የታረቀበት | ›› |
| የእግዚአብሔር ልጅ | ›› | የነገሰበት | ›› |
| የሞት አበጋዝ | ›› | የወደቀበት | ›› |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አይሁድ በቅናት | አበባ | መስቀሉን ቀብረው | አበባ |
| ቢከድኑት እንኳን | ›› | በቆሻሻቸው | ›› |
| ጌታን መቃወም | ›› | ስለማይችሉ | ›› |
| ይኸው ተገኘ | ›› | ወጣ መስቀሉ | ›› |
| ደጉ ኪረኮስ | አበባ | ሽማግሌው | አበባ |
| እሌኒን መራት | ›› | በደመራው | ›› |
| ጌታ በእርሱ ላይ | ›› | በመስቀሉ | ›› |
| ጭሱ ሰገደ | ›› | ወደ መስቀሉ | ›› |
| የዕምነት ምልክት | አበባ | መስቀል ነውና | አበባ |
| ተራራው ሜዳ | ›› | ሆነ እንደገና | ›› |
| እንደተነሣ | ›› | ጌታን እንደካዱ | ›› |
| ነጎድጓድ ወጣ | ›› | ከእጸ መስቀሉ | ›› |
| እኛም በመስቀል | አበባ | እንመካለን | አበባ |
| በእግዚአብሔር ጥበብ | ›› | መች እናፍራለን | ›› |
| ሞኝነት እንኳን | ›› | ቢሆን ለዓለም | ›› |
| ኃይል እጸወነ | ›› | ለዘለዓለም | ›› |
| ግድግዳው ፈርሷል | አበባ | የልዩነቱ | አበባ |
| ምድርና ሰማይ | ›› | ሆነ እንደጥንቱ | ›› |
| ነፍስና ስጋ | ›› | በእርሱ ታርቀዋል | ›› |
| ህዝብና አህዛብ | ›› | ወንድም ሆነዋል | ›› |

## 160. የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባቸው /4/
እመቤታችንን እናያታለን
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው /4/
እመቤታችን አለች ከጎናቸው /4/
አባ ህርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ፍቅር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋር ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው /2/
አንዱ ሀገር ስትሄድ አማኑኤል አለችው
›› ኢየሱስ ››
›› አንድዬ ››
ለመናኒው ጸሎት ልዩ እጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እመብርሃን

መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ድንኳን የሚሉልሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ /2/
ቤቴልሔም ስሔድ አይሻለሁ
ቀራንዮ ስሔድ አይሻለሁ
ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ /2/

## 161. ትህትናሽ ግሩም

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም /2/
እናቱ ሆነሻል ለመድሃኒዓለም /2/

ንጽህት ስለሆንሽ እመቤቴ /2/
እንከን የሌለብሽ ››
የፍጥረታት ጌታ ››
ባንቺ ያደረብሽ ››
የድንግል መመረጥ ››
ዜናው አስገረመኝ ››
እሳቱን ታቀፈች ››
የማይቻለውን ››

ምርኩዜ ልበልሽ እመቤቴ /2/
ጥላ ከለላዬ ››
ጋሻዬ ልበልሽ ››
የኔ መመኪያዬ ››
በዓለም እንዳልጠፋ ››
ሕይወቴ መሮብኝ ››
እንደ ወይን አጣፍጪው ››
ድንግል ድረሽልኝ ››

የምስራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ /2/
የሁላችን ተስፋ ››
እሙነ ፀሐይ ጽድቅ ››
የሁሉ ጠባቂ ››
ድንግል የድል አክሊል ››
ድንግል የጽድቅ ስራ ››

ድንግል መሰላል ነሽ ››
የተዋህዶ ተስፋ ››

## 162. ገድሉ ተዓምራቱ

ገድሉ ተዓምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣኦትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋህዶ ኮከብ ተክለ ሐዋርያ
አባ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ

ዳግማዊ ዮሐንስ ጠፍር የታጠቀ
ንጹህ ባህታዊ ጠላት ያስጨነቀ
የጸጋ ዘ አብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብር ሊባኖስ መናኝ አስከተለ

ደካማ መስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት
ባለ ስድስት ክንፉ ተክልዬ የእኛ አባት
እርሱስ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አስቦ
ሌጊዮን ሲዋረድ  እፍረት ተከናንቦ

ከካህናት መካከል ሕሩይ ነው ተክልዬ
መጣሁ ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት

የባረከው ውሃ የረገጥከው መሬት
ገላው ያረፈበት ሆኗል ጸበል ዕምነት
ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

## 163. <u>ክብረ ቅዱሳን</u>

ክብረ ቅዱሳን <u>ይዕቲ</u> /2/ ክብረ ቅዱሳን /2/
ሙዳየ መና <u>ግሩም ሙዳየ መና</u> /2/
የቅዱሳኑ ክብር ነሽና
እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና
የወለድሽልን የሕይወት መና
ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና
ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ
ጽንስ የዘልላል ሰላምታ ድምፅሽ
እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል
ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል

የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ
ታላቁን ብርሃን አየንብሽ
አትጨልምም ሕይወታችን
ልጅሽ እስካለ ፀሐያችን
ሰዓሊለነ ሰላም ለኪ
ተማህጸነ በኪዳንኪ
ንኢ ርግብየ ምስለ ወልድኪ
ሰማይ ወምድር ይወድስኪ

## 164. እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም እመቤቴ /2/
ባንቺ ያደረብሽ የሠራዊት ጌታ
እመቤቴ ማርያም ይድረስሽ ሰላምታ /2/
ሕይወቱን የሰጠ ፍጹም ለሰላም
ሁሉንም የሚችል ያለ በአርያም
የአምላክ ማደሪያ ድንግል ማርያም /2/
ጌታ የመረጠሽ እስከ ዘለዓለም /2/
የምድር ባለ ጸጎች ሲማልዱ ፊትሽ
የሰማይ መላዕክት ምስጋና ያቅርቡልሽ
አህዛብ ይንበርከክ ለሃያሉ ልጅሽ /2/
ክብር ይገባሻል በእናትነትሽ /2/
ላንቺ ሲያስተላልፍ ገብርኤል ሠላምታ
ከልዑል ተልኮ ከሠራዊት ጌታ
ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎ ያበሰረሽ /2/
እመቤቴ ማርያም ምስጋና ይድረስሽ /2/

## 165. እቴ ሙሽራዬ

እቴ ሙሽራዬ ሰሎሞን ያለሽ /2/
እኔም ልበልሽ እናቴ እመ አምላክ/ማርያም/ ጊቢ በቤቴ /2/
ሁሉም ሰው ለራሱ ወንበር ሲዘረጋ
የክብርን ሽልማት ለራሱ ሲያስጠጋ
ድንግል እንደ ባሪያ ውሃ ተሸከመሽ
ጌታን በትህትና ታገለግያለሽ
ወርቀ ዘቦ ለብሰው በቤቱ ከሞሉት
በሀርና በእንቁ ከተንቆጠቆጡት

በሰው ፊት ያማሩ ብዙ ሆነው ሳለ
ጌታ ግን ወደደሽ እናቴ ነሽ አለ
አሳድጎሽ ሳለ መልአኩ መግቦ
ተሸልመሽ ሳለ በዝቶልሽ ተውህቦ
እጅግ በትህትና ስላገለገልሽው
እንደ ኪሩብ መላዕክ ጌታን ተሸከመሽው
የባሪያውን ውርደት ተመልክቷልና
ለወለድሽው ንጉስ ይድረሰው ምስጋና
ከልብ የወጣ እንጂ ከንቱውን አይደለም
ብጽዕት እንላለን እኛ ዘለዓለም

## 166. <u>ካንተ የሆነው</u>

ካንተ የሆነው መልካም ነው /2/
ሁሉን በጊዜው ስትሰራው
ካንተ የሆነው መልካም ነው

የኑሃሚን ርስት ሞአብ አይደለችም
ለምለሙን እንጀራ ስቡን ብታበቅልም
በሙላት ወጥታችሁ ባዶ አትመለሱ
የእስራኤልን ቅዱስ ቃልኪዳን አስታውሱ

ሩት አትለፊ የቡኤዝን እርሻ
ጌታ ፈቅዶልሻል የእንጀራሽን ድርሻ
ያለኝ ይበቃኛል ብለው ለሚያምኑት
እጅግ አትርፈዋል ሰላም በረከት

እስማኤል አይደለም የእግዚአብሔር ስጦታ
አብርሃም ሆይ ጽና ባለህበት ቦታ
ሰላም እና ፍቅር ይዞ የሚመጣው
ይስሐቅ ይወለዳል ቢዘገይም ጊዜው

ሰዶም ብታበቅል ለምለሙን ቁጤማ
ለእግዚአብሔር ልጆች መቼም አትስማማ
ድንጋይ እንኳን ቢሆን የአብርሃም ርስት
ጠግበናል ልጆቹ ማርና ወተት

## 167. <u>አማላጅ ነው</u>

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠህ ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢ መላዕክ ጠባቂ የእስራኤል
የመላዕክ አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል

<u>አማላጅ ነው ሚካኤል</u> /2/ የአምላክ ባለሟል
ለእነ ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል
ፈርኦን በእስራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
ቢከታተላቸው ጦሩን አስነስቶ
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
ከባህር ያወጣኸው ጻጋ ዘአብን
ከአረመኔው ንጉስ እግዚእ ሐሪያን
ከልለህ የጠበቅህ በብዙ ተዓምራት
እኛንም ጠብቀን ከበደል ከሃጢያት
በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላዕክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ ከቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት
መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሃለን እንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

## 168. <u>እልፍ አእላፋት</u>

እልፍ አእላፋት ወትእልፈት ቅዱሳን ንጹሃን መላዕክት
ቆሙ ለአገልግሎት ጸንተው በአንድነት
<u>ቅዱስ</u> /3/ አምላክ በማለት /2/
ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት ሀገር
የሐይማኖት የፍቅር የምልከት ክር
እውነት የታየብሽ የመላዕክ ክብር
እንጽና ሲል ገብርኤል በአለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ
የሳጥናኤል ምኞት እንደ አበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በዕምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ጸጋውን ተገፎ
ቅዱሳን መላዕክት በዕምነት የጸናችሁ
በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ
ስግደት ወበጸጋ እንስገድላችሁ

## 169. <u>ድንግል መከራሽን</u>

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታውሰው
በሔሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት

ኧረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሃን አቋርጠሽ
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አሰበሽ
በግብፅ በረሃ <u>መከራሽን አየሽ</u> /2/ መከራሽን

አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በመከራ ጊዜ
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኝብኝ <u>አደራሽን ማርያም</u> /2/ አደራሽን

አቤት የዚያን ጊዜ ያየሽው መከራ
ያለቀስሽው ለቅሶ ጭራሽ አይወራ
የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨረስሽው <u>ሆነሽ ሀዘንተኛ</u> /2/ ሀዘንተኛ

## 170. ኢትዮጵያ ሆይ

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ /2/
ከህዝብሽ ጋር እልል በይ /3/
እጆችሽን በበረከት ስለሞላ /2/
ስላዳነሽ በጭንቅ ቀን ከሞት ጥላ /2/
እግዚአብሔር ብርሃንሽ ስለሆነ /2/
ከአስፈሪው ቀን ልጆችሽን ስላዳነ /2/
ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ /2/
በሽብሻቦ እልል በይ /2/
በሽብሻቦ ለአምላክሽ ዘምሪለት /2/
ስብራትሽን ይጠግናል በምህረት /2/
ለህዝብሽም እግዚአብሔር ኃይላቸው ነው /2/
በስቃይሽ የጎበኘሽ መመኪያቸው /2/
ሕዝብህን ባርክ ለዘለዓለም ጠብቃቸው /2/
በጽድቅህም ከፍ አድርጋቸው /2/

የምስጋና ነጎድጓድ ከአፍሽ ይውጣ /2/
ድሮም ቢሆን እግዚአብሔር ነው ያንቺ ዕጣ /2/

## 171. <u>ቅዱስ ሚካኤል</u>

<u>ቅዱስ ሚካኤል</u> /3/ ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ስጋዬ
ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ /2/

አንተ ስለሆንክ ሚካኤል
የአምላክ ባለሟል ››
ልመናህ ፈጥኖ ››
ከአምላክ ያቀርባል ››
የዋህ መላዕክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው /2/

ደዌ የጸናበት ሚካኤል
ባንተ ይድናል ››
በአደባባይህ ››
ምስክር ሆኗል ››
ከቤትህ መጥቶ የተማጸነ
በቃል ኪዳንህ ሕይወቱ ዳነ /2/

ከአምላክ ተሰጥቶህ ሚካኤል
ክብርህ ያበራል ››
ለጎስቋላው ሰው ››
መጠጊያ ሆኗል ››
ትልቅ ትንሹ ድሃው ሐብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ /2/

በብሉይ ኪዳን ሚካኤል
ከአምላክ ተልከህ ››
ህዝበ እስራኤልን ››
ነፃ ያወጣህ ››
በአዲስ ኪዳንም ድንቅ ስራ አለህ
በተዓምራትህ ትፈውሳለህ /2/

ባለመድሃኒት ሚካኤል
ያቃተውን ››
ፈዋሽ ጸበልህ ››
ሆኖኛል ኃይል ››
እንደ መጻጉ ድህነት አገኘሁ
ፈውሰሽኛል ባንተ ተመካሁ /2/

## 172. <u>እንበረታለን ገና</u>

እንበረታለን ገና በጸጋው ተደግፈን /2/
ወልድ ዋህድ እያልን ዓለምን እንከድናለን /2/
ጴጥሮስ የመሰከረው ዓለት ነው መሠረቱ
የአባቶቻችን አምላክ የዋጀን በስቅለቱ
ሲጠብቀን ይኖራል ከወጣንበት ቦታ
እናመልካለን እርሱን <u>በፍቅር በደስታ</u> /2/
ሲገሉን ሲያሳድዱን በቁጥር እንበዛለን
ሲንቁን ሲያዋርዱን በስሙ እንከብራለን
የሲኦልም ደጆች አይችሉንም እኛን
የተከለሃይማኖት አምላክ <u>ይችላል ሊያድነን</u> /2/
ልፋታችንን ያያል የሰማይ አምላካችን
ብዙውን እየሰጠን ጥቂቱን እንወስዳለን
ጽኑ ነው ማይተባችን ሳይበጠስ ይኖራል
የምናመልከው አምላክ <u>በልባችን ይሰራል</u> /2/
ተመስገን አምላካችን ዛሬ በዛን በፊትህ
በአህዛብ ተራሮች ላይ ይመሰገናል ስምህ
እያለፍን በጽድቅህ ዓለምን ልናቀና
ጌታ ሆይ ቅደምልን <u>ቃልኪዳን አለህና</u> /2/

## 173. <u>በዕምነታቸው</u>

በዕምነታቸው ዳኑ ከዚያ ነበልባል /2/
አናንያ አዛርያ ሚሳኤል /2/
ናቡከደነጾር ጨካኙ ንጉስ
በባቢሎን ሀገር ጣኦት የሚያነግስ
ወጣቶች ተነሱ በቅናት መንፈስ
አናንያ አዛርያ ሚሳኤል /2/
ላሰራኸው ጣኦት አንሰግድም እያሉ
በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ልባቸውን ሞሉ
አናንያ አዛርያ ሚሳኤል /2/
እንደ ሦስቱ ህፃናት በዕምነት ለሚቆመው
መለዓኩን ይልካል እግዚአብሔር ሊረዳው
ገብርኤል /2/ ከልኡል /2/

## 174. እጠበኝ ቆሽሻለሁ

እጠበኝ ቆሽሻለሁ አምላኬ በድያለሁ
ያለ እናት ያሳደግከኝ ያለ አባት የጠበቅከኝ
ያን ሁሉ ዛሬ ረሳሁ እጠበኝ ቆሻሻለሁ /2/
ከድንኳንህ ብታስገባኝ ሞገስ ሰጥተህ
የአፍኒንን ምግባር ይዤ አስቀየምኩህ
ቅባ ሜሮን ያተምክበት ልጅነቴ
እንዳይጎድፍ ጠብቅልኝ ቸር አባቴ
ኃይል አኑረህ እንደ ሶምሶን በፀጉሬ
ጎልያድን አስጥለኸኝ በጠጠሬ
አቅም ቢያንሰኝ በስጋ ጦር ተሸንፌ
ደጅህ መጣሁ የእንባ መባ በዓይኔ አቅፌ
እንዳትረሳኝ በመዳፍህ ቀርጸኸኛል
እንዳትተወኝ ያለ መጠን ወድደኸኛል
ባትሰነዝር ልትቀጣኝ የሞት በትር
የትዕግስትህ ሰሌዳ ነው ለኔ ክብር
ከከንፈሬ ጥበብ ጽፈህ ቅኔ ሲፈስ
በመታበይ አሳዘንኩት ያንተን መንፈስ
ፍቅር ግተህ በእቅፍህ ሥር ያሳደግከኝ
እባክህን በበደሌ አትቅሰፈኝ

175. **ተመስገን እንበል**

ተመስገን እንበል ተመስገን /2/
በድል አሳልፈህ ያንን ዘመን
አሳይተኸናል ይህን ተመስገን
ጀርባችን ቢቆስልም በዱላቸው
ተገልጦ ባያልቅም መዝገባቸው
የጠራን በደጁ ተከለን
ዓይናቸው እያየ ባረከን ተመስገን
መቼ ነው እያልን ናፍቀን ነበር
ንጋትና ጀንበር ስንቆጥር
ይኸው ሞት በቃል ታረደና
ልባችን ታመነ በአንተ ጸና ተመስገን
ግብፅን ጥለን ወጣን ሲኦልን
ባህሩን ተሻገርን እሳቱን
ኢያሪኮም ፈርሷል በዝማሬ
ነገም ድሉ ያንተ ነው እንደ ዛሬ ተመስገን

ጨለማው አለፈ ፀሐይ ወጣ
ጠላት ተሸነፈ ሃይሉን አጣ
ጌትነት ውዳሴ ክብር ማዳን
በዙፋኑ ላለው ለእርሱ ይሁን ተመስገን

## 176. <u>ብርሃኔና መድሃኒቴ ነው</u>

ጌታ ብርሃኔና መድሃኒቴ ነው /2/
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው /2/
አያሳስበኝም የሳአል ጥላቻ
ልቤ አይደነግጥም በጎልያድ ዛቻ
የምታመንበት ስሙ ጋሻዬ ነው
ኃይልና ብርታቴ ጌታ ጉልበቴ ነው
ሞገስ ይሆነኛል በነገስታቱ ፊት
እመሰክራለሁ ስሙን ያለ ፍርሃት
አያስጨንቀኝም ሞትና መከራ
ሁሉን የሚችለው አለ ከእኔ ጋራ
ጻድቃንን በገዳም የሚያበረታቸው
ሰማዕታትን በደም እንዲህ ያጸናቸው
አሁንም ይሰራል የብረሃን ጌታ
ስሙን ተሸክሞ በዕምነት ለበረታ
ከስም ሁሉ በላይ የሚበልጥ ስም ይዟል
የማመልከው አምላክ ከሁሉም ይበልጣል
ምንስ እሆናለሁ ስሙን ተደግፌ
በኢየሲስ ክርስቶስ ጥላ ሥር አርፌ

## 177. <u>በጌቴሴማኔ</u>

በጌቴሴማኔ በአታክልቱ ቦታ/2/
ለኛ ሲል ጌታችን <u>በዓለም ተንገላታ</u> /2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት /2/
እኛም ነበረብን <u>የዘለዓለም ሞት</u> /2/
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ /2/
ይገርፉት ነበረ <u>ሁሉም በየተራ</u> /2/
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /2/
እንዲህ ሲል ጸለየ <u>አባት ሆይ ማራቸው</u> /2/

በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ /2/
በሰው እጅ ተገርፎ <u>ሞተ ተቀበረ</u> /2/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /2/
እያየች በመስቀል <u>ልጇ ሲንገላታ</u> /2/
ፍቅሩን የገለጸው ተወልዶ በስጋ /2/
ኢየሱስ ክርስቶስ <u>አልፋና ኦሜጋ</u> /2/

## 178. አልፋና ኦሜጋ

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንከ
በከሐዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብከ
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
ቅድሳት እጃችህ የፈጥኝ ታሰረው
እንደበግ ተጎተትህ ብትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ
በአውደ ምኩራብ ከጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሐና ቀያፋ ከመሳፍንቱ ደጅ
ከነሔሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ
ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
ሳዶርና አላዶር ዳናትና አዴራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር በተራ
አምስቱ ችንካሮች ቅንዋት መስቀል
ወገኖችህ መጡ ሥጋህን ለማቁሰል
የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
ምራቅ ተፋብህ ራስከን ሊጎዱ
ግፈኞች አይሁዶች ባንተ ላይ ቀለዱ

## 179. ጌታዬ ሆነህ

ጌታዬ ሆነህ ደም ግባት አልባ
ጀርባው በጅራፍ ስለኔ ደማ

የኔን መገረፍ እርሱ ተገርፎ
ክብር አለበሰኝ እርሱ ተገፎ /2/
በሀሰት ሸንጎ ወጥመድ ተጠምዶ
ጌታ ተያዘ ሕይወቴን ፈቅዶ
ከፉዎች ቢያዩት እንደ ወንበዴ
ለእኔ ግን ሆኗል መውጫ መንገዴ /2/
ታሰረሃን ስለኔ ኢየሱስ መድህኔ /2/
ሲዘብቱበት ምራቅ ሲተፉ
የማይደፈር ደፍረው ሲዘልፉ
በከበቡት ፊት ቃል ከለከለ
እኔ እንድናገር እርሱ ዝም አለ /2/
ተወጋህ ስለኔ ኢየሱስ መድህኔ /2/
ሕይወት መንጭቷል ተወግቶ ጎኑ
ለከሳሾቹ ተርፏል ማዳኑ
እጅ እግሩን ሚስማር ሲቸነከረው
የሞትን እሾህ ከእኔ ነቀለው /2/
ተወጋህ ስለኔ ኢየሱስ መድህኔ /2/
እርቃኑን ሆኖ ፈተው ልብሱን
በምህረቱ ጠል ነፍሴን አርከቶ
አለመለመኝ እርሱ ተጠምቶ /2/
ተጠማ ስለኔ ኢየሱስ መድህኔ /2/

## 180. በእጸ መስቀል ላይ

በእጸ መስቀል ላይ በዚያ አደባባይ /2/
አምላክ ሆይ ጌታ ሆይ ተንገላታህ ወይ /2/
መስቀል አስይዘው ኪራያላይሶ
ወደ ጎልጎታ ››
ሲገርፉት ሲያዳፉት ››
ስትንገላታ ››
ያንን አቀበት ኪራያላይሶን
ያንን ዳገት ››
ጀርባህ ተገርፎ ››
ስትቃትት ››
አንተን እያዩ ኪራያላይሶን
ሴቶች ሲያለቅሱ ››
እናቶች ቀርበው ››
ላብህን አበሱ ››

መስቀል አስይዘው ኪራያላይሶን
እንዲያ ሲያዳፉህ ››
የቀሬናው ሰው ››
ስምኦን አገዘህ ››

## 181. <u>የህያዋን አምላክ</u>

የህያዋን አምላክ ሙታን ሊያስነሳ
በእኩለ ሌሊት ክርስቶስ ተነሳ /2/
ሙታን አይደለንም ክርስቶስ ተነሳ
ህያዋን ነን እኛ ››
በመስቀል ያዳነን ››
ከሃጢያት ቁራኛ ››
የተዋረድነውን ክርስቶስ ተነሳ
ሊያከብረን ዳግመኛ ››
ሞትን አሸንፎ ››
ተነሳልን ለእኛ ››
እናንተስ አትፍሩ ክርስቶስ ተነሳ
እመክራችኋለሁ ››
የተሰቀለውን ››
እንድትሹ አውቃለሁ ››
ህያዋን ከሙታን ክርስቶስ ተነሳ
ለምን ፈለጋችሁ ››
እንደተናገረ ››
ተነስቷል ጌታችሁ ››
ክርስቶስ ሲነሳ ክርስቶስ ተነሳ
በእኩለ ሌሊት ››
አስቀድሞ ታየ ››
ለመቅደላዊት ››

## 182. <u>የፍቅር እናት</u>

የፍቅር እናት የሰላም /2/
ይናፍቀኛል ስምሽን ሳልጠራው ስቀር ማርያም
በሕይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ
አንቺ አለሽና ከአጠገቤ

ምኞቴም ይሰመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ
ትላንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ
የለም ለነገ የሚያስፈራኝ
ሜዳ ይሆናል ተራራ
ልጅሽ ስላለ ከኔ ጋራ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ

## 183. <u>በማህፀን ቅኔ</u>

በማህፀን ቅኔ ለማርያም ተሰማ
ከተራራማ ሀገር በኤፍሬም ከተማ
ዮሐንስ ይናገር በረሃ ያደገው
ድንግል ስትናገር ምን እንዳዘለለው
የእናቱ ማህፀን የቅኔ ርስት ሆነች
ድንግል የአምላክ እናት ፊቱ ስለቆመች
በሐሴት ዘለለ ዘመረ በደስታ
ከድንግል ሲወጣ ታላቁ ሰላምታ
በድንግል ማህፀን ስላየ ጌታውን
ከመወለድ ቀድሞ ሰማነው መዝሙሩን
ትንቢቱ ሲፈጸም በሆድዋ ሲነግስ
ሰገደ ለአምላኩ የስድስት ወር ፅንስ
ጀመረ ስብከቱን ገና ሳይወለድ
ተፈጥሮ መች ቻለች ነብዩን ለማገድ
አፉ ተከፈተ በታላቅ ምስጋና
ከእናቱ ማህፀን ድምፅን አሰማና
የዮሐንስ እናት ኤልሣቤጥ ገረማት
ልጇ በማህፀን ቅኔ ሲቀኝላት
ድምጿን ከፍ አረገች ዓለም እንዲሰማ
ሞላት መንፈስ ቅዱስ ለመዝሙር ለዜማ

## 184. ልቤ በእግዚአብሔር ጸና

ልቤ በእግዚአብሔር ጸና /2/
አፌን አላቀኩኝ ለስሙ ምስጋና
በጠላቶቼ ላይ አፌ ተከፈተ
ማዳኑን አይቼ ልቤ ተደሰተ
እንደ እግዚአብሔር ያለ ረዳት ማን አለ
ደካማ ባሪያውን ስለተመለከተ
ጠግበው የነበሩ እንጀራን ተራቡ
ተርበው የነበር እንጀራን ጠገቡ
መች ጎድሎብኝ ያውቃል አንተን ተደገፌ
በእጆችህ በረከት ተሞልቷል መዳፌ
እግዚአብሔር ይገድላል እንዲሁም ያድናል
የኃይለኞችን ክንድ ሰብሮ ይታደጋል
መካኒቱ ሐና ወለደች ሰባት
ስራህ ይደንቀኛል በቀን በሌሊት
ምስኪኑን ከጉድፍ ያነሳል ከምድር
ይዘረጋለታል የክብሩን ወንበር
ተመከረ ልቤ ሐናን ተመልከቶ
እግዚአብሔር ሊጋስ ነው ለጠበቀው ተግቶ

## 185. ይበራል በክንፉ

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው
የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው
ያሳደገኝ መልዓክ ዛሬም ከእኔ ጋር ነው /2/
ከፊቴ ቀደመ ደመናን ዘርግቶ
እንዳልደናቀፍ ጉድባዎቼን ሞልቶ
ዛሬ ላለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ
ሰው ለመባል በቃሁ ሚካኤል ደገፈኝ
በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ
አለሁ እስከዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ
የሕይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከእርሱ ጋራ
ተጽፏል በልቤ የሚካኤል ስራ
በዚሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሰሶውን
ጽድቅ እየመገበ አሳደገኝ ልጁን
የአምላኬን ምስጋና ዘውትር እያስጠናኝ
እርሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ
ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር
ይሰማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር

የወሰደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ
ታላቁን በረከት በውስጤ አፈሰሰ
ሴኬምን እንዳላይ ከንፎቹን ጋረደ
መራኝ ወደ ሕይወት መዳኔን ወደደ
የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ
በጸጋው ቃል ቃኘኝ በበረከት ሞልቶ

## 186. ዘምር ዘምር አለኝ

ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ /2/
የአምላኬን ቸርነት እንዴት ብዬ ልርሳ
ያደረገልኝን እንዴት ብዬ ልርሳ
የሚቃጠለው ስብ በፊትህ ምንድን ነው
ሰማይና ምድር ሁሉ ገንዘብህ ነው
ያለኝን ሰብስቤ ባኖረው ከፊትህ
ዋጋ አይሆንም ጌታ ስለ ቸርነትህ
ይበዛል ይሰፋል የእግዚአብሔር ምስጋና
አይቆምም በዘመን ማዕበል ነውና
እንኳን ድንጋይ ቀርቶ ጋራው ቢናድብኝ
የከንፈሬን ፍሬ ማንም አይወስድብኝ
የጳውሎስ የሲላስ መከራ ቢጸና
አልተውም ቅኑውን የአምላክን ምስጋና
ሊያስጥለኝ አይችልም እስር ሰንሰለት
አለብኝ ውለታ የሰማዩ አባት
የተደረገለት ብዙ የተቀበለ
ይኖራል በፍቅሩ እየተቃጠለ
ክብሬን ሁሉ ትቼ ልዘምርልህ
ይህ ነው ችሎታዬ ላንተ የምሰጥህ

## 187. <u>አንድ አድርገን</u>

አንድ አድርገን ጌታ ሆይ አንድ አድርገን
ሰላምህን ፍቅርህንም ለግሰን
ቤተ ክርስቲያን ሆይ ምነው ተረበሽ
አንድነትሽ ጠፍቶ ሰላምን አጣሽ
አንደኛው ሲጠቅምሽ ሌላኛው ሲጎዳሽ
ብዙ ልጆች ወልደሽ የወላድ መካን ሆንሽ
በዘርና ጎሳ ስንከፋፈል
ቅጥራችን ፈረሰ በጠላታችን

መሳለቂያ ሆነን በየአደባባዩ
ልዩነትን አይተው ብዙዎች ተለዩ
ላያችን የሚያምር ልስን መቃብሮች
አስመስለን ያለን የሀሰት አማኞች
በመካከላችን ፍቅርን አስወጥተን
እንደ ርብቃ ልጆች እንገፋፋለን
ለዕምነት ያልቆመው በውሸት ሲከሰን
አንድነት ሳይኖረን ዘመንን አስቆጠርን
ያ ጥቅም ፈላጊው ሰምን እያጠፋ
ለስጋው የሚሆን ርስቱን አሰፋ

## 188. <u>በአምላካችን እንጻር</u>

በአምላካችን አንጻር እንዘምራለን
በእግዚአብሔር ቅዱሳን በግርማ ተከበን /2/
ሠማይ ተከፈተ ደስ ይበለን
ማሕሌት ተሰማ »
ዛሬ ተከበናል »
በመለኮት ግርማ »
በሰማይ ተሰማ የመላዕክት መዝሙር
የሠላም የደስታ የእውነት የፍቅር /2/
ደመና ከበበን ድንግል ተደሰተች
የሕዝቡን መመለስ ትመለከታለች /2/
ታላቅ ደስታ ነው በሰማይ ሠራዊት
ሰይጣን ድል ተነስቶ እኛ ስንባረክ /2/
ሰዎች እልል በሉ ውስጣችን ይታደስ
አምላክ ከእኛ ጋር ነው በልባችን ሊነግስ /2/

## 189. ፈተና ወጀብ ቢበዛ

ፈተና ወጀብ ቢበዛ አይተናል ህዝቡን ሲያበዛ
በሕይወት አንዴ ጠርቶናል እግዚአብሔር መች ይተወናል /2/
ፍቅር ነው የናርዶስ ሽቶ
ወደደን ተሰቅሎ ሞቶ
ነጎድጓድ መብረቅ ቢሆንም
በሕይወት አለን አሁንም /2/
መኳንንት ደጁን ከፈቱ
የጸጋው ፈልቷል ዘይቱ

ተራግፏል ሸክማችን
ምህረቱ ቢፈስልን /2/
ተጽናንቷል አርፏል ልባችን
በእሳት ታጥሯል ቅጥራችን
ብንወድቅም አንሸነፍም
ይዘናል የአምላካችን ስም /2/
ሕይወት ነህ የጽድቅ ጥላ
ያውቅሃል ቃል የተመላ
ነህ አንተ ጣፋጭ ምግባችን
እግዚአብሔር ቸሩ አምላካችን /2/

## 190. <u>ድንግል ትንሣኤሽን</u>

ድንግል ትንሣኤሽን እስከምናይ ድረስ
ገብተናል ሱባኤ በአንድነት በመንፈስ
ለእኛ እስከሚገለጥ ቶማስ ያየው እውነት
አንወጣም ከደጅሽ ኪዳነ ምህረት /2/

ሞትን የረገጠ ልጅሽ ካንቺ ጋር ነው
ውጦ የሚያስቀርሽ የቱ መቃብር ነው
የእርገትሽን ዜና ከቶማስ ሰምተናል
ትንሣኤሽ እውነት ነው ሰበንሽን አይተናል

ሞትማ በሞት ተሸንፏል በአንቺ ላይ እንዴት ኃይል ያገኛል/2/

ልናየው ወደድን የቶማስን ክብር
ለምን ተሰወረን የትንሣኤሽ ምስጢር
በራችንን ዘግተን በጸሎት ወድቀናል
ተገልጠሽ አብሪልን ልጆችሽ ናፍቀናል

ሞትማ በሞት ተሸንፏል በአንቺ ላይ እንዴት ኃይል ያገኛል/2/

መዝሙረኛ አባትሽ ዳዊት ጽፎልናል
ሞትን የማያይ ሰው ማን አለ ብሎናል
ይህ እውነት በዘመን አንቺ ላይ ቢደርስም
በሞት ተሸንፈሽ መቃብር አትወርጂም

ሞትማ በሞት ተሸንፏል በአንቺ ላይ እንዴት ኃይል ያገኛል/2/

ቶማስ ከደመናው ወርዶ ሲያናግረን
ስለሆነው ነገር እጅጉን ተመስጥን
እኛም ይህን ክብር ተመኘን ለማየት
ድንግል አሳስቢልን ኪዳነ ምህረት

ሞትማ በሞት ተሸንፏል በአንቺ ላይ እንዴት ኃይል ያገኛል/2/

## 191. የአብ ቃል አክብሮሽ

የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ
እግዚአብሔር በቃሉ ፍጹም ያከበረሽ
የምንመካብሽ መሰላል አንቺ ነሽ /2/
ቅድስና ለአንቺ ጽድቅም ለአንቺ ሆኖ
ዓለምን የፈጠረ በአንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ሕይወትን ያፈራሽ
አንቺን ለመረጠ አንቺን ለአጸናሽ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላክሽ /2/
አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ
የኤፌሶን ወርቅ የሚፈልቅብሽ
የግዮን ማዕበል ኢትዮጵያን የከበብሽ
ዮርዳኖስ ሆነሽ አህዛብን ፈወስሽ
በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ /2/
መዓዛሽን ወዶ ወልድ ዋህድ ዋጀሽ
አብም በሰማያት በህሊናው ጻፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ
እመካብሻለሁ እመቤቴ ስልሽ /2/
ወልድ በመውደዱ ከአንቺ መወለዱን
ንጹህ ሆኖ አግኝቶሽ ቅዱሱን ስጋሽን
ለቃሉ ማደሪያው ጽላቱና ታቦት
በብሩህ ደመና ተመስለሽለት
ከስጋሽ ተከፍሎ ከደምሽ ደም ወሰዶ
ከነፍስሽም ነፍስ ፍጹም ተዋህዶ /4/

## 192. የእቲሳ አንበሳ

የእቲሳ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ
ወገንህን ታደገው ከሃጢያት አበሳ
ተኩላው ለምድ ለብሶ በእርግጥ መጥቷልና
ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና
ዮሐንስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና

የዓለም ምናምንቴ የተባልከው ቅዱስ
የዋሁ መነኩሴ አባ ሕርያቆስ
ቅዳሴ ማርያምን ናና ዛሬ ቀድስ
በዕጣኑ መዓዛ ድውያንን ፈውስ /2/

የወንጌል አንበሳ ጎርጎርዮስ ፍጠን
ምሶሶው ሳይወድቅ መንጋው ሳይበተን
መብረቁ አትናቴዎስ ሞገዱን ገስጸው
አፈ ጉባኤያችን በመስቀልህ ዳኘው /2/

መርከቧን የሚያውክ መብረቅ መጥቷልና
አምላካችን ፈጥነህ አድነን ቶሎ ና
ጴጥሮስ ሆይ ቀስቅሰው ልንጠፋ ነው ብለህ
ሞገዱ እያየለ ዝም እንዳይል ጌታ /2/

ከሳቴ ብርሃን ሰላማ ቶሎ ና
ኖላዊ እረኛ ያስፈልጋልና
ስጋውን የጎዳ ነፍሱን የጠቀመ
ነቅ ጉድፍ የሌለው ግብሩ የታረመ /2/

## 193. <u>ገብርኤል ኃያል</u>

ገብርኤል ኃያል መላከ ሰላም መላከ ብስራት
የምታወጣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሚነድ እሳት
ፍቅርህ ተስሏል በልባችን
ፊትህ ቆመናል ባርከን ብለን

የጽናታቸው ዝናው ሲሰማ
ከዚያች ባቢሎን ከሞት ከተማ
ህፃናት ሳሉ በራ ዕምነታቸው
ቆመህ ተገኘህ መካከላቸው

ውሃው ሲዘልል ቢያስደነግጥም
በጋኖቹም ውስጥ ቢለዋወጥም
ጸንተው ዘመሩ ልጅና እናቱ
አንተ ስትደርስ ከዚያ ከእሳቱ

ቂርቆስም ጸና ሞትን ሳይፈራ
አንተ ሳላለህ ከነርሱ ጋራ
አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ
አምነው ድል ነሱት ያንን መከራ

እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ
ቆመህ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ
ከፋውን ዘመን የማልፍበት
ጽናትን ስጠኝ ድል ልንሳበት
እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ /2/

## 194. ጽላት ዘሙሴ

ጽላት ዘሙሴ ዕፀጳጦስ ዘሲና /2/
ፀናጽል ፀናጽል /5/ ለአሮን ካህን
ኟኸ ኟኸ ፀናጽል /5/ ለአሮን ካህን
አልፌያለሁና እመቤቴ ያን ሁሉ መከራ
ከኔ ጋር ስለሆንሽ እመቤቴ ስምሽን ስጠራ /2/

| | |
|---|---|
| በዚያ በጭንቅ ቀን | ድንግል |
| እጅግ በሚያስፈራው | ›› |
| ማን ያድነኝ ነበር | ›› |
| ስምሽን ባልጠራ | ›› |
| በሞትና ሕይወት | ›› |
| መካከል ቢሆንም | ›› |
| ታምርሽ አነሳኝ | ›› |

ማርያም አልተውሽኝም ድንግል አልተውሽኝም
እጅግ የከበደ ነበረ ያገኘኝ ፈተና
ታሪክ ሆኖ ቀረ እመቤቴ ባንቺ ዳንኩኝና /2/

| | |
|---|---|
| ዙሪያው የሚያስፈራ | ድንግል |
| ጽኑ ነው ገደሉ | ›› |
| በዚያ የወደቁ | ›› |
| እንዴት ይተርፋሉ | ›› |
| ስምሽ ድጋፍ ሆኖ | ›› |
| ከሥር ተነጠፈ | ›› |
| በሚያስደንቅ ምስጢር | ›› |
| ሕይወቴ ተረፈ | ›› |

## 195. ሰዎች ፈረዱብኝ

ሰዎች ፈረዱብኝ አንተ ግን አዳንከኝ /2/
አምላኬ ሆይ ተመስገንልኝ /2/
ሌላ ምን ቃል አለኝ
ሊያልፉኝ አልወደዱም ነቄን ሊሰውሩ
ሰዎች ፈጠኑብኝ በደሌን ሊያወሩ
አንተ ግን ሰብስበህ በፍቅር ሸፈንከኝ
በመተላለፌ አዝነህ ሳትለየኝ
ይህ ፍቅርህ ሰበረኝ አጣበቀኝ ከአንተ
ደጅህ ያወጣኛል ሁሌ እየጎተተ /2/
መርከሴን አውጀው ሲያነሱብኝ ድንጋይ
ሰወረኝ ታምርህ ልጅህ ሳልሰቃይ
ወደህ ስለማርከኝ ከፉዎች ተከዙ
ይህ አይደለም ብለው የኃጢአት ደሞዙ

ከአንተ በላይ ጌታ ማን ሊያውቀኝ ይችላል /2/
የፍቅርህን ሚዛን ማንስ ያዛባዋል /2/
ማዳንህ ይደንቃል ለወደኩት ልጅህ
ምህረትህ ይደፋል ሁሌም በሚዛንህ
እንደሰው አይታይ ፍርድህም ይለያል
ለባርያህ አርነት በምህረት ፈርደሃል
ፍቅር እየዘረዘርክ መንገዴን የጠረግህ /2/
ስለ ልጅህ ጽድቅን ለድህነት የፈረድክ /2/
እኔ አልፈርድብህም በሰላም ሂድ አልከኝ
ዳግም እንዳልበድል በፍቅር እያየሽኝ
ወደ ጽድቅህ ህጎች ነፍሴን አፈሳለሁ
እንዲህ ከወደድከኝ ወዴት እሄዳለሁ
አልለይም ካንተ ከፍቅር መድረኬ /2/
አመልካለሁ አንተን ፊትህ ተንበርክኬ /2/

## 196. ኪዳነ ምህረት እናቴ

ኪዳነ ምህረት እናቴ አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ

የተገለጠው ብርሃን ከምስራቅ የተወለደው
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ዓለምን ሁሉ አዳነው /2/

እንደው ዝም ብሎ ይገርመኛል የአምላክን ሥራ ሳስበው
ምክንያት አንቺን አድርጎ ይህንን ዓለም አዳነው /2/

በረሃውን ባሰብኩት ጊዜ የግብጽን አሸዋ ግለት
አንቺ ትንሽ ብላቴና ኸረ እንዴት ቻልሽው በእውነት /2/

## 197. እንዲህ እናምናለን

እንዲህ እናምናለን እንታመናለን /2/
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ እግዚአብሔር ብለን /2/
የእግዚአብሔር አብ ፍቅሩ ይሰፋል ይረቃል
ልጁን እስኪሰጠን እንዲሁ ወዶናል
በደብረ ታቦር ላይ እርሱን ስሙት ላለው /2/
በመዝሙር ለቃኘን ምስጋና ይድረሰው /2/
አብርሃም ይስሃቅን አባት እንደሆነው
አይደለም ልደቱ በአማን ልዩ ነው
የተወለደ ነው ከቶ አልተፈጠረም /2/
ከአባቱ ጋር ቅድመ ዓለም የኖረ /2/
ሊያጽናናን የሚላክ ከአብ የሚወጣ
በሃምሳኛው ዕለት ወደ እኛ የመጣ

የራሱ የሆነ ፍጹም አካል ያለው /2/
ጰራቅሊጦስ ጌታ እግዚአብሔር አምላክ /ቅዱስ/ ነው/2/
በዕደ ዮሐንስ ሲጠመቅ በማይ
ወልድ አምላክ መሆኑን ስንሰማ ከላይ
በአምሳለ እርግብ ወርዶ በርሱ የኖረው /2/
አካላዊው ቃል እስትንፋስ ሕይወት ነው /2/

## 198. ኢትዮጵያዊው ጻድቅ

ኢትዮጵያዊው ጻድቅ ማነው ብዬ ጠየኩ
በረከት ፈልጌ ልሳለመው ናፈኩ
ክብሩን ልመሰከር ተፈታ ምላሴ
ከደጁ ደርሼ ፍቅሩን በመቅመሴ

በእቲሳ ምድር ዘር ሆነህ በቅለህ
ተለየህ ለአምላክ ዓለምን ጥለህ
ደብረ ሊባኖስ ህያው ምስክር
ስለ አንተ ዝና ስለ አንተ ክብር
ተ/ሃይማኖት ወዳጄ ተባርኳል በአንተ ጓዳ ደጄ

አክባሪው አምላክ ስላከበረህ
ዛሬም ከእኛ ጋር በመንፈስ አለህ
ደጅ እንጠናለን በትህትና
የጻድቅ ጸሎት ሃይል አላትና
ተ/ሃይማኖት ፀሐይ ጼጋህ ይምጣልኝ ከሰማይ

ወደ ለምለም መስክ ሰብከህ መራኸን
የቃሉን ወተት አጠጥተኸን
ያቀጣጠልከው የወንጌል ችቦ
የአምላክ አድርጓል ትውልዱን ስቦ
ተ/ሃይማኖት ወዳጄ ተባርኳል በአንተ ቤቴ ደጄ

ሰላሳ ስልሳ መቶ ያፈራሕ
በደብረ አስቦ ቆመህ በአንድ እግርህ
የመቶ ሎሚ መሻት ቀረና
የጌታ መንገድ ጥርጊያውም ቀና
ተ/ሃይማኖት ወዳጄ ተባርኳል በአንተ ጓዳ ደጄ

## 199. ባርከን ባርከን

ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን /2/ ኧኸ
ቅዱስ መንፈስህ አንድ ሃሳብ አድርገን /2/
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሃሳብ አድርጊን /2/
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን /2/

ጥሪህን ስንሰማ ወደ አንተ እንድንመጣ
በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ላንወጣ
በሕይወት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም
እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኒዓለም
ባርከን ባርከን

ተፈረደብን የባርነት ሕይወት
መጣብን መርገም በመብል ምክንያት
ሲኦል እስራት እኛ የዳንብሽ
ድንግል ሆይ ምንጊዜም አይለየን ምልጃሽ
ባርኪን ባርኪን

አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን
በምግባር ስንደክም ሲጎል እምነታችን
በስጋችን ፈቃድ ወደን እንዳንጠፋ
በምህረትህ ጎብኘን አንተ ሁነን ተስፋ
ባርከን ባርከን

ንጽህተ ሕሊና ቅድስት እናታችን
አሳስቢ ሁልጊዜ ስለ ሃጢአታችን
ሊያድነን ነው እና ክርስቶስ በሞቱ
አስምሪን እማምላክ ድንግል ወላዲቱ
ባርኪን ባርኪን

## 200. የአፎሚያ ረዳት

የአፎሚያ እረዳት ነህ ሚካኤል /2/
ቅሩብ እግዚአብሔር የልዑል
ፈጥነህ ድረስልን ስንጠራህ ሚካኤል
ፊት ለፊታችን አምላክ ሰደደህ
አቀናህልን መንገዱን ጠርገህ
የቤሊሆርን ምክር እያፈረስክ
ከልጆችህ ጋር ከነዓን ደረስክ
ከእኛ ጋር ነበርክ አርባውን ዘመን
እንጠራሃለን ሚካኤል ብለን
በቃዴስ ክንፍህ ተዘርግቶልን
ደመናው ባንተ ተጋረደልን
አብረኸን ልትሆን ጌታ የላከህ
አንተ ሚካኤል ታዳጊያችን ነህ
ሙሴ ሲለየን ደጉ አባታችን
ሚካኤል ነበርክ ከላይ መሪያችን
የባርነቱ ጉዞ እስኪያበቃ
እጅግ ረዳት የእኛ ጠበቃ

ሳጥናኤል መክሮን የሐሰት ምክር
ሊወስደን ሻተ ሙሴ መቃብር
ስለማይጠቅመን አንተ ሰወርከው
ምክሩን በታትነህ አስጎነበስከው

## 201. የሰላምታሽን ድምፅ

የሰላምታሽን ድምፅ ስሰማ እመቤቴ /2/

ሀዘኑ ጠፋልኝ በዛልኝ ሐሴቴ /2/

የሰላምታሽን ድምፅ ከተራራው ሀገር
›› ከኤፍሬም ከተማ
›› ልቤ ተረጋጋ ድምፅሽን ሲሰማ
›› ቅድስት ኤልሣቤጥ ሆይ
›› በጣሙን ታደልሽ
›› የአምላኬን እናት አጽናኝ አገኘሽ

የሰላምታሽን ድምፅ ተገብቶኝ አይደለም
›› ቃልዋን ለመስማት
›› ፈቃዷ ሆነና ተሞላው ሐሴት
›› አንተ የእግዚአብሔር ካህን
›› በደህና ሂድ በለኝ
›› የእመቤቴ ድምጿ ስንቅ እንዲሆነኝ

የሰላምታሽን ድምፅ ነጎድጓድ ነው ቃሏ
›› እኔን ያጽናናኝ
›› ቤተ መቅደስ ሆዷ ነው የሰማ
›› ጸጋ መንፈስ ቅዱስ
›› ይኸው ተሞላሁኝ
›› ምስጋና ለድንግል ለማቅረብ በቃሁኝ

የሰላምታሽ ድምፅ በቅዳሴው መሃል
›› ውብ ቃልሽ ይሰማል
›› ሁሉም ተረጋግቶ አንቺን ያዳምጣል
›› ያዘነ ያጽናናል
›› ትካዜን ያጠፋል
›› ድንግልን የሰማ በተድላ ይኖራል

## 202. ተነሳልን

ተነሣልን መድኃኒታችን /2/
ከዲያቢሎስ ግዞት ነጻ ሊያወጣን
በመስቀል ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደም
ተደመሰሰልን የሃጢአት መርገም

በጠንካራ ድንጋይ መቃብር ቢዘጋ /2/
ድል አድርጎ ተነሳ አልፋና ኦሜጋ /2/
ሞትን ድል አድርጎ ለተነሳው አምላክ
እኛን ከባርነት ለታደገን በእውነት
ጌታዬ ተመስገን ሌላ ምን እላለሁ /2/
ለከበረው ስምህ ምስጋና አቀርባለሁ /2/
እልልታን እናቅርብ ለሃያሉ ንጉሥ
ሞትን አጠፋልን እኛን ለመቀደስ
ከባርነት ቀንበር እኛን አላቆናል /2/
በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወቱን ሰጥቶናል /2/
የአዳም ልጆች ሁሉ እንዘምር በእልልታ
ለሃያሉ እግዚአብሔር ለሰራዊት ጌታ
እንዘምር ዘምሩ ሰዎች ደስ ይበለን /2/
ሞትን አሳፍሮ ጌታ ተነሳልን /2/

## 203. በንጹህ ደሙ

በንጹህ ደሙ ያዳነን
ከወደቅንበት ያነሳን /2/
ብዙ ነው የእርሱ ውለታ
እንዘምራለን ለጌታ

ቀና ብለናል በክብረ
አንገቱን ደፍቶ በፍቅር
ስለኛ ብዙ ሆኖልን
የብርሃን አክሊል ደፋልን
የዓለም መድሃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው /2/

እርቃኑን ሆኖ ሸለመን
እየደከመ አቆመን
እርሱ በመስቀል ሲሞት
እኛ ተፃፍን በሕይወት
የዓለም መድሃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው /2/

እስከ ሺ ትውልድ ይምራል
ፍቅር ነውና ይራራል
አይዝልም የእርሱ ትከሻ
መጨረሻ ነው መድረሻ
የዓለም መድሃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው /2/

በደም ያጌጠ ልብስ አለው
ከአማልክት ማንም አይመስለው

ትውልዱ ማዳኑን ይስማ
ነግሷል በፅዮን ከተማ
የዓለም መድሃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው /2/

## 204. ተዋህዶ

ተዋህዶ ሃይማኖቴ
የጥንት ነሽ የእናትና አባቴ
ማህተቤን አልበጥስም
ትኖራለች ለዘለዓለም

የግብፅን ከተሞች በደም ገንብተናል
በመግደል ጽድቅ የለም ሞተን ግን ኖረናል
ማህተብሽን ፍቺው በጥሺው ቢሉኝ
እኔስ ከነአንገቴ ውሰዱት አልኩኝ

ጴጥሮስ ተሰቀለ ጳውሎስ ተሰየፈ
ተዋህዶ እያለ እረ ስንቱ አለፈ
ሌሎችም በእሣት በስቃይ አልፈዋል
ዘመን የማይሽረው ታሪክን ጽፈዋል

ፊተኛ ነንና እንዳንሆን ኋለኛ
ሕዝቤ ተነቃቃ ተነሳ አትተኛ
ጅብ ከሄደ ውሻ እንዳይሆን ጩኸቱ
የተዋህዶ ልጆች አሁን ነው ሰዓቱ

አይተን እንዳላየን ስንት አሳልፈናል
የእርሱ ፍቃድ ይሁን ብለን ዝም ብለናል
አሁን ግን ይበቃል ዝምታው ይሰበር
ይገለጥ ይታወጅ የተዋህዶ ነገር

## 205. እረድተሃልና

እረድተሃልና ባህራንን ሚካኤል
ጠብቀሃልና ቴዎብስታን ››
አስታርቀን አማልደን ››

ከሰማያት ስትወረድ ሚካኤል
ለሰው ልጆች ልትራራ ››
በክብርህ የተነሳ ››
መላው ምድር አበራ ››
በመከራዬ ጊዜ ››
ፈጥነህ የደረስክልኝ ››
ከአምላኬ ተልከህ ››
ከጭንቅ የገላገልከኝ ››

አልተረዳሁትም ሚካኤል
በእጄ ያለውን ››
የሞቴን ደብዳቤ ››
የሸሸኩትን ››
ልጨብጥ ስጣደፍ ››
የሰይፉን ስለት ››
የመላዕክት አለቃ ››
አዳነኝ ከሞት ››

ገና ህፃን ሳለሁ ሚካኤል
አሳድገኸኛል ››
ከብዙ ፈተና ››
አንተ አድነኸኛል ››
አሁንም ጠብቀኝ ››
ቸል አትበለኝ ››
አባቴ ሚካኤል ››
ልጄ ሆይ በለኝ ››

## 206. ንቁም

ንቁም በበሕላዊነ /4/
እስከ ንረክቦ ለመላዕክነ
ገብርኤል አለ ለመላዕክቱ
ጸንተው በመቆም እንዲበረቱ
እንደ ሊባኖስ ዝግባ ከፍ ያሉ
የጥፋት ልጆች ምድርን ቢሞሉ
አብዝተን እንጩህ ስሙን እንጥራ
እንጠብቅ ጌታን ለእኛ እስኪራራ
ሐሰት ቢነግስም እውነት ተረግጦ
ቃየል ሲነሳ ድንጋይ ጨብጦ
ጸብ ክርክሩ ቢያነዋውጸን
እንቁም በእምነት ትዕግስትን ይዘን
ብርቱ ሰንሰለት በእኛ ላይ ቢከብድ
በእሾህ ቢታጠር መሄጃው መንገድ
አይናችን ቢያይም ሰላም ደፍርሶ
መርዙን ይነቅላል እግዚአብሔር ደርሶ
መናወጥ ቢሆን በመርከባችን
ሞት ቢያጠላባት ጓዳ ደጃችን
ግራ ቀኝ ሳንል ፍጹም እንጽና
እግዚአብሔር እስርን ይፈታልና
ደስታችን ሲርቅ ላንደርስበት
ፊታችን ቢርስ በእንባ ጅረት

የሚያረጋጋን በሃያል ቃሉ
እግዚአብሔር አለ ያልፋል ይህ ሁሉ

## 207. ምህረት ከአምላክህ

ገና ሕጻን ሳለህ ጌታ መርጦሃል
ተክለሃይማኖት ክብር ይገባሃል
ኢትዮጵያ ሀገርህን አትተዋት
ምህረት ከአምላክህ ለምንላት

አንተ የደከምክበት ተ/ሃይማኖት አውሬው ሰልጥኖብን ተ/ሃይማኖ
ያ መልካም አዝመራ » ተፍገምግመናል »
እንክርዳድ ሞላበት » ተክልዬ አትተወን »
ተክለ አብ ቶሎና » ከአምላክ አስታርቀን »
አዝ

የምንኩስናውን ተ/ሃይማኖት ዛሬ በእኛ ጊዜ ተ/ሃይማኖት
ተግባሩን የፈጸምክ » ክደቱ በርትቷል »
ጣኦታትን ሰብረህ » መንጋ የሚጠብቅ »
ጠላትን ያሳፈርክ » አባት ያስፈልጋል »
አዝ

ገድላት ታምራቷን ተ/ሃይማኖት ለአንዲቱ ሃይማኖት ተ/ሃይማኖት
ንቀው ሲያቃልሉ » ለቀደመቺቱ »
ስርዓቷን ጥሰው » መከታ ሁንላት »
እናድሳት ሲሉ » ዛሬም እንደ ጥንቱ »
አዝ

ተኩላ ቤቱ ገብቶ ተ/ሃይማኖት ዘመኑን ምሰሉ ተ/ሃይማኖት
ከበጎች መሃል » እያለ ሲያባብል »
ክህደትን ሲያስተምር » ቶሎ ድረስልን »
ሕዝቡን ሲያታልል » አንተ ዝም አትበለን »

208. <u>ፃድቃን ሰማዕታት</u>

ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ
በአካለ በአካለ ስጋና <u>በአካለ ነፍስ</u> /2/ ያሉ
ከፈጣሪ አማልደው እኛን ያስምራሉ
የእግዚአብሔር አይኖቹ ጻድቃን ከማየት
ጆሮቹም አይርቁም እነርሱን ከመስማት
የጻድቅ ሰው ጸሎት ሃይልን ታደርጋለች
በምልጃቸው ድነን
የእግዚአብሔር መከራ ሳያሳቅቃቸው
እሳትና ስለት ሳያስፈራራቸው

ሰማያዊ ተስፋ ስለሚታያቸው
በፈተና ሁሉ ጸኑ በእምነታቸው
ሃጥኡ ነዌ እንኳን በሲኦል እያለ
ስለ ወንድሞቹ ምህረት ከለመነ
እናንተማ ጻድቃን በገነት ያላችሁ
ምንኛ ትረዱን አምነን ስንጠራችሁ
ቀዝቃዛ ውሃ እንኳን በጻድቅ ሰው ስም
የሚያጠጣ ቢኖር ዋጋው አይጠፋም
ብሎ እንዳስተማረ ጌታ በወንጌል
አምነን እንፈጽመው ዋጋ ያሰጣል

## 209. <u>ቤተ ክርስቲያን</u>

ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /4/
<u>አትመረመርም</u> /2/ እጅግ ጥልቅ ናት
ኸኸ <u>አትመረመርም</u> /2/ እጅግ ጥልቅ ናት
በስጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ /2/
የዕምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ /2/
<u>አንዳንዱ በክህደት</u> /2/ ፈጣሪውን አጣ
ኸኸ <u>አንዳንዱ በክህደት</u> /2/ ፈጣሪውን አጣ
የመስቀሉ ቃል ለእኛ የእግዚአብሔር ሃይል ነው /4/
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው
ኸኸ ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ /2/
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ /2/
<u>አንዳንዱ ቢክደው</u> /2/ እየተታለለ
ኸኸ <u>አንዳንዱ ቢክደው</u> /2/ እየተታለለ
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት /2/
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት /2/
<u>ወላዲተ አምላክ</u> /2/ መሰረተ ሕይወት
ኸኸ <u>ወላዲተ አምላክ</u> /2/ መሰረተ ሕይወት

## 210. እምድንግል

እምድንግል /3/ ተወልደ አማኑኤል

መጣ ተወለደ | አማኑኤል ተወለደ
የሠራዊት ጌታ | ››
ድምጹንም ሰማነው | ››
ይኸው በኤፍራታ | ››

የማይታይ ታየ | አማኑኤል ተወለደ
የማይዳሰሰው | ››

ሥጋ ማርያም ለብሶ | ››
በበረት አየነው | ››

እርቅ ተወጠነ | አማኑኤል ተወለደ
በቤተልሔም | ››
ሐዘን ተደምስሶ | ››
ሰፈነ ሰላም | ››

ሰብአ ሰገል መጡ | አማኑኤል ተወለደ
በኮከብ ተመርተው | ››
እጣን ወርቅ ከርቤ | ››
እጅ መንሻ ይዘው | ››

በቤተልሔም ተወለደ ተወልደ አማኑኤል /2/
እምዘራ ዳዊት /4/ ተወልደ አማኑኤል /2/

## 211. ማርያም

ማርያም /3/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
ባንቺ ስላደረ የዓለሙ ሁሉ ጌታ /2/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
መድሃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ
ገብርኤል /2/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ስጋን በመልበስ
በቤተ መቅደስ ተቀምጣ ድንግል
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

## 212. ኧረ እንዴት ነው አቡኤ

ኧረ እንዴት ነው አቡኤ
ኧረ እንዴት ነው ጻድቁ /2/

የሌጊዮን ጭፍሮች በስምህ አለቁ ኧረ እንዴት ነው አቡኤ ኧረ እንዴት ነው ጻድቁ
በፆም በጸሎትህ በመብረቅ ወደቁ ››
ገድሉ አንጸባራቂ ታምሩ የገነነ ››
በረከት ያገኛል ኪዳኑን ያመነ ››

ኧረ እንዴት ነው አቡኤ
ኧረ እንዴት ነው ጻድቁ /2/

ስለትን ይሰማል ጸበሉ ፈዋሽ ነው ኧረ እንዴት ነው አቡኤ ኧረ እንዴት ነው ጻድቁ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለጠሩት አባት ነው ››
እናቱ አክሌሲያ አባቱ ስምኦን ››
ምግቡ ምስጋና ነው ተሰጥቶታል ኪዳን ››

## 213. መድሃኒቴ

መድሃኒቴ ጌታ መድሃኒቴ
መድሃኒቴ የዘላለም ቤቴ

መድሃኒቴ በደለኛ ነበርኩ መድሃኒቴ ጌታ መድሃኒቴ
›› ሃጢአቴ የበዛ ››
›› ታሪክ ተቀየረ ››
›› አምላክ ሆነኝ ቤዛ ››
መድሃኒቴ የዘላለም ቤቴ /2/
መድሃኒቴ ከካራን ተለየሁ መድሃኒቴ ጌታ መድሃኒቴ
›› አገኘሁ ነጻነት ››
›› የአምላክን ፍቅር ››
›› በገሃድ አየሁት ››
መድሃኒቴ የዘላለም ቤቴ /2/
መድሃኒቴ አልተለየሽኝም መድሃኒቴ ጌታ መድሃኒቴ
›› አሁን አውቄአለሁ ››
›› ክብርህ ገናና ነው ››
›› ለዓለም እነግራለሁ ››
መድሃኒቴ የዘላለም ቤቴ /2/

## 214. አማላጄ

አማላጄ ድንግል አማላጄ /4/
አማላጄ ከሀዘን ከሰቆቃ አማላጄ ድንግል አማላጄ
›› ድኛለሁ ልጅሽ ››
›› የእናትነትሽ ››
›› ደርሶኝ ጥበቃሽ ››
አማላጄ ድንግል አማላጄ /2/
አማላጄ እናቴ እልሻለሁ አማላጄ ድንግል አማላጄ
›› ስጦታዬ ለኔ ››
›› ሁሉን አልፌአለሁ ››
›› ቆመሽልኝ ጎኔ ››
አማላጄ ድንግል አማላጄ /2/
አማላጄ ዘወትር ጠዋት ማታ አማላጄ ድንግል አማላጄ
›› ስምሽን እጠረራለሁ ››
›› አማላጅነትሽን ››
›› ለዓለም እነግራለሁ ››
አማላጄ ድንግል አማላጄ /2/

## 215. የመስቀሉ ነገር ሲገባን

የመስቀሉ ነገር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን /4/
የመስቀሉ ነገር የገባቸው /4/
እመቤታችን አለች ከነናቸው /4/
አባ ህርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ፍቅር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋራ ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር
የመስቀሉ ነገር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን /4/
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው /2/
አንዱ ሀገር ስትሄድ አማኑኤል አለችው
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው /2/
አንዱ ሀገር ስትሄድ ኢየሱስ አለችው
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው /2/
አንዱ ሀገር ስትሄድ አንድዬ አለችው
ለመናኒው ጸሎት ልዩ እጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እሙብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኛለሽ ምን ልሁን
የመስቀሉ ነገር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን /4/
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሀገር የሚሉሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ /2/
የመስቀሉ ነገር ሲገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን /4/
ቤተልሔም ስሄድ አይሻለሁ
ቀራንዮ ስሄድ አይሻለሁ

ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም

## 216. ይላል አንደበቱ

ይላል አንደበቴ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው
አይተወኝምና ወላጅ እንደሌለው
ትላንት የጠበቀኝ የነገም ተስፋዬ
ትላለች ነፍሴ ፍቅር ነህ ጌታዬ
የትላንት ሕይወቴን ዞር ብዬ ሳየው
ማምለጫ የሌለው አጥሩም እሾህ ነው
ወደርስቴ ወጣሁ ይድረስ ምስጋናዬ
ደጆች ቢዘጉብኝ በር ሆኖኝ ጌታዬ/2/
በጥልቁ በረሃ ምግብ መጠጥ ሆኖኝ
መንገዴን አቀና እጄን በአፌ አስጫነኝ
በእሳትና ውሃ መካከል አልፌ
ተመስገን እላለሁ ቅኔ ሞልቶት አፌ/2/
የብቸኝነቴን መዐበል ገስጿል
ለኔ ብርሃን ሆኖ ለከሳሽ ጨልሟል
ቀስቱን እያለፈ ታደገኝ ከስቃይ
የጌታዬ ሃሳብ ፍቅር ነው በኔ ላይ /2/
ትላንት ዛሬ ነገ ዘላለም ጠባቂ
የልቤን ፍላጎት ሳልነግርው አዋቂ
በባህሪው ቅዱስ የሌለው አምሳያ
ስሙ መደቤ ነው መልህቄን መጣያ/2/

## 217. <u>ድንግል ማርያም</u>

ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አሰምታ ትናገር ነበር
ሰላም ላንቺ ይሄን አለኝ ቅዱስ ገብርኤል
ሌላ ምንም አላውቅ <u>ያው ቃል እግዚአብሔር</u> /2/

ከመቅደስ ቁኝ ብዬ ትንቢት እየሰማሁ
ሀሩን አስማምቼ ጥበብን እየፈተልኩ
ሳለሁ በመገረም ያንን ቃል አስቤ
አምላክ ሰው ሆነብኝ ተመሰጠ ልቤ

ማናት ብዬ ሳስብ ያቺ ብላቴና
ገብርኤል ደረሰ ብስራቱን ያዘና
ዙፋኑ አደረገኝ የባሪያቱን ውርደት ተመልክቷልና

እንዴት ያንን ማህፀን ሰማይን ይሆናል
የልዑሉ ዙፋን ወዴት ይተከላል
እያልኩኝ ስጠይቅ በልቤ ለራሴ
የመንፈስ ቅዱስ ሃይል አደረ በራሴ

ማናት ብዬ .......

እንዴት ከድሃ ቤት ይሄ ንጉስ ያድራል
ለርሱ የተገባ ሰው ወዴት ይገኛል
ገሊላን አሰብኳት ዞሬ በህሊና
ለካስ ተሸንፏል በባሪያው ትትና

ማናት ብዬ ......

እሳት የማይበላው ሀመልማል አይኖርም
እንዲህ ያለ ቅጠል ናዝሬት አይገኝም
ህሊናዬ መጥቆ ሲበር ወደ ሲና
አንቺኮነሽ አለኝ ገብርኤል መጣና

ማናት ብዬ .......

## 218. አጌጥንበት

አጌጥንበት ስምህን ተዋብንበት ፍቅርህን
ሞገሳችን ሆነሃል የጽድቅ ልብሳችን አማኑኤል /2/
ተዋህዶ የአዳምን ስጋ አማኑኤል ሆነ ከኛ ጋ
በግርግም በቤተልሔም ተወልዶ ሆነልን ሰላም
ብንጠግብ በልተን ጠጥተን ብንገባ በሰላም ወጥተን
ልጆችን ወልደንም ብንስም ጠርተን ነው ጌታ ያንተን ስም
ቢያምርብን ቢሞቀን ለብሰን ብንረሳ ለቅሶና ሀዘን
ፍቅርህ ነው ዛሬን ያሳየን ተመስገን እንልሃለን
በባእድ ሀገር ብንኖር ቢገጥመን መከራ ችግር
ነጩን ልብስ ለብሰን ታይተናል መስቀሉን ከማህተቡ ጋር /2/

## ዘሰማየ ገብረ

ዘ ሰማየ ገብረ /2/ ወምድረ ሣረረ /2/
አልቦ ዘ ይመስሎ ለአምላክነ /2/
ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና /2/
ሃያል አምላክ ህያው ጌታ ያላንተ ማን አለና /2/

## ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብእሔር /2/ ምስጋና ይገባሃል
ለዚህች ዕለት ለዚህች ሰዓት /2/
በሠላም በጤና አደረስከን /2/

## ንጽሕተ ንጹሓን

ንጽሕተ ንጹሓን ከዊና ከመታቦር ዘደር ዘሲና
ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግልና ነበረት
ሲሳየ ሕብስተ መና ወ ስቴሐኒ ስቴ ድመና

## ኢያቄም ወሐና

ኢያቄም ወ ሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ
መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍጹም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሽ
አ /4/ እመ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሽ /2/

## ይቤላ ሕፃን

ይቤላ ሕፃን ለእሙ ኢትፍርሂ እም /2/ ነበልባለ እሳት
ለአናንያ ወ አዛርያ ወ ሚሳኤል
ዘ አድሃኖሙ ውእቱ ያድህነነ

## አውደ ዓመት

አውደ ዓመት ለባርኮ
ባርኮ አውደ ዓመት
ንኢ ማርያም በምህረት ወ ሣህል /2/

**ስለቸርነትህ**

ዓመቱን አሳልፈህ ለዚህ ያደረስከን
ስለቸርነትህ ጌታ ሆይ ተመስገን /2/

## ተልኮ መጥቶ

ተልኮ መጥቶ /2/ ገብርኤል /2/
እንዲህ ብሎ አላት ለድንግል /2/
የማህፀንሽ ፍሬ /2/ ኢየሱስ
የተባረከ ነው ቅዱስ /4/

## ማርያም ተአቢ

ማርያም ተአቢ እምኵሉ ፍጥረት /2/
ኢያዋያ እሳተ መለኮት /2/
ማርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት /2/
ስለያዘች እሳተ መለኮት /2/

## <u>ወረደ</u>

ወረደ እመስቀሉ /2/

<u>**እመስቀሉ**</u> /2/ አብርሃ ለኩሉ /2/
መስቀል ሐይል ንነ መስቀል ጽንነ
መስቀል ቤዛነ

መድሃኒትነ ለእለ አመነ /2/

## መስቀል ብርሃን

መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን
ወሃቤ ሠላም መድሃኔዓለም መስቀል ብርሃን ለእለ ነዓምን
መስቀል ብርሃን ነው ለመላው ዓለም መሠረት ነው
የቤተክርስቲያን

ሠላም ሰጪ ነው መድሃኔዓለም /2/

መስቀል ብርሃን ነው ለምናምን ሰዎች /2/

# ኩሉ ዘፈቀደ

ኩሉ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር
በሰማይኒ ወ በምድርኒ ወ በባህርኒ
ወበኩሉ ቀላያት ቀላያት /2/

# ጥልን በመስቀሉ

ጥልን በመስቀሉ ገደለ /2/
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሰላምን አደለ /4/

## ወረዶ

ወረዶ እመስቀሉ /2/

እመስቀሉ /2/ አብርሃ ለኲሉ

# መስቀል ሃይልነ

መስቀል ሃይልነ መስቀል ጽንነ መስቀል ቤዛነ መድሃኒተ ለዕለ አመነ

## የመስቀሉ ሃይል

የመስቀሉ ሃይል ለሚጠፉት ይመስላል ሞኝነት
ለእኛ ግን ሃይል ነው /2/
የሚሰጥ ሕይወት ነውና በዕምነት

# በወንጌሉ ያመናችሁ

በወንጌሉ ያመናችሁ /2/
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ /2/

## መስቀል ብርሃን

መስቀል ብርሃን ለኩሉ ዓለም መሰረተ ቤተ ክርስቲያን
ወሃቤ ሰላም መድሃኒዓለም
መስቀል ብርሃን ለእለ ነአምን

ትርጉም ፡- መስቀል ብርሃን ነው መሰረት ነው የቤተክርስቲያን
ሰላምን ሰጪ ነው መድሃኒዓለም
መስቀል ብርሃን ነው ለምናምን ሰዎች

## መስቀል ሃይልነ

ማርያም ተአበይ በኩሉ ፍጥረት
እያው አያ እሳተ መለኮት

# አክሊሎሙ አሆ

አክሊሎሙ አሆ ለሰማያት
ሲዋቶሙ ለካህናት
ለሀሲዮን መድሃኒት /2/
ኧኸ ለሀሲዮን መድሃኒት /2/
የሰማዕታት ኧኸ አክሊላቸው /2/
የካህናት ሹመታቸው /2/
ጽዮን ናት መድሃኒታቸው /2/
ኧኸ ጽዮን ናት መድሃኒታቸው /2/

## እስጢፋኖስ

እስጢፋኖስ ሰማዕት ሊቀዲያቆናት
በምዕመናን የተሾምክ /2/
ያምላክ ትዕዛዝ በስራ የፈፀምክ /2/

## መንክረ ግርማ

መንክረ ግርማ ሀይለ ልዑል ጸለላ
አማን/2/ መላዕክት ይኬልልዋ/2/

ትርጉም ፡- በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል ሀይል ጋረዳት/2/
በእውነት/2/ መላዕክት አመሰገኗት/2/

**<u>በመኑ</u>**

በመኑ በአምሳለ መኑ አስተማስለኪ /2/
እመቤቴ የኔ አማላጅ አዛኝቷ አ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ

<u>ትርጉም</u> ፦ ማን በተመሰለው ምሣሌ እመስልሻለሁ
እመቤቴ የኔ አማላጅ አዛኝቷ ምስጋናን የተመላሽ ነሽ

## ሆሣዕና እምርት

ሆሣዕና እምርት እነተ አቡነ ዳዊት /2/
ቡርክት እንተ ትመጽእ መንግስት /2/
ትርጉም ፡- የታወቀችይቱ የድህነት ቀን የምትመጣይቱ
የአባታችን የዳዊት መንግስት ቡርክት ናት

# እም አፈ ደቂቅ

እም አፈ ደቂቅ ወ ህጻናት አስተዳሎከ ስህሐት /2/

በእንተ ጸላኢ /4/ ከመ ትንሰቶ ለጸላኢ ወለገፋኢ /2/

# ተወልዳለችና

ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መድሃኒት /2/

እናመስግናት እናወድሳት አንውደዳት /2/

እናመስግናት እናወድሃት እርሷ ናትና

የአዳም ሕይወት /2/

## መጻዕ መርዓዊ

መጻዕ መርዓዊ ፍስሐ ለኩሉ /2/
በሰላም ጻኡ ተቀበሉ /2/
ሙሽሮች ደረሱ ደስታ ለሁሉ /2/
በሰላም ውጡ ተቀበሉ /2/

# መርዓዊ ሰማያዊ

መርዓዊ ሰማያዊ /2/
ለእመ ገብረ በዓለ /2/አኸ /2/
ይኑሩ በሰላም /3/ ፀንተው ዘለዓለም
ደናግል ተነሱ ያዙ መብራትን
ሙሽራው ደረሰ አጉል እንዳንሆን
ወንጌልን ይዘዋል ጎዳናቸው ያምራል
ዓላማው መልካም ነው እነሱን እንምሰል
የድካም ዋጋቸው /2/
ብርሃኑ ያበራል በሃይማኖታቸው
የሙሽራው ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኩት ብሩክ ሰው ይሁን
የሙሽሪት ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኳት ብሩክት ትሁን

# እልል እልል

እልል እልል ደስ ይበለን /2/
አጅበን መጣን ሙሽሮችን
እልል ብላችሁ ተቀበሉን
እናንት ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ /2/
የአብርሃም የሣራ ይሁን ጋብቻችሁ
መልካም መተሳሰብ ክርስቶስ ይስጣችሁ
ሣራና አብርሃም ሁሉም የሚያውቃቸው
ሁለቱም ቅዱሳኖች ናቸው
ፍቅራቸውን አይቶ አምላክ ባረካቸው
ለእናት ለአባት ታዛዥ ብሩክ ልጅ ሰጣቸው
ለጌታ መስዋዕት እኔ ልቅረብ ያለው
ይስሐቅን ለአብርሃም የሰጠው
በመልካም ጋብቻ በጥሩ ትዳር ነው /2/

ቅዱስ አባታችን ፈጣሪያችን ሆይ
ጌታችን አምላካችን ሆይ
በአብርሃም ጎጆ እንደገባህበት
በሙሽሮችም ቤት በረከት ሙላበት /2/
በቃናዋ መንደር የተዳርክ ሰርገኛ /2/
አምላክ ተገኘልህ ሆነህ እድለኛ /2/
በቃናዋ መንደር የተዳርሽ ሠርገኛ
ድንግል ጎበኘችሽ ሆነሽ እድለኛ
ማርያም ጎበኘችሽ ሆነሽ እድለኛ

## የቃናው ደስታ

የቃናው ደስታ ዛሬ ተደገመ
ጌታ ከእናቱ ጋር በሠርጉ ታደመ
የዘለዓለም አምላክ ስለአለ በዚህ ቤት
ሙሽራው ሙሽሪት አጉኙ በረከት
 መርዓት ተሸልማ የድንግልና አክሊል
 እዩት ሥርዓቱን እጅግ ያስደስታል
 አንድ አካል ሙሽሮች እዩአቸው ሲአበሩ
 በወንጌሉ በተክሊሉ ሄዱ እየተመሩ
እንግዳችሁ ብዙ ድንኳናችሁ ሙሉ
ጌታ ከእናቱ ጋር አለ በመሃሉ
የወይን ጋኖቹ ዛሬ ሙሉ ናቸው
አማኑኤል ድንግል ማርያም ስለአሉ ቤታቸው
 በክብር ታጅቦ ሲመጣ መርዓዊ
 እጅግ ያስደስታል አይደለም ምድራዊ
 ዛሬ በዚህ ድንኳን ደስታ ተደረገ
 በአማኑኤል በአምላካችን ስለተባረከ
በተክሊል በቁርባን የሆነው አንድነት
አይነጣጠልም ዳግም ወደ ሁለት
ሙሽሪት ሙሽራ ተደሰቱ ዛሬ
በሠርጋችሁ ተገለጠ የእምነታችሁ ፍሬ

## ሁለቱም አንድ ሆኑ

ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ /2/
በእግዚአብሔር በሕያው ቃሉ
ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ
ወንድና ሴት አደርጎ የፈጠራቸው
በሁዋላም በቃሉ አንድ አደረጋቸው

እናትና አባቱን የአዳም ልጅ ይተዋል
ከሚስቱም ጋር በሰላም በአንድ ይተባበራል
ሁለቱ አንድ ሥጋ ሆነው ይኖራሉ
ብሎ አስተምሮናል ጌታችን በቃሉ
አንድ ሥጋ ናቸው አይደሉም ሁለት
የባልና የሚስት ሕይወት ውሕደት
እንግዲህ እግዚአብሔር ካጣመራችሁ
በሆነው ባልሆነው ሰው አይለያችሁ
ለወገኖቻችሁ ምሳሌ ሆናችሁ
በክርስቶስ ፍቅር አምላክ ያቁማችሁ
ምንጣፋችሁ ንጹሕ መኝታችሁ ቡሩክ
ስለሆነላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ
ዓለም እንዲደነቅ ጠላት አንዲያፍር
በሃዘን በደስታ ይኑራችሁ ፍቅር

## ደመቀ አበራልን

ደመቀ አበራልን የአማኑኤል ሥራ /2/
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ
በቤተ ክርስቲያን ጥላ ተጠልለው
ተክሊል አድርገዋል ሙሽሪት ሙሽራው
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው
ሙሽሪት ሙሽራው አበራ ገጻቸው
የተራራቀ አካል አንድ ሆነ በተክሊል
እግዚአብሔር ይመስገን እልል እልል እንበል
አጥንትሽ ከአጥንቴ ሥጋሽ ከሥጋዬ
አዳም የሰበከው ይኸው ዛሬ ታዩ
የተክሊክ ብርሃንዋ በእኛ መሃል በርቶ
እረቂቅ አንድነት ታየ በእርስዋ ጎልቶ
ይህን ድንቅ ነገር ለማየት ያበቃን
ሚስጥሩን የሚገልጥ እግዚአብሔር ይመስገን
ነጭ መጎናጸፊያ በአንድ ተጎናጽፈው
በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አረፉ ከጥላው
ሙሽሪት ሙሽራው ለፍቅር ተሸነፉ
ለቁርባን መቁረቢያ ነጭ ልብስ አሰፉ

## ተፈስሒ ቤተክርስቲያን

ተፈስሒ ቤተክርስቲያን ተፈስሒ ቤተ ሥላሴ
ያሳደግሻቸው ልጆችሽ አብርሃም ሣራን ሲሆኑልሽ
ያሳደግሻቸው ሙሽሮችሽ አብርሃም ሣራን ሲሆኑልሽ

ትምህርትሽ ገብቶአቸው የወንጌሉ ቃል
በኑሮ ሊያበሩ ይኸው መጥተዋል
በክርስቶስ ትምህርት በቃሉ ተመርተው
ለዓለም መስከሩ ተራራ ላይ ቆመው ተፈስሒ

ከእንቅቡ በታች አይደለም መብራቱ
በራ እንጂ ለሁሉ ከእነ በረከቱ
ጢስ የሌለው ሻማ ደምቀው የሚበሩ
ልጆችሽ ሙሽሮች እንደ ጡዋፍ አበሩ ተፈስሒ

ሰላም ለአንቺ ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽለት ለወንዱ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽለት ከምርቃት ጋሪ ተፈስሒ

ቃልሽ ይለውጣል ግሩም ነው ሃያል
አመንዝራዎችን ድንግል ያደርጋል
ተገለጠ ክብርሽ በሙሽሮች ዛሬ
መከር ሆኖልሻል በአፈራሽው ፍሬ ተፈስሒ

ሰላም ለአንኪ ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽላት ለውድዋ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽላት ከምርቃት ጋራ ተፈስሒ

## ሙሽራዬ

ሙሽራዬ /3/ አበባዬ
ከጎንህ የምትሆን እህት አገኘህ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለህ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ለዚሁ ከአበቃችሁ
ቤታችሁ ይመረቅ በፍቅር ያጽናችሁ
ወንድ አግኝተሻል የሚያስብልሽ
የእኛማ ሙሽራ እንካን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን እኛም ደስ ብሎናል
በቤተ ክርስቲያን ሠርጋችሁ ውብ ሆኗል
እንደነፍስህ አድርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንህ በጌታችን ፊት
እንድታስቢለት አንቺም ለአካልሽ
አደራ ትላለች ወንጌል እናትሽ
በሥጋ በደሙ ሕይወት አግኝታችሁ
ፍሬአችሁም ይብዛ ይባረክ ጓዳችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይኼ ጋብቻችሁ
እስከ መጨረሻው ኑሩ ደስ ብሏችሁ

## ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ

ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ /2
ለዚህች ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ /2/
በእግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ፈቃዱ
በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሐዱ /2/
በሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድሃኔዓለም ፊት ጋብቻን ፈጸሙ /2/
በቤተክርስቲያን በፈጣሪአቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህች ቅድስት ዕለት /2/
አንድ የሚያደርጋቸው ተነበ ወንጌሉ
በካህኑ መስቀል በረከት ታደሉ /2/
በወንጌል ብርሃን በሐዋርያት ቃል
በእመብርሃን ፊት ጋብቻችሁ ሰምሯል /2/
በአምላክ ሥጋና ደም ሁለቱም ታተሙ
የሕብረት ቃል ኪዳን በአንድ ላይ አሰሙ/2/
ጸንቶ የሚያጸድቅ የማይለያያቸው
ክቡር ቃል ስለአለ በመካከላቸው /2/
እስከ መጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአማኑኤል ሥጋ አስተሳሰሮአቸዋል /2/

## በሠርጋችን ዕለት

በሠርጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በዕምነት ሆነን
ከእናትህ ጋር ከእመቤታችን
ከመላእክትህ ጋር ና በሠርጋችን
ከሐዋርያት ጋር ና በሠርጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሠርጋችን

በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳንም ጌታ ስንጠራህ
የጥሪ ወረቀት ልከናል እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር

ነይ ከልጅሽ ጋር እመቤታችን
እንድታሚይልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶውን እንዲሞላ
በረከት የእርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ

በጎደለው ሁሉ እየጨመርሽልን
ቤታችንን ሁሉ ሙይው እናታችን

ለአገልጋዮችም ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖችን ይሙሉአቸው

# አጅቡት በእልልታ

አጅቡት በእልልታ ሲመጣ ሙሽራው
ፍጹም የሚያስደስት የሠርጉ ዕለት ነው
ዘመዶቹ ሁሉ ተቀበሉት ውጡ
የሙሽራው መምጫ አሁን ነው ሰዓቱ

እልል /2/ እንበል እንዘምር በደስታ
ይህን ለአደረገ ለሠራዊት ጌታ
ሁሉንም በጊዜው ይፈጽማልና
ይኸው አበቃቸው ለዚህ መልካም ዜና

ሙሽሪት ተደሰች ዝምታው ምንድነው
የዳግም ልደትሽ የሠርግሽ ዕለት ነው
አዳም ጎንሽ ቆሞ ሔዋን ሆይ ሲልሽ
መንፈሳዊ ሐሴት ይሙላ በልብሽ

እህት ወንድሞቿ እናትና አባትዋ
ተነሱ ዘምሩ ለልጃችሁ ደስታ
መሄድዋ ነውና ወደ ቤቷ ዛሬ
ወደ አዲስ ጎጆዋ ሸኟት በዝማሬ

ቤተሰቦችሽን ሁሉንም ትተሽ
መሄድሽ ነውና ወደ መኖሪያሽ
ከአማኑኤል ጋራ ባልሽን ይዘሽ
ተነሽ ሙሽራዬ ደርሷል ሰዓትሽ
ከድንግልም ጋራ ሚስትህን ይዘህ
ተነስ ወንድሜ ሆይ ደርሷል ሰዓትህ

## እንደ አብርሃም እንደ ሣራ

እንደ አብርሃም እንደ ሣራ /2/
ሥላሴ ይኑሩ ከእናንተ ጋራ /2/
ቤታችሁ ይባረክ በበረከት ይሙላ
ፈቅደው ይስጧችሁ ሰላምና ጤና
ቤቱም የሥላሴ ይሁንላችሁ
ዘወትር ይኑሩ በመካከላችሁ
ጌታዬ በይው ውድሽ ነውና
እህቴ በላት ሥጋህ ናትና
ጽድቅ የተሞላ ፍሬ ይስጣችሁ
አብርሃም ሣራን ሁኑ ጸንታችሁ

ቤታችሁ ይከፈት ለእንግዳ ሰው
ከፍላችሁ ስጡ ለተራበው
መልካሙን ፍሬ አፍሩ ተግታችሁ
ስመ ሥላሴን እያሰባችሁ

## ሙሽራው ሙሽሪት

ደስ አላቸው ሙሽራው ሙሽሪት
በዝማሬ ››
ደምቆ ታይቷል ››
ጋብቻቸው ››
እግዚአብሔር ይመስገን ሙሽራው ሙሽሪት
ሃያሉ ጌታችን ››
ለዚህ ላበቃቸው ››
ወንድም እህታችንን ››
ጋብቻ ቅዱስ ነው ››
ብሎአል አምላካችን ››
እንደዚህ ሲፈፅም በቤተክርስቲያን
መኖር የለበትም ሙሽራው ሙሽሪት
አዳም ብቻውን ››
ብሎ ፈጠረለት ››
ከጎኑ ሔዋንን ››
ዛሬም እንደቀድሞ ››
እንደ መጽሐፉ ››
መርጦ እህት ሰጠው ለአዳም ሙሽራው
ሔዋን ጎኑ ሆና አዳም ሙሽራው ሙሽሪት
አዳም ሆይ ስትለው ››
በረዳትነቷ ››
አዳም ደስ ደስ አለው ››
በፍቅር ተሳስረው ››
አንድ አካል ሆነዋል ማንም አይለያቸው

## ንጽሕት ድንግል

ንጽሕት ድንግል ቡሩክት
የአምላክ እናት እመቤት
ልጆችሽ ሙሽሮች ሁለቱም አንድ ሆኑ
ተዋሃዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ
ፍጹም መንፈሳዊ ልዩ ፍቅር
አንቺ ያለሽበት መልካም ትዳር

መሠረቱ ዛሬ ልጆችሽ
ቅድሰት ሆይ ባርኪያቸው ተነኝተሽ
ድንግል ጒጇቸውን ቀድሰሽ
እውነተኛ ፍቅር መሥርተሽ
በመካከላቸው ተነኝተሽ
ሁሉን አሰጪያቸው አማልደሽ
ሙሽሮቹም አምነው በምልጃሽ
እናታችን ባርኪን ነይ ሲሉሽ
ፈጥነሽ ድረሽና በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሺ መሃላቸው
አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ
የሕይወት አጣፋጭ ቅመም ነሽ
ሙሽሮቹም ዛሬ ይጠሩሻል
የጒጇችን ፋና ነይ ይሉሻል

## የቤታችን እራስ

የቤታችን እራስ ልጅሽ ነው
አማላጅነትሽ የሚያድነን ነው /2/
እመብርሃን /2/ ሰላም አንቺ እኮ ነሽ እመቤታችን
ምን አለንና እኛ በጓዳችን
የጎደለ ነው ያለው ማድጋችን
ነይ ከልጅሽ ጋር እንድትሞይልን
ድንግል እመቤታችን
ያለን ውሃ ነው ከባዶ ጋን ጋራ
የጓዳውም ወይን ብዙም አላፈራ
የድሃ ጎጇችን እንዲባረክልን
ድንግል አሳስቢልን
በሰራፕታ ምድር ታምራት ያረገ
በኤልያስ አድሮ ሕዝቡን የባረከ
ዛሬም እርሱ ነው የቤቱ ሰላም
አምላክ መድሃኔዓለም
ጭንቀትን አይተሽ የልብን ሃዘን
ታሳስቢያለሽ እንዲጎበኘን
እኛም አንቺን ጠርተን ከእፍረት ድነናል
ድንግል ክብር ይገባሻል

## ዕፁብ ድንቅ ሥራ

ዕፁብ ድንቅ ሥራ /2/
በእውነት የታደለ የእግዚአብሔር ሙሽራ

በእውነት የታደለች የእግዚአብሔር ሙሽራ
ነፍሳችሁ በሰማይ እርግብ ትመስላለች
ከመላእክት ጋር ዛሬ ዘምራለች /2/
እልል /2/ በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ
ያበራ ጀመረ ሙሽራው ፀዳሉ
ያበራ ጀመረ ሙሽሪት ፀዳሏ
ከክርስቶስ ሠላም እንዴት ይርቃል ሰው
ሥጋና ደሙን ላይሳሳ ከሰጠው
የመንፈስ ቅዱስ ህፃናት በመሆን
በሥጋ ወደሙ መቀደስ አለብን /2/
በእግዚአብሔር ተባርኮ የመኖር ምስጢር
የዘላለም ሕይወት ይሰጣል ፍቅር
ሥጋውን ፍሪዳ ደሙንም መጠጥ አርጎ
ሰጥቶናል አማኑኤል ሕይወቱን ለውጦ

## ድንቅ ነው በጣም

ድንቅ ነው በጣም ድንቅ ነው /2/ በጣም
በሠርጋችን እለት ተገኘ መድሃኒዓለም
በሠርጋችን እለት ተገኘች ድንግል ማርያም
በቃልህ ተመርተው ለዚህ ቀን በቅተዋል
በፊትህ ጋብቻን ይኸው ፈጽመዋል
በፈሰሰው ደምህ ህብረት መስርተዋል
በሥጋም በነፍስም /2/ የአንተነን ብለዋል
የአዳምን አንድ አጥንት ከጎኑ ወስደህ
አጋር እንድትሆነው ሔዋንን ሰጠህ
ሁለቱንም ባርከህ እንደፈጠርካቸው
ዛሬም ለሙሽሮች /2/ ሰላምን ስጣቸው
ጌታ ሆይ ፍቅርህን በቃልህ መሰረት
አንድ ሆነዋልና በዚች ቅድስት ዕለት
እርሱንም እርሷንም ባርከህ ቀድሳቸው
ዘላለማዊ ክብር /2/ ጸጋህን ስጣቸው
የዲያብሎስ ተንኮል እንዳያጠምዳቸው
እስከመጨረሻው ጋሻ ሁንላቸው
ከቅዱስ ቁርባኑ ሁለቱም ሳይርቁ
ጽናቱን ስጣቸው /2/ አብረውኢ እንዲዘልቁ

## አምሮ ሲያበራ

አምሮ ሲያበራ ኑ ተመልከቱ /2/
በእግዚአብሔር ክብር ሲመላ ቤቱ /2/

ማነው የገባው በዚህ ጣራ ስር
ለሙሽሮች ደስታ ሊያበስር
ቤቱ ተመላ ሰላም ፍሥሐ
እናቅርብለት ምስጋና አምሀ
በአብርሃም ቤት የተገለጠው
በአልዓዛር ቤት እራት የበላው
ከእናቱ ጋራ ገባ ከቤቱ
ቤተ ዘመዱ ኑ ተደሰቱ
የእኛ ሙሽራ ደስ ይበልህ
ታላቅ እንግዳ ገብቷል ቤትህ
ሙሽራችን ሆይ ደስ ይበልሽ
የሰማይ ንግሥት ጎበኘችሽ
ለእድምተኞቹ መልካም ወይን አለን
የቃናው ጌታ የጠመቀልን
አናፍርም እኛ እንግዳ ጠርተን
አምላክ ከእኛ ጋር ስለሆነልን

## ቃና ዘገሊላ

ቃና ዘገሊላ /2/ በዛ በሠርግ ቤት
ተገኝተሻል ድንግል ከልጅሽ ጋራ
ተገኝተሃል ጌታ ከእናትህ ጋራ
እድምተኞች ሞልተው የተጋበዙበት
ሲበሉ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
ድንግል እናታችን ቤዛዊት ዓለም
አንቺ ደረሽለት ሆንሽው አማላጅ
አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉ ይቻልሃል ወይኑን ሙላላቸው
ማድጋው ጋዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው አመቤታችን ነሽ
የጌታ አምላክነት የተገለጠበት
ምንኛ ታደለ የነዶኪማስ ቤት
ዛሬም ይኸው በዚህ በሠርገኞቹ ቤት
በረከት ፈሰሰ በአምላክ ቸርነት
ውሃው ተለውጦ የወይን ጠጅ ሲሆን
በቃና ገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ከኖረ በመካከላችን
ሁሌ ይሰጠናል ይህን መሰል ወይን

## ደስ አላቸው

ደስ አላቸው ሙሽሪት ሙሽራው /2/
እግዚአብሔር ስለባረካቸው

ደስ አላቸው የልባቸው ምክር
›› የብቻቸው ምሥጢር
›› ዛሬ ተፈፅሟል
›› በቤተ ክርስቲያን
›› እሱ በፈቀደ
›› አገናኝቷቸዋል

ደስ አላቸው ቅዳሴው ሲቀደስ
›› ዝማሬው ሲዘመር
›› ሲባረኩ በአምላክ
›› ለዚህ ክብር በቅተው
›› ተክሊል ሲቀዳጁ
›› ቁርባን ተቀብለው

ደስ አላቸው ከዝሙት ጠብቆ
›› ከዓለም ፈተና
›› ወደ ቤቱ ጠርቶ
›› ለቅዱስ ጋብቻ
›› ስለመረጣቸው
›› የወንጌልን ቃል
›› በመፈጸማቸው

## ወንድና ሴት

ወንድና ሴት አርጎ እንደፈጠራቸው
ኋላም ለኑሯቸው ጋብቻን ሰጣቸው
አንዴ ከተጋቡ አንድ ሥጋ ናቸው
ከእንግዲህ ወደፊት ይጸናል ፍቅራቸው
ደስ ይበለን ሙሽሪት ሙሽራው /2/

አንድ አካል ሆነዋል አምላክ አጣምሯቸው
በምንም ምክንያት ምንም አይለያቸው
በጣም ይወዳታል በክብርት ሚስቱን
ስለሷ አሳልፎ ይሰጣል ነፍሱን

ለአብርሃም ለሣራ እንደሰጠ ትዳር
ለእናንተም ይለግስ የዘለዓለም ፍቅር
አንቺም እንደ ሣራ እርሱም እንደ አብርሃም
ተፋቅራችሁ ኑሩ እስከ ዘለዓለም

ለዚህ ላበቃችሁ ለቸሩ አምላካችን
ምሥጋና ይድረሰው ዛሬ ከሁላችን

በሉ ደህና ግቡ ወደ አዲስ ጎጆአችሁ
አምላክ በጥበቡ ፍቅርን ያብዛላችሁ

## ንሴብሆ

ንሴብሆ ለሥላሴ /2/
ክብር ተመስገን አምላከ ሙሴ /2/
የእኛ አማላጅ እናታችን
ነይ ነይ  ወደእኛ እመቤታችን
ፈጥነሽ ተገኚ በመሃላችን
ና ወደእና ሚካኤል /2/
መልአከ ምክሩ ለልዑል
ከእግራችን ይውደቅ ሳጥናኤል
ና ወደእኛ ገብርኤል /2/
ከእሳቱ አውጣን ከነበልባል
በክንፍህ ጥላ እንጠለል
ና ወደእኛ ዑራኤል /2/
እንደ ቅዱስ ዕዝራ ሱቱኤል
ጥበብን ስጠን ማስተዋል
ና ወሰእኛ በፈረስ
የልዳው ፀሐይ ጊዮርጊስ
ገድልህን ሰምተን እንፈወስ
ና ወደእኛ ተክለሃይማኖት /2/
ይጠብቀን የአንተ ጸሎት
ጸንተን እንድንቆም በሃይማኖት /2/

## ኅዳር 4

### ገሊላ እትዊ

እመቤቴ እስከ መቼ በባዕድ ሀገር ትኖሪያለሽ/2/
ገሊላ ግቢ/4/
አገርሽ ገሊላ ግቢ/2/
ገሊላ እትዊ/4/
አገረኪ ገሊላ እትዊ/2/
አ.ዝ -------------------//
እመቤቴ ማርያም ገሊላ እትዊ
ስደት ይበቃሻል ገሊላ እትዊ
ንጉሥ ሞቷል ብሎ ገሊላ እትዊ
ገብርኤል ነግሮሻል ገሊላ እትዊ
በእሳት ሠረገላ ገሊላ እትዊ
ሱራፌል ይመራሻል ገሊላ እትዊ
አ.ዝ -------------------//
የዝናቡ ጌታ ገሊላ እትዊ
እናት ሆነሽ ሳለ ገሊላ እትዊ
ሰይጣን በሰው አድሮ ገሊላ እትዊ
እያስከለከለ ገሊላ እትዊ
ውሃ ጥም ጸንቶብሽ ገሊላ እትዊ
አፍሽ ደርቆ ዋለ ገሊላ እትዊ
ይበቃል እናቴ ገሊላ እትዊ
እረሃብ ጥማትሽ ገሊላ እትዊ
ሂጂ ወደ ገሊላ ገሊላ እትዊ
ወደ ዘመዶችሽ ገሊላ እትዊ
አ.ዝ -------------------//
የሰማዕታት አክሊል ገሊላ እትዊ
የጻድቃን እናት ገሊላ እትዊ
ባርከሽ ሰጠሻቸው ገሊላ እትዊ
መከራ ስደትን ገሊላ እትዊ
እኛም ይታደለን ገሊላ እትዊ

የአንቺው በረከት ገሊላ እትዊ
አ.ዝ ------------------//
ገጽሽ ብሩህ መልካም ገሊላ እትዊ
ልክ እንደ ፀሐይ ገሊላ እትዊ
እግዝዕትነ ማርያም ገሊላ እትዊ
እሙ ለአዶናይ ገሊላ እትዊ
አይገባም ለአንቺ ገሊላ እትዊ
መከራና ስቃይ ገሊላ እትዊ

## ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል
ንዒ ሠናትየ ማርያም
ንዒ ንዒ ንዒ ንዒ
አመ አምላክ ንዒ ማርያም

## አክሊለ ጽጌ

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀጸላ መንግስቱ ለጊዮርጊስ /2/
ክበበ ጌራ ወርቅ /2/ አክሊለ ጽጌ /2/

## እስከ ማዕዜኑ

እስከ ማዕዜኑ እግዝእትየ ውስተ ምድረ ነኪር
ትሄልዊ /2/
ገሊላ እትዊ /4/ ሀገርኪ ገሊላ እትዊ /2/

## ኅዳር 18

### እልፍ አእላፋት

እልፍ አእላፋት ወትዕልፊት
ቅዱሳን ንጹሐን መላዕክት
ቆሙ ላገልግሉት ጸንተው ባንድነት
ቅዱስ /3/ አምላክ በማለት
አ.ዝ………//
ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት ሐገር
የሐይማኖት የፍቅር የምልክት ክብር
እውነት የታየብሽ የመላዕክት ክብር

አ.ዝ………//

እንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ

አ.ዝ………//

የሳጥናኤል ምኞት እንዳበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ እንዳበባ ረግፎ

አ.ዝ………//

ቅዱሳን መላእክት በእምነት
የፀናችሁ በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ
ስግደት ዘበ ጸጋ እንስገድላችሁ

## ገብርኤል ምልዕኒ

ገብርኤል ምልዕኒ መንፈሰ ልሳን
ለተናብቦ መንፈሰ ልሳን
ሞጣሕተ ብርሃን (2) ኸኸ
ዘይትገነብቦ ሞጣሕተ ብርሃን (2)

## ሐመልማላዊት

ሐመልማላዊት ሐመልማላዊት (2)
ሙሴ ዘርአያ (2)
በደብረ ሲና ማሕደረ ስብሃት (2)

## ጽላት ዘሙሴ ጽላት

ጽላት ዘሙሴ ጽላት (4)
ጽላት ዘሙሴ ጽላት (2)
ሙሴ ከፈጣሪው የተቀበላት
ዓሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉባት
ጽላት ዘሙሴ ጽላት
ይእቲ ዕፀ መድኀኒት (4) ማርያም ቅድሰት፤

## ንሴብሆ

ንሴብሆ ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
ንሴብሆ ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ 2 x አዝማች
ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልዘምር ማህሌት
ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
አዝማች..........................................
ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሃን
ግርማ ለብሶ አስገረመኝ የአምላኬ ዙፋን
ንሴብሆ ለአመላከ ዕዝራ
አዝማች...............................................
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ
እንዘምር
ዕልል እንበል በመስጋና ጸጋውን እንጀምር
ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
አእዋፉ በማለዳ መዝሙር ሲጀምሩ
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በሚስጢር ሲያወሩ
ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
አዝማች................................
ከበሮ ሆይ ጸናልናል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
ከበሮ ሆይ ጸናልናል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን መስጋና እናድርስ
ንሴብሆ ለአምላከ ዕዝራ
---- አዝማች ------

## ኅዳር 25

### ርግብዬ — Regbyie

| | |
|---|---|
| ርግብዬ (2) ማርያም እሙ ለእግዝየ<br>በቀለመ ወርቅ ጻፊ ስምዬ<br>በአምደ ብርሃን ጻፊ ስምዬ<br>በቀለመ ወርቅ ጻፊ ስምዬ<br><br>የተመረጥሽ ጌጤ (2) ሽልማቴ<br>የክብሬ አክሊል ነይ እመቤቴ ርግብየ<br>ወደ አንቺ እጮሀለሁ በቸገረኝ ጊዜ<br>አንድታስቀሪልኝ የልቤን ትካዜ ርግብየ<br>ርግብዬ.......................<br><br>የማትፈርሺ መቅደስ ንጽህይት አዳራሽ<br>የመለኮት እሳት በማህጸንሽ ያዝሽ ርግብዬ<br>የድህነቴ ምክንያት የሕይወቴ ፋና<br>የችግሬ ደራሽ ርህርህተ ሕሊና ርግብዬ<br>ርግብዬ............................<br><br>ስጠራ ስምሽን ከጠዋት እስከ ማታ<br>ፈጥነሽ ድረሽልኝ እንዳልገላታ ርግብዬ<br>የነቢያት ትንቢት የሰማእታት አክሊል<br>የጸሎት ማረጊያ የወርቅ መሰላል ርግብዬ<br>ርግብዬ.............................<br><br>ምርኩዝ መደገፊያ የሃይማኖት በትር<br>ሁነሽ የተገኘሽ የሕይወት ማህደር ርግብዬ<br>መንገዴ ጨልሞ ወድቄ እንዳልቀር<br>ደግፈሽ አሻግሪኝ ያንን የኃጢአት ባህር<br>ርግብዬ<br>ርግብዬ............................. | Regbuie /2/Maryam Emu leEgziye<br>Bekeleme werke tafi semye<br>Beamde brhan tafi smye<br>Bekelme werk tafi sme<br><br>Yetemeresh gieta gieta shlmata<br>Yekbri aklil neye embata rgbye<br>Wede anchi Echoalehu becegeren giza<br>Endtaskerln yelban tekazie regbye<br>Regbye.................<br>Yematfrshi mekdes netehit adarash<br>Yemelekot Esat bemahtensh yazsh<br>regbye<br>Yedhnetie meknyat yehyweta fana<br>Yechgra derash rhrhte hlina regbye<br>Regbye..........................<br>Setera smshn ketewat Eske mata<br>Fetnesh dershln Endalglata regbye<br>Yenebyat tenbit yesemahtat aklil<br>Yetelot maregiya yewrk meselal<br>regbye<br>Regbye.....................<br>Merkuz medgefiya yehaymanot beter<br>Hunesh yetegnsh yehywet mahder<br>regbye<br>Mengede chlmo wedke Endalker<br>Degfesh esagrin yanen yehatiat bahr<br>Regbye........................ |

## ስምህ በሁሉ

## Semh behulu

| | |
|---|---|
| ስምህ በሁሉ ተመሰገነ<br>ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ<br>አንተን ማወደስ ያስደስተናል<br>ስምህን ማክበር  ክብራችን ሆኖአል /2/<br>ስምህ............<br>አምላክ ተመስገን በሰማያት<br>ስምህ ይወደስ በፍጥረታት<br>ከህፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ<br>አንተን ማመስገን ይሁን የኛ ዕጣ /2/<br>ስምህ.........<br>በምግብ እጦት ብንሰቃይም<br>ማህሌትህን አናቋርጥም<br>የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም<br>እንዘምራለን ለአምላካችን ስም /2/<br>ስምህ.........<br>ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣ<br>ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም<br>ቸርነትህን እንጠብቃለን<br>ከአንተ ደጅ አምላክ የት እንሄዳለን /2<br>ስምህ.........<br>አምላክ ተመስገን በሰማያት<br>ስምህ ይወደስ በፍጥረታት<br>ከህፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ<br>አንተን ማመስገን ይሁን የኛ ዕጣ /2/<br>ስምህ......... | Semh behulu temesegene<br>Kekbr belay kebrh genene<br>Anten mawedes yasdestenal<br>Smhn makeber kbracn honoal<br><br>Semh .........<br>Amlak temesgen besemayat<br>Semh yewedes beftretat<br>Kehtanat afe mesgana yewta<br>Anten mamesgen yehun yena Eta /2/<br>Semh .........<br>Bemgb Etot bnsekaym<br>Mahliethn anakwartem<br>Yemekera dofe biwerdbnm<br>Enzemralen leamlakacne Semh /2/<br><br>Semh.........<br>Semay zenab demena biyaweta<br>Fekrh beEna weste alakuwretem<br>Cernethn Entebkalen<br>Keante dej amlak yet enhadalen/2/<br><br>Semh...............<br>Amlak temesgen besemayat<br>Semh yewedes beftretat<br>Kehtanat afe mesgana yewta<br>Anten mamesgen yehun yenaEta /2/<br>Semh............... |

### ንጹም ፆመ Ntum tome

| | |
|---|---|
| ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ /2/<br><u>ወንትፋቀር</u> /4/ በበይናቲነ | Ntum tome wenafker bitene /2/<br><u>Wnetfaker</u>/4/ bebeynatine |

### እግዚአብሔር ሀያል ነው Egziabhar melkam new

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ሃያል ነው የ ሚሳነ ው የለም<br>በዙፋኑ ፀንቶ ይኖራል ዘላለም<br>ማዕበሉን ከፍሎ ህዝቡን ያሻግራል<br>ለሰው የሚሳነው ለእርሱ ግን ይቻላል<br><br>ማዳንና ጥበብ ሀይል በእጁ ሆኖ<br>ለሰው የማይቻል ለእርሱ ቀሊል ሆኖ<br>ፈጥኖ ይጎበኛል የምስኪኑን ጓዳ<br>ፈፅሞ አይዘገይም ጌታ ሲሰናዳ<br><br>አንዱን እየሻረ አንዱን እየሾመ<br>የተዋረደውን ክብር እየሸለመ<br>ከኋላ ያለውን ከፊት አሳልፎ<br>በጎ ቀን ያመጣል ጨለማውን ገፎ<br>እንደ ቋጥኝ ቢከብድ የህይወት ፈተና<br>ሰውን የሚያፀና አምላክ አለንና<br>ደስ ያሰኛል እርሱ መከራን አጥፍቶ<br>ታግሶ የቆመ ማን አፈረ ከቶ<br>የሚያስፈራ ጊዜ ቢመጣ ክፉ ቀን<br>እናልፋለን እኛ እግዚአብሔርን ይዘን<br>ወራት ከብዶባችሁ ያጎነበሳችሁ<br>ታሪክ ሆኖ ያልፋል እግዚአብሔር ሲያያችሁ | Egziabhar melkam new yemisanew yelem<br>Bezufanu tento yenoral zelalem<br>Maeblun keflo hezbun yasagral<br>Lesew yemisanew leErsu gen yecalale<br><br>Madanena Tebeb hailen beEju hono<br>Lesew yemeychal leErsu kelil hono<br>Fetno yegobenal yemskinun guwada<br>Fetmo ayezegeym gieta sisenadda<br><br>Andun Eyesare andun Eyesom<br>Yetewaredewn kbr Eyeshleme<br>Kewala yalewen kefit asalfo<br>Bego ken yametal chlemawn gefo<br><br>Ende kuwatn bikebd yehywet fetena<br>Sewn yemiyatena amlak alena<br>Dese yasenal Ersu mekeran atfto<br>Tagso yekom man agre keto<br><br>Yemiyasfera gizie bmeta kefu ken<br>Enalfalen ena Egziabharn yezen<br>Werat kebedo bachu yanebaesachu<br>Tarik hono Egziebher siyaayachu |

## እስመ አልቦ ነገር

እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር /2/

እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር /2/

አልቦ ነገር /3/ ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር

መካኒቱን ወላድ አንተ ታደርጋለህ

ከጭንጫ አለት ላይ ውኃን ታፈልቃለህ

በወጀብ መካከል አንተ መንገድ አለህ

የአስጨናቂዎችን ክንድ ትሰብራለህ      አዝ - - -

ለሶምሶን ብርታቱን የሰጠኸው ጽናት

በጠላቶቹ ፊት ሞገስ የሆንክለት

የእጅህን በረከት ከአርያም ላክልኝ

ፊትህን አብራልኝ እኔም ድናለሁኝ

አዝ - - -

የኤርትራ ባሕር ከፊት ተዘርግቶ

የፈርዖን ሠራዊት ከኋላችን መጥቶ

ዋይታ ሲበረታ ሙሴን ተናገርከው

ባሕር ተከፈለ ሕዝቡን አሻገርከው      አዝ - - -

ሰማያት ደመናን ከቶ ባይቋጥሩ

ከብቶችም ከበረት ከጋጣ ባይኖሩ

ሸለቆን በውኃ ቤትን በበረከት

መሙላት ያውቅበታል የዘላለም አባት      አዝ - -

## ሐመልማላዊት

ሐመልማላዊት ሐመልማላዊት (2)

ሙሴ ዘርአያ (2)

በደብረ ሲና ማሕደረ ስብሃት (2)

## ተክለ ሀይማኖት

ተክለ ሀይማኖት የአለም ብርሃን ናቸው

ይኸው ለዘላለም ያበራል ስራቸው /2/

## ታህሳስ 02

### ልዑል ሠምራ

ልዑል ሠምራ ዳዊት ዘመራ (2)

በቤተ መቅደስ ተወክፍዋ (2)

ልዑል ወደዳት ዳዊትም አመሰገናት

በቤተ መቅደስ ተቀበሏት /2/

### እያቄም ወሃና

እያቄም ወሐና አባት እናትሽ (2)

ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ

መና ከደመና ወረደልሽ

ዕፁብ ድንቅ ጽዮን ማርያም አንቺ ነሽ

ኦ እመ ክርስቶስ ድንግል አንቺ ነሽ

ኦ ወላዲተ አምላክ ማርያም አንቺ ነሽ፤

### ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቀረብ ይሻለኛል (2)

መታመኛዬ እሱ ነውና ይገባዋል ክብርና

ምሥጋና

ፍቅሩን እያሰብን እንቅረብ ወደ እርሱ

ይምረናልና መሐሪ ነው እርሱ

በልባችን ይንገሥ ይግባ ከቤታችን

የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን

የቤታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን

.........አዝ..........

ከቶ አላገኝም እሱን የሚመስል

ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ኃይል

በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ

ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ (2)

.........አዝ..........

የለመለመ መስክ መሸሸጊያየ ነው

በሰላም ወጥቼ ሰላም እገባለሁ

ተስፋየ እርሱ ነው ይመራኛልና

ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምሥጋና

ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና

.........አዝ..........

ለእኔስ ይሻለኛል መቅረብ ወደ ጌታ

ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ

ስለዚህ እቀርባለሁ አልቀርም ከደጁ

ጠግቤ እኖራለሁ ከበረከት እጁ (2)

.........አዝ..........

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቀረብ ይሻለኛል (2)

መታመኛዬ እሱ ነውና ይገባዋል ክብርና

ምሥጋና

## ታህሳስ 9

## አርሴማ

### ነአምን በአብ

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ

ወነአምን /4/ ነአምን በመንፈስ ቅዱስ

እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ

እናምናለን /4/ እናምናለን በመንፈስ ቅዱስ

### ይርድዓነ

ይርድዓነ አምላክነ አምላክ ነ ወመድኃኒነ /2/

አምላከነሰ አምላከ አድኅኖ ስብሀት ለአብ

ስብሀት ለወልድ  ስብሀት ለመንፈስ ቅዱስ/2/

## አትተወኝ አትጣለኝ

አትተወኝ አትጣለኝ (4)

ወድቄያለሁና ጌታ ሆይ አንሣኝ (2)

ቸሩ መድኀኒቴ የአልዓዛር ቤት ራት

የኑሮዬ ጣዕም የሕይወቴ መብራት

በኃጢአት ጭቃ ላይ ወድቄያለሁና

ጌታዬ ሆይ አንሣኝ እጅህን ዘርጋና (2)

የሰጠኸኝ ክብር የልጅነት ሥልጣን

እንደ ሶምሶን ዝሙት ከደሊላ ጋራ

እርቃኔን ቀረሁኝ ተላልፌ ሕግህን

አምላኬ ዘርጋልኝ የምሕረት እጅህን (2)

ዘወትር እየበደልኩ ከሕግህ እርቄ

በኃጢአት ጭቃ ላይ ክፉኛ ወድቄ

በበደል እ ራት ተይዣለሁና

አባቴ ሆይ ማረኝ መሐሪ ነህና (2)

## ታህሳስ 23

### አባ አቡነ

አባ አቡነ አባ መምህርነ /2/ አባ ተክለ ሀይማኖት /2/

እምዓእላፍ ህሩይ/2/ ተክለሀይማኖት

### የእቲሳ አንበሳ

የእቲሳ አንበሳ ተክልዬ ተነሳ

ወገንክን ታደገው ከሃጥያት አበሳ

ተኩላው ለምድ ለብሶ በርግጥ መጥቷልና

ጴጥሮስ ሆይ ዝም አትበል እንደጥንቱ ቅና

ዮሐንስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና

የዓለም ምንምንቴ የተባልከው ቅዱስ

የዋሁ መኖክሴ አባ ሕርያቆስ

ቅዳሴ ማርያምን ናና ዛሬ ቀድስ

በእጣኑ መአዛ ደውያንን ፈውስ /2/

የእቲሳ አንበሳ...........

የወንጌል አንበሳ ጎርጎርዮስ ፍጠን

ምሰሶ ሳይውድቅ መንጋው ሳይበተን

መብርቁ አትናቴዎ ሞገዱ ገስፀው

አፈ ጉባኤያችንን በመስቀሉ ዳኘው /2/

የእቲሳ አንበሳ...............

መርከቧን የሚያውክ ነፋስ መጥቷልና

አምላካችን ፈጥነህ አድነን ቶሎ ና

ጴጥሮስ ሆይ ቀስቅሰው ልንጠፋ ነው ብለህ

ሞገዱ እያየለ ዝም እንዳይል ጌታ /2/

የእቲሳ አንበሳ.............

ከሳቴ ብርሃን ሰላማ ቶሎ ና

ኖላዊ እረኛ ያስፈልግልና

ሥጋውን የጎዳ ነፍሱ የጠቀመ

ነውር ጉድፍ የሌለው ክብሩ የታረመ /2/

የእቲሳ አንበሳ ...............

## ጊዮርጊስ ሀያል

ጊዮርጊስ ሀያል ሀያል ወመስተጋድል

ጊዮርጊስ ሀያል ሀያል ወመስተጋድል

ገባሪ ተዐምር (2) ኮከበ ግብር

## ገድልከ ግሩም

ገድልከ ግሩም ነገርከ ጥዑም /፪/

ጊዮርጊስ ኃያል እንቊ ስም ቅረበነ/፫/ በሠላም /፪/

## ታህሳስ 30

### ሣር ቅጠሉ ሰርዶው

ሣር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንባሌጥ ቄጤማው

በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም የነበረው (2)

በልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው

ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው፤

እልል በይ ቤተ ልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ

የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)

ያ ትሁት እረኛ የትህትና አባት

ብርሃን የለበሰው በእኩለ ሌሊት

ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ ሠራዊት

ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት፤

እልል በይ ቤተ ልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ

የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)

እረኝነት ታናሽ የወራዳ ግብር

ብሎ ሰው በግምት ደንግጎት የነበር

የብዙ ሰው ራሱ መሆኑን እረኛ

ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ፤

እልል በይ ቤተ ልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ

የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ (2)

### እምሰማያት ወረደ

እምሰማያት ወረደ ወእምማርያም 'ተወልደ'(2)

ከመ ይኩን ቤዛ (2)

ለኩሉ ዓለም ለብሰ ስጋ ማርያም (2)

ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ (2)

እንዲሆነን ቤዛ (2)

ለዓለሙ ሁሉ ለበሰ የማርያምን ስጋ /2/

### አይኖቼ ማዳኑን

ዓይኖቼ ማዳኑን አይተዋልና /2/

ይገባዋል /2/ ክብርና ምስጋና

አ.ዝ .................

ከሰማይ ወረደ ሰውን በማፍቀር

ኃያሉ ጌታችን ቸሩ እግዚአበሔር

በቤተልሔም ዋሻ በዚያ በግርግም

ተወለደ ዛሬ መድኃኔዓለም

አ.ዝ .................

የተነበዩለት ብዙ ነብያት

ከድንግል ተወልዶ አዳነን በእውነት

ከበደል ጉራንጉን አነሳን ከትቢያ

በአንድነት እንዘምር እንበል ሃሌ ሎያ

አ.ዝ .................

የተናቅን ሰንሆን እኛን ሊያከብር ወዶ

በፍቅር አከበረን እራሱን አዋርዶ

ምን ዓይነት ፍቅር ነው ፍጹም ምህረት

የአምላክ መወለድ በከብቶች በረት

አ.ዝ .................

በንጽህና ጸንተሽ ቤተመቅደስ የኖርሽ

በኀቱም ድንግልና መድኃኒትን ወለድሽ

የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ ጌታ

ተወልዷል ከድንግል የሰዎች አለኝታ

## በቤተልሔም

በቤተልሔም ተወልደ /2/ አማኑኤል

እም ዘርዓ ዳዊት /4/ተወልደ አማኑኤል/2/

## ጥር 7

### የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት

ድንግልን ከመሃል ሚካኤልን ከፊት

ኣእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት

እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት (2)

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት

ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ሥሉስ ሲሉ

ይህን ልዩ ክብር ሊያዩ የታደሉ

በጽድቅ ሥራቸው በምድር ይታያሉ .........አዝ.......

የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር

ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር

ፍቅርና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ (2)

.........አዝ.........

የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር

ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር

ፍቅርና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ (2

## ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመስግኑ ሥላሴን አመስግኑ

የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ (2)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ምሥጋና ይገባል ከምንም በፊት

ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረው ጌታ

ምሥጋና ይገባል ከጥዋት እስከ ማታ

..........አዝ........

ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑህ

መላእክት በሰማይ ሚዘምሩልህ

እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን

በሰማይ በምድር እንጠራሃለን

.........አዝ.......

ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ

ብተማም በአምላኬ እረካለሁኝ

ሥላሴ አምባዬ ክብሬም ናቸውና

ሁሌ ይመሩኛል በሕይወት ጐዳና፡

..........አዝ........

ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ

ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ

ሥላሴ አምባዬ ክብሬም ናቸውና

ሁሌ ይመሩኛል በሕይወት ጐዳና

## ተወልደ

ተወልደ ኢየሱስ 'በቤተልሔም'(2)

ዘይሁዳ በቤተልሔም:(2)

አዋልደ ጢሮስ 'አሜሃ ይሰግዳ'(2) በቤተልሔም:(2)

## ዘሰማየ ገብረ

ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድረ ሣረረ (፪)

አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ (፬)

ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና (፪)

ኃያል አምላክ ሕያው ጌታ ያለርሱ ማን አለና (፪)

ዘዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድረ ሣረረ (፪)

አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ (፬)

## ጥር 21

### ሞትሰ

ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ

ሞታ ለማርያም የዐጽብ ለኵሉ»

ሞት ለሚሞት /ለሟች/ ይገባል

የማርያም ሞት ግን ሁሉን ያስደንቃል

### በሰላም ነዒ

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም /2/

ምስለ ወልድኪ አማኑኤል

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም

ስለ ሚካኤል ወገብርኤል

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም

ምስለ ሱራፌ ወኪሩቤል

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም

ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን

በሰላም ነዒ ነዒ ማርያም

ትናዘዘኒ ሀዘነ ልብዬ

## ወዳጄ ሆይ

ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ

የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለብሽ

የተዘጋጅ መቅደስ ንጽህት አዳራሽ

ሕዝቅኤል ያየሽ የምስራቋ በር

ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር

የልዑል ማደረያ አማናዊት መቅደስ

ስለ ንጽህናሽ ምስጋናን እናድርስ

ወዳጄ ሆይ........................

ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል

ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል

ያለ ዘርዐ ብዕሲ በኅቱም ድንግልና

አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና

ወዳጄ ሆይ........................

ምስራቀ ምስራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ

ጨረቃን የምትመስይ ፀሀይን የወለድሽ

የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ

ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሽሺ

ወዳጄ ሆይ........................

## እግዚአብሔር እረኛዬ ነው

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል

በእረፍት ውሃ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል

## አማኑኤል ጌታዬ

አማኑኤል ጌታዬ ሆይ በምህረትህ ተቀበለኝ

ሀጥያት እኔ ልጅህን ዳግም እንዳይገዛኝ

ሀይልህን አንተ አልብሰኝ ....

## ጥር 29

## አማኑኤል ናና

አማኑኤል ናና መድኃኔዓለም ናና አማኑኤል ናና

በቀኝህ ለመቆም እንሻለንና አማልኑኤል ናና

እግዝ አብሔር አምላክ አማኑኤል ናና

በገሀድ ይመጣል መድኃኔዓለም ናና

የሚያቃጥል እሳት አማኑኤል ናና

በፊቱ ይነዳል መድኃኔዓለም ናና

ፍሬ እና ገለባን አማኑኤል ናና

በሥልጣኑ ይለያል መድኃኔዓለም ናና

...............አዝ............

ጌታ ስትመጣ አማኑኤል ናና

በሚያስፈራ ግርማ መድኃኔዓለም ናና

መላእክት ሲሰግዱ አማኑኤል ናና

ከሰማይ ከራማ መድኃኔዓለም ናና

ማነው የሚቆመው አማኑኤል ናና

ከጻድቃን ከተማ መድኃኔዓለም ናና

...............አዝ............ ለአንተ የሚያስደስት

አማኑኤል ናና ምግባርን ሳልሰራ መድኃኔዓለም ናና

ምን ትመልስ ይሆን አማኑኤል ናና

ነፍሴ ስትጠራ            መድኃኔዓለም ናና

……………አዝ…………

ኮናኔው በርትዕ ነህ      አማኑኤል ናና

ፈታሄ በጽድቅ           መድኃኔዓለም ናና

ባለጸጋ ድሀ             አማኑኤል ናና

ብለህ የማትንቅ          መድኃኔዓለም ናና

ቸርነትህ ይርዳኝ         አማኑኤል ናና

ሲያል እንዳልወድቅ     መድኃኔዓለም ናና

……………አዝ…………

ትናፍቀኛለች            አማኑኤል ናና

መንግሥተ ሰማያት     መድኃኔዓለም ናና

ዘለዓለም በሙሉ        አማኑኤል ናና

ሰላም ያለባት            መድኃኔዓለም ናና

ከእመብርሀን ጋር        አማኑኤል ናና

የምኖርባት              መድኃኔዓለም ናና

## አድነነ እግዚኦጤና አልባ ፆም

አድነነ እግዚኦ አድነነ አምላክነ

ዘ አድሀንካ ለነነዌ ሀገር  በትንብልና

ትንብልና ሳህል

## የካቲት 5

### ጼና አልባሲሆ

ጼና አልባሲሆ /2/ ለገበረ መንፈስ ቅዱስ

ከመጼና ጽሂን

አልባሲሆ ዘሜላት ዘወረደ ውስተ ገነት

### ንጹም ፆመ

ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጾነ

ወንትፋቀር /4/ በበይናቲነ

ጾምን እንጹም፤ ወንድማችንን እንውደድ፤

እርስ በርስም እንዋደድ

### አድነነ እግዚኦ ፆም

አድነነ እግዚኦ አድነነ አምላክነ

ዘ አድሀንካ ለነነዌ ሀገር  በትንብልና

ትንብልና ሳህል

### ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው

ይኸው ለዘላለም ያበራል ስራቸው /2/

### ጾም ጸሎታችን

ጾም ጸሎታችንን ተቀበልልን (2)

አንተን ደስ የሚያሰኝ ይሁንልን(4)እኽ

## የካቲት 12

### ሕይወቴ ቢመራ — Hywetie bimera

| | |
|---|---|
| ሕይወቴ ቢመራ ጌታ በቃልህ<br>ጣፋጭ ይሆን ነበር ሲያድሰኝ ፍቅርህ<br>ያንተ ጸጋ ጌታ ስለበዛልኝ<br>ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ<br>በሕይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ<br>በወንጌል ማመኜ /2/<br>ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ<br>ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ<br>ምን አይነት መውደድ ነው ለኔ አንተ ያለህ<br>ምን ይከፈለዋል ለፍጹሙ ፍቅርህ<br>በሕይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ<br>በወንጌል ማመኔ /2/<br>ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለኔ ያለህ<br>ምን ይከፈለዋል ለፍጹሙ ፍቅርህ<br>ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት<br>ቃልህን ልጠብቅ በፍጹም ፍርሃት<br>በሕይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ<br>በወንጌል ማመኔ /2/ | Hywete bimera gieta bekalhe<br>Tafach yehon neber siyadsen fekreh<br>Yante tega gieta slebezaln<br>Chlemaw tegefo berhanh meran<br><br>Behywetie ...................<br>Wediet ehadalhu yejhe tebabe hone<br>Fekrh Eyadesen motehln denie<br>Men aynete mewdade new lenie ante yaleh<br>Men yekefelewal lefxumu fekreh<br><br>Behywetie ................<br>Men aynet mewded new ante lena yalh<br>Men ykfelewal leftumu fekreh<br>Dejh lay tateya dejh lay lemut<br>Kalhn letebeke beftum ferhat<br>Behywetie ............................ |

### ጾም ጸሎታችን

ጾም ጸሎታችን ተቀበልልን (2)

ደስ የሚያሰኝህ ይሁንልን (2) እኽ/

እንዳንሸነፍ ኃይልህን (2)

አፍሮ ይመለስ ይውደቅ ሰይጣን (2) እኽ/

አምላካችን ሆይ ይቅርታህ ስጠን

ምሕረትህ ይብዛ በሁላችን (2) እኽ

## መመኪያዬ አንተ ነህ

መመኪያዬ አንተ ነህ የነፍሴ መዳኛ

ተመልከት ወደኔ አትስጠኝ ለዳኛ

ሕይወቴን ላንተ (2) ብያለሁ

አምላክ የኔ ጌታ የት አገኝሀለሁ

ከበደሌም አንጻኝ ደግሞም ከሀጥያቴ

በመንፈስ ይታደስ መላው ሰውነቴ

ሕይወቴን ላንተ.....................

አቀበቱ ልቤ ከጫንጫ ትዕቢት

አሸብርቆ ነበር አይፈርስ መስሎት

ሕይወቴን ላንተ.....................

የጾም ንጉስ መምጣት ስለተነገረ

መደልደል አለበት እየተሰበረ

ሕይወቴን ላንተ.....................

ሶስናን ያዳንካት ከሀሰት ምስክር

እኔንም አዳንኝ ካልታሰበ ነገር

ሕይወቴን ላንተ............

## የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ /፪/

ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/፪/

የሐስት ምስክር አቁመው ከሰሱት /፪/

በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/፪/

ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ/፪/

ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተፋቅሮ/፪/

ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /፪/

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ /፪/

በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ /፪/

በችንካር ላይ ቆመው ምንም ሳይሰለቹ /፪/

የብርሃን አክሊልን ለሰማእት ያደለ/፪/

የሾክ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /፪/

## የካቲት 26

### እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው

በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው (2)

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን

ሞት ነግሶበት ሳለ በኛ በሁላችን

ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው

በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው (2)

እግዚአብሔር መልካም ....................

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት

ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት

በተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት

እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት (2)

እግዚአብሔር መልካም ...................

በሃዘን በችግር በመከራ ጊዜ

ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ

የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ

እግዚአብሔር መልካም ነው ሀዘኔን አስረሳኝ

የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ

ክርስቶስ እየሱስ ሀዘኔን አስረሳኝ

እግዚአብሔር መልካም ....................

## ድንግል የዚያን ጊዜ

ድንግል የዚያን ጊዜ (2) ኃዘንሽ በረታ

በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ (2)

የግፍ ግፍ ደርሶበት የዚያን ጊዜ ተጠማሁ ሲልሽ

ለውሻ ያጠጣሽ በውርቅ ጫማሽ (2)

ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ ራርቶ ልብሽ

ለፍጡር በማዘን ውኃ ያጠጣ (2)

ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ ሲናገር ልጅሽ

ታዲያ እንደምን ቻለው ወላድ አንጀትሽ (2)

እንደዚ ስታለቅሽ ዚያን ጊዜ ኃዘን ሲውጥሽ

እነማን ነበሩ አስተዛዘኑሽ (2)

ስታለቅሽ በማየት የዚያነረ ጊዜ ራረቶ ልጅሽ

ዮሐንስን አጽናኝ እንደ ልጅ ሰጠሽ (2)

## በመከራ ጽና

## Bemekera tena

| | |
|---|---|
| በመከራ ጽና በፈተና ጽና<br>ለጊዜው ነው እንጂ ሁሉም ያልፋልና<br>እዮብ ተጨነቀ በጣም ተማረረ<br>በመከራው ብዛት ትዕግስትን ተማረ<br>ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱንም<br>በመከራ ጸና አልካደም አምላኩን<br>በመከራ ጽና.................<br><br>መፈተን መልካም ነው ያንጻል እንደወርቅ<br>በመጨረሻው ቀን በክብር እንድትደምቅ<br>አንዱን ሳትሻገር ሌላው ቢተካብህ<br>በሕይወትህ ዘመን ፈተና  ቢያጠቃህ<br>በመከራ ጽና.................<br>ከአምላክህ ተስማማ እራስህን አዋርድ<br>በቃሉ ተመራ እንድፈቃዱ ሂድ<br>ዋጋህ በአምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና<br>በርታ ክርስቲያን ሆይ በፈተና ጽና | Bemeker tena befetena tena<br>Legiziew new Enji hulum yalfalena<br>Eyaob techneke betam temarere<br>Bemekeraw bezat tegsten temare<br>Lej yelelew hone ata nbretunm<br>Bemekera tena alkadem emlakun<br>Bemekera tena.............<br>Mefeten melkam new yanetal endewerk<br>Bemechresaw ken bekbr Endtedemke<br>Andun satshger lilaw bitekabeh<br>Behyweth zemen fetena biyatekah<br>Bemekera tena.............<br>Keamlakh tesamama erashn award<br>Bekalu temera Endefekadu hid<br>Wagah beamlakh Zend besemay alena<br>Berta krstiyan hoy befetena tena |

## እንዘ ይብሉ

## Enze yeblu

| | |
|---|---|
| እንዘ ይብሉ የዜምሩ በልሳነ ዘኢያረምም (2)<br>መንግስተ ሥላሴ ዘለዓለም (4)<br>የማያቋርጥ አንደበት እንዲህ እያሉ<br>ያመሰግናሉ የስላሴ መንግስት ዘላለማዊ ነው | Enze yeblu yezemru belsan zeiyarememe/2/<br>Mengste selase zelealeme/4/<br>Yemayakwart andebet Endih Eyalu yamesegnalu/2/<br>Yeselase mengst zelalemawi new/2/ |

## አልፋና ኦሜጋ

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ

በከሐዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ

ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ

እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ

ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ

ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ

ቅድሳት እጆችህ የፊጥኝ ታስረው

እንደበግ ተጎተትህ ብትምራቸው

የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ

ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ

በአውደ ምኩራብ ከጲላጦስ ዘንድ

አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ

ከሐና ቀያፋ ከመሳፍንቱ ደጅ

ከነሔሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ

ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ

በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ

ሳዶርና አላዶር ዳናትና አዴራ

ተፈልገው መጡ ለችንካር በተራ

አምስቱ ችንካሮች ቅንዋት መስቀል

ወገኖችህ መጡ ሥጋህን ለማቁሰል

የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ

ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ

ምራቅ ተፋብህ ራስክን ሊጎዱ

ግፈኞች አይሁዶች ባንተ ላይ ቀለ

## መጋቢት 3

## እኔስ በምግባሬ ENES BEMGBARIE

| | |
|---|---|
| እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ<br>እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ (2)<br>ያንን የእሳት ባህር እንዳላይ አደራ<br>ድረሽኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ (2)<br>አዝ...<br>የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና<br>የናሆም መድኃኒት ንዒ በደመና (2)<br>አዝ...<br>አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ<br>የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ (2)<br>አዝ...<br>አፈሳለሁ እምባ በጣም ተጨንቄ<br>እማፀንሻለሁ በደሌን አውቄ (2)<br>እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ<br>እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ (2) | Enes bemgbarie dekama honalhu<br>Ezeniln dngl elemnsahlhu /2/<br>Yanen yeast bahr endalay edera<br>Dreshln dngl smshn stera /2/<br>Enas bemgbarie dekama............<br>Yedawit mesenko ye Elyas mena<br>YeNahom medhanet neye bedemena/2/<br>Enas bemegbare dekama...................<br>Anci neshe gulbetie bedekemen gizie<br>Yelba metna eredat mrkuzie /2/<br>Enas bemegbare dekama...................<br><br>Afesalhu emba betam technke<br>Ematensalhu bedelien awqie /2/<br>Enas bemegbare dekama...................<br>Enies bemgbarie dekama honalhu<br>Ezeniln dngl elmnshalhu /2/ |

## ዓለምን ለማዳን ALEMN LEMADAN

| | |
|---|---|
| ዓለምን ለማዳን የተሰቀለው<br>እየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው<br><br>ጌታችን ተሰቅሎ ሲያዩት መላዕክት በ<br>ዝማሬ ፈንታ አለቀሱለት<br>ሚካኤል ዝም አለ ገብርኤል ገረመው<br>አምላኩን እርቃኑን ተሰቅሎ ስላየው/2/<br><br>አዝ (ዓለምን ለማዳን)<br><br>ነፍሱን ለወዳጁ የሚሰጥ ቢገኝም<br>ለጠላቱ የሚሞት በጭራሽ አይኖርም<br>ጠላቶቹ ሳለን ለእኛ የሞተው<br>ክርስቶስ ልዩ ነው ወደር የሌለው /2/<br><br>አዝ<br><br>እውርን ቢያበራ የሞተን ቢያነሳ<br>በመመስገን ፈንታ ሆነበት አበሳ<br>ሰማያዊው ዳኛ ሊፈረድበት<br>ተከሶ ቀረበ ከጲላጦስ ፊት /2/<br><br>.......አዝ ....<br><br>የጸሎተ ሐሙስ ዕለት እራት የሆነው<br>አርብ በመስቀል ላይ የተሰቀለው<br>ፍቅር አስገድዶት ለእኛ የሞተው<br>መልካሙ እረኛችን መድሃኒዓለም ነው<br>/2/ | Alemn lemadan yetesekelew<br>Eyesus krestos Egziabhar new<br><br>Gietacn teseklo siyayut melaEkt<br>Bezmarie fenta eleqeshulet<br>Mikaiel zme ale gebriel geremew<br>Amlakun Erkanun teseklo<br>slayew/2/<br><br>Alemn lemadan....................<br><br>Nefsun lewdaju yemiset bignm<br>Letelatu yemimot betrash aynorm<br>Telatocu salen lena yemotew<br>Krstose leyu new weder yelilew/2/<br><br>Alemn lemadan....................<br><br>Ewrn biyabera yemoten byanesa<br>Bememesgen fenta honebet<br>ebesa<br>Semayawiw dana liferdbet<br>Tekeso kerbe kplatos fit /2/ |

## መጋቢት 10 ደብረ ዘይት

### አቤት የዚያን ጊዜ — Abetyezian gizie

| | |
|---|---|
| አቤት የዚያን ጊዜ ክርስቶስ ሲመጣ (2)<br>ትንሹም ትልቁም (3) መድረሻውን ሲያጣ፤<br>ከምስራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ (2)<br>አየራት ሲላኩ (3) ማአትን ለማዝነብ፤<br>ሰማይና ምድር በአንድ ሲወሐዱ (2)<br>የት ይሆን መድረሻው (3) የት ይሆን መንገዱ<br>...አዝ...<br><br>ጻድቃን በቀኝ በኩል ሃጥአን በግራ (2)<br>ሲነፋ መለከት (3) ሲደለቅ ዕንዚራ፤<br>ምድር ቀውጢ ስትሆን አጽም ሲሰበሰብ (2)<br>ሐፍረት ይይዘዋል (3) ሰው ለፍርድ ሲቀርብ<br>....አዝ...<br><br>ጨኸት ሲበረታ የማይጠቅም ለቅሶ (2)<br>እንደ ቍራ ጠቁሮ/3/ ጽልመትን ተላብሶ፤<br>ገነትን ሲያገኙ ጻድቃን በስራቸው (2)<br>ኃጥአን ወደ ሲኦል/3/ ተፈረደባቸው።<br>....አዝ... | Abet yezian gizzie kerstos simet /2/<br>Tnshum tlqum /3/ medresawn syata<br><br>Kemsraq kemerab kesemien kedebub /2/<br>Ayerat silaku /3/ meatn lmazneb<br>Semayna medr beand siwahdu /2/<br>Ytyhon mdereshaw /3/yetyhohon mengdu<br><br>Tadqan bene bekul hatan begra /2/<br>Senfa mlket /3/ sidelk Enzirra<br>Mdre kewTi sthonn atm sisbesb /2/<br>Hfret yeyezewal /3/sew lefrd sekrb<br><br>Tadkan bekn bekul hatan begra /2/<br>Sinefa meleket /3/ sidlek Enzira<br>Mder kewti sthon atem sisebeseb /2/<br>Hfrer yeyezewal /2/ sew lefrd sikerb<br><br>Chuet  sibereta yemayTekm lekso /2/<br>Ende kura tekro /3/ telmetn telabso<br>Genetn siyagnu tadqan besracew /2/<br>Hatan wede siol/3/ teferedebacew |

## ከመላእክት ጋራ

ከመላእክት ጋራ ሲገለጽ በሰማይ፤

ፀንተን እንጠብቀው ክብሩን ሁሉ እንድናይ፤

በግርማ ሲመጣ ባስደንጋጭ ሁኔታ፤

ውዮልሽ ነፈሴ ሆይ ወዮ የዛን ለታ

እኸ ምስጋና ይድረስህ ሁል ጊዜ ጧት ማታ

ሃሌ ሃሌ ሉያ የሠራዊት ጌታ

ሰማይና ምድር ከፊቱ ሲሸሹ፤

ወዴት ልግባ ይላል ትልቁ ትንሹ፤

ጻድቃን ሲደሰቱ የሃጥአን ፋንታ፤

ሆኖ ጠበቃቸው ልቅሶና ዋይታ፤

እኸ ምስጋና ይድረስህ ሁል ጊዜ ጧት ማታ፤

ሃሌ ሃሌ ሉያ የሠራዊት ጌታ፤

ስለማይታወቅ አምላክ አመጣጥህ፤

በመንፈስህ አፅናን ፀንተን እንጠብቅህ፤

ሰይጣን እንዳይገዛን በመንግሥት ቦታ፤

እግዚኦ ከልለን ከልቅሶ ከዋይታ።

እኸ ምስጋና ይድረስህ ሁል ጊዜ ጧት ማታ፤

ሃሌ ሃሌ ሉያ የሠራዊት ጌታ፤

## ተወልዳለች Tewldalech

| ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መድኃኒት<br>እናመስግናት እናወድሳት እንውደዳት/2/<br>የአዳምን ሕይወት/2/ | Teweldalcna yegeta enat yena medhnit<br>Enamesgnat enawdsat enwdedat /2/<br>Yeadamn Hywet /2/ |
|---|---|

## ጌታ ተነስቷል Gieta tenestwal

| ጌታ ተነስቷል እልል እልል በሉ<br>አምላክ ተነስቷል የምስራች በሉ<br>ሙስና መቃብርን በኃይሉ አጥፍቶ<br>ሁላችን አየነው ክርስቶስ ተነስቶ<br><br>አዳምን ለማዳን ቃል ኪዳን ገብቶለት<br>ዘመኑን ጠብቆ ካሣ ሊከፍልለት<br>ከሰማያት ወርዶየ ተሰቀለው<br>ሞትን በሞት ሽሮ ይኸው አየነው<br>ደቀ መዛሙርቱ እጅጉን ተጨንቀው<br>በጌታቸው መሞት በኃዘን ተመተው<br>በተዘጋ ደጃፍ ተሰብስበው ሳለ<br>እጆቹን ዘርግቶ ሰላም ለእናንተ አለ<br><br>ማርያም መግደላዊት እየገሰገሰች<br>በሌሊት ተነስታ ወደ አምላኳ ሄደች<br>አይሁድ አንገላተው የሰቀሉት ጌታ<br>ተነስቶ አግኝታው ተመላች በደስታ | Geta tenestwal elele elele belu<br>Amlak tenestwal yemsrac belu<br>Musna mekabrn behylu atfto<br>Hulacn ayenew kerstos teneseto<br><br>Adamn lemadan kale kidan<br>gebtolet zemenun tebeko kasa<br>likflelat<br>Kesmayat werdo yetesekelew<br>Motn bemot shro yhew ayenew<br><br>Deke mezamurtu ejgun technkew<br>Begetacew memot behzn temtew<br>Betezega dejaf tesebsbew sale<br>Ejocun zergto selam leEnante ale<br><br>Maryam megdelawit Eyegsegsec<br>Belielit tenesta wede emlakwa hedec<br>Ayyhud engelatew yeseqlut gieta<br>Tenesto agntaw temelach bedesta |
|---|---|

## አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ

## Amlak hoy wedena

| | |
|---|---|
| አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ ለብሰህ<br>የማርያምን ሥጋ/2/<br>ባክኖ የነበረው የአዳም ዘር ውጤቱ ነበር<br>የሚያሰጋ/2/<br><br>በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን<br>ድህትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ /2/<br>ምን የበዛ ነበር ትህትናህ ትዕግስትህ<br>የማይለወጥ/2/<br><br>የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጎንህን<br>ሲወጉህ በጦር/2/<br>አንተ ግን ለእ ነ ርሱ ከአባትህ ምህረትን<br>ትለምን ነበር/2/<br>ግን መቼ አወቁ እነርሱ በኃጢአት ደንዝዞ<br>ልባቸው<br>መድኃታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም<br>ሞትክላቸው/2/<br>ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍጻሜ<br>በኋላ<br>አረ እንዴት እድለኖች ናቸው በፊትህ የ<br>ሚያገኙት ተድላ/2/<br>በዚያች በደብረዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ<br>ሲፈልቅ/2/<br>ከቶ ከየ ት ይሆን እጣዬ ያን ጊዜ የ እኔ<br>አወዳደቅ/2/<br><br>የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ እኔን<br>እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው<br>ልቤን/2/ | Amlak hoy wedena batemeta<br>lebseh yemaryamn sega/2/<br>Bakno yeneberew yeadam zere<br>wtetu neber yemiasega/2/<br><br>Beziya amet beziach were beziach<br>kene dhnetn lesew lije stsete/2/<br>Men yebeza neber ththnah<br>tegesteh yemaylewete/2/<br>Yesohe aklile defetew berash<br>gonhn siweguh betore/2/<br>Ante gen lenersu keabath meretn<br>telemen neber/2/<br>Gen mechei aweku Enersu<br>behateyate denzezo lebachew/2/<br>Medhanitacewn gerefuh sekeluh<br>anteme moteklachew/2/<br>Dagem setemeta lefrde kealem<br>fetame bewala ere endate<br>edelenoch nacew befith<br>yemiagenu tedela/2/<br><br>Beziyach bedebrezeyt bota<br>desyana lekeso sifelk/2/<br>Keto keyet yehon etayie yan giza<br>yeenie awedadeke/2/<br>Yetetet eroro befith endayakatlen<br>Enane/2/<br>Erdan fetariyie keahunu adesew<br>yezagew leban/2/ |

## ቸርነትህ ነው

## Chrneth new

| | |
|---|---|
| ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከዛሬ<br>ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከዛሬ<br>ላመስግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ/2/<br>መክሊቴንም ቀብሬ ባሳዝንህ<br>መብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ<br>በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ<br>በፍቅር ጎብኝተህ ከሞት አውጣኝ<br>ከቤትህ እርቄ መች ጠገብኩኝ<br>በረሐብ በእርዛት ተቸገርኩኝ<br>አምናለሁ አምላኬ እንድትምረኝ<br>ለይቅርታ መጣሁ ተቀበለኝ<br>አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ<br>ባንተ ቸርነት ግን እመካለሁ<br>የከበደው ሸክሜ ይቀለኛል<br>ይቅርታ ለባርያህ ይደርሰኛል<br>በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር<br>ስራህን ለትውልድ ለመመስከር<br>እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ<br>አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ<br>በሰው እጅ መመካት አቁሚያለሁ<br>እረዳቴ አንተ ነህ አውቄያለሁ<br>አንተ ከጠበከኝ በህይወቴ<br>ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ<br>የኔን ሰራ ተወው ተግባሬንም<br>የመስቀሉን ነገር መርሳቴንም<br>አዚሜን አንስተህ አንተን ልይህ<br>እየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ | Chrneth new yaderesen Eske zare<br>Chrneth new yetebeken Eske zare<br>Lamesgnh yenie gieta lezmaria /2/<br>Meklitan kebra basaznh<br>Mebratieanm yeza baltebkhe<br>Betalak yeketta Endatresan<br>Befker gobnteh kmot awtan<br>kebath Erka mech tegebkun<br>Berehab berzat techgerkun<br>Amnalhu amlaka Endtmren<br>Leykrta metahu tekbelen<br>Andach endelielen awkwlrhu<br>Bante chernt gen Emekalhu<br>Yekebeden shkmiea yekelenal<br>Yekerta lebariyah yedersenal<br>bemekdesh komie lemezemer<br>Srrahn letwyald lememesker<br>Ena man nen beya asbalhu<br>Amlak cernethn adenkalhu<br>Besew Eje memekat akumiealhu<br>Eredatie ente neh awkalhu<br>Ante ketebekn behywta<br>Ketra ayedeferm medhanitie<br>yenien sra tewew tegbarienem<br>Yemeskelun neger mersatanem<br>Azimiean ansteh anten leyh<br>Eyesus krstos amlaka neh |

## ሚያዚያ 01

### እም አፈ ደቂቅ

እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐት/2/

በእንተ ጸላኢ/4/ ከመትንሡቶ ለጸላዒ ወለገፋኢ/2/

**ትርጉም**፡- ከህጻት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ

የጠላት ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስ ዘንድ

### ሰላምሽ ዛሬ

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም

ወደ አንቺ መጥቷልና አምላክ ዘ ለዓለም/2/

ሆሳዕ ና በአርያም እያሉ ዘመሩ ህፃናት

በኢየሩሳሌም

አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ

የህዝቦችሽ ብርሀን መጣልሽ በግርማ/2/

ሆሳዕ ና እያሉ አመሰገ ኑት

በኢሩሳሌም ያሉት ሕፃናት/2/

ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙት

መስቀል ተሸክሞ ሆነን መድሃኒት/2/

የኢየሱስን ህመም ደናግልም አይተው

እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው/2/

## ሆሳዕና በአርያም

ሆሳዕና በአርያም ሆሳዕና በአርያም ሆሳዕና

ሆሳዕ ና ብለን እናቅርብ ምስጋና

ሆሳዕ ና በሉ ሆሳዕና

ለወልደ አምላክ ሆሳዕና

ትህትናን አሳየን ሆሳዕና

ስሙ ይባረክ ሆሳዕና

ሆሳዕ ና በሉ ሆሳዕና

ለሰማይ ን ጉስ ሆሳዕና

ግርማን ለብሶ መጣ ሆሳዕና

እኛን ሊቀድስ ሆሳዕና

ሆሳዕ ና በሉ ሆሳዕና

ለወልደ ዳዊት ሆሳዕና

ነብያት በትንቢት ሆሳዕና

ለተና ገ ሩለት ሆሳዕና

ሐዋርያት በወን ጌል ሆሳዕና

ለሰበኩለት ሆሳዕና

ሆሳዕ ና በሉ ሆሳዕና

ለአምላከ ምህረት ሆሳዕና

ተወልዶ ከድን ግል ሆሳዕና

እን ደ ህጻናት ሆሳዕና

እረኞች በዋሻ ሆሳዕና

የ ሰገ ዱለት ሆሳዕና

የ አዳም ልጆች ሁሉ ሆሳዕና

ደግሞም መላዕ ክት ሆሳዕና

## ሚያዚያ 6 ስቅለት

### እውነት ስለሆነ

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ

ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ

የሃሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው

ህይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው

ከቃሉ እምነት ባያገኙበት

ዝምታውን አይተው አላዘኑለት

ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለበደል

ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል/2/

የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ

ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉ

እሩህሩሁን ጌታ ቸንክረው ሰቀሉት

ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት/2/

ስለቸርነቱ ስድብን ከፈሉት

ስለርህራሄው የሾህ አክሊል ሰጡት

ሀሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው

መራራ አስጎነጬት ጨክኖ ልባቸው/2/

ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው

አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው

ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ

ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ/2/

## ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ

በመስቀል ሆነህ አባት ሆይ

ድምፅህን በማሰማት አባት ሆይ

ነፍስህን ሰጠህ አባት ሆይ

አ.ዝ---------------

የሰማይ ከዋክብት በሙሉ ረገፉ

ጨረቃና ፀሐይ ደምን አጎረፉ

ብርሃናት ጨለሙ ለማንም አልታዩ

ሥጋህን በመስቀል ላይ ተጋልጦ ስላዩ

አ.ዝ---------------

ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ

አሰምቶ ጮኸ ተጠማሁ እያለ

ማርና ወተቱን ለሚመግበው

ሐሞት አመጡለት ይቅመሰው ብለው

አ.ዝ---------------

አካሉ ሲወጋ ውኃ ደም ፈሰሰ

በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ

የጽዮን ደናግል ዋይ ዋይ ሲሉልህ

ለእነርሱ አሰብክ እንጂ ላንተስ አላሰብክ

አ.ዝ---------------

እናቱ ስታለቅስ በመስቀል ሥር ሆና

ዮሐንስን ሰጣት ጠብቆ እንዲያጽናና

መላእክትም ታዩ አጋንንትም ሸሹ

የአይሁድ ሠራዊት ፈርተው ተረበሹ

## እዩና እመኑ ሰዎች

እዩና እመኑ ሰዎች
ድንጋዩ ተፈነቃቅሏል
ክርስቶስ በእኩለ ሌሊት
በኃይሉ ሞትን ድል ነስቷል /2/

እልልታ ለዚህ ይገባል
ግርግርታ ለዚህ ይገባል
የሞት ኃይል ተዋርዷል ዛሬ
ሲዖልም ተመሰቃቅሏል

መላእክቱ ነጭ ለብሰው
ምስራቹን አበሰሩ
ተነስቷል ኢየሱስ ብለው
ለዓለም እንዲናገሩ

እዩና እመኑ ሰዎች
ድንጋዩ ተፈነቃቅሏል
ክርስቶስ በእኩለ ሌሊት
በኃይሉ ሞትን ድል ነስቷል /2/

እልልታ ለዚህ ይገባል
ግርግርታ ለዚህ ይገባል
የሞት ኃይል ተዋርዷል ዛሬ
ሲዖልም ተመሰቃቅሏል (2)

## ናና የምስጋና ጌታ — Nana yemsgana geta

| | |
|---|---|
| ናና የምስጋና ጌታ<br>ናና የምህረት ጌታ<br>ማዳንህ ተገኝታለችና<br>ሰላምህ ተገኝታለችና<br><br>ኢየሩሳሌም ሆይ ምስጋና ጀምሪ<br>መለከትን ንፊ ነጋሪት ጎስሚ<br>ሰላምሽ ታውጇል መዳንሽም ቀርቧል<br>ጌታ ሊጎበኝሽ ከበራፍሽ ቆሟል<br><br>አዝ....<br>ያልታደልሽው ሀገር ጌርጌሲዎን ሆይ<br>ለምን ተቃወምሽው አምላክሽን ስታይ<br>የከተማውን በር መዝጊያውን ቆልፈሽ<br>ከሩቅ የሸኘሽው ሲመጣ ሰላምሽ<br><br>አዝ....<br>የቢታንያ ድንጋይ አንደበት አውጥቶ<br>ምሥጋና ጀመረ አምላኩን ለይቶ<br>ሣርና ቅጠሉ ዘንባባው ሰገደ<br>ፍጥረት ሊያመሰግን አምላክን ወደደ<br><br>አዝ.....<br>ሕጻን ሽማግሌው ምሥጋና ሲያቀርቡ<br>ተቆልፎ ነበር ፈሪሳዊ ልቡ<br>ዛሬም በምስጋና ልባችን ይለወጥ<br>የሆሣዕና ጌታ ይመላለስበት<br>አዝ........... | Nana yemsgana gieta<br>Nana yemhret gieta<br>Madanh tegentalechna<br>Selamh tegentalechna<br>Eyerusalem hoye mesgana jemri<br>Meleketn nefi negarit gosmi<br>Selamsh tawjowal medanshem kerboal<br>Gieta ligobensh keberafsh komowal<br>Nana yemesgana geta.............<br>Yaltadelshw hager giergiesiwon hoye<br>Lemn tekawemshw amlakshn staye<br>Yeketemawn bere mezgiyawn kolfesh<br>Keruk yeshneshw simeta selamsh<br><br>Nana yemesgana geta.............<br>Yebitanya dengay andebet awteto<br>Mesgana jemere amlakun leyeto<br>Sarena ketelu zenbabaw segede<br>Fetret liamesegen amlakun wedede<br>Nana yemesgana geta.............<br>Htan shmagliew mesgana siyakerbu<br>Tekolfo neber ferisawi lebu<br>Zarem lemsegana lebachn yelewet<br>Yehosana gieta yemelalesbet<br><br>Nana yemesgana geta............. |

## እግዚአብሔርን አመስግኑ Egziabharn Amesgnu

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔርን አመስግኑ<br>ስራው ግሩም ድንቅ ነው በሉት<br>እግዚአብሔርን አመስግኑት<br>ስራው ግሩም ድንቅ ነው በሉት<br>ሰማይን ያለ ምሰሶ   ምድርንም ያለ መሰረት<br>ያጸናው እርሱ ነው<br>ስራህ ድንቅ ለው በሉት<br>አዝ....<br>የባህርን ጥልቀት የመጠነ<br>ዳርቻዋን የወሰነ<br>እግዚአብሔርን አመስግኑ<br>ስራህ ድንቅ ነው በሉት<br>አዝ....<br>ማዕበል ነፋስን የሚገስጽ<br>ፍጥረቱ ለስሙ የሚታዘዝ<br>ትጉህ እረኛ ድካም የሌለበት<br>እግዚአብሔር ስራህ ግሩም ድንቅ ነው በሉት<br>ንጹህ ባህሪይ ነው ሁሉን የሚገዛ<br>የነገስታት ንጉስ አልፋና ኦሜጋ<br>ዘለዓለም እርሱ የማይለወጥ<br>እግዚአብሔርን ስራህ ድንቅ ለው በሉት<br>ጥበብን የሚገልጥ ጥበበኛ<br>ፍርድ የሚያደርግ እውነተኛ ዳኛ<br>እንደ እርሱ ያለ ከቶ አይገኝም<br>እግዚአብሔር ግሩም ነው ዘለዓለም | Egziabharn Amesgnu<br>Sraw grum dnke new belut<br>Egziabharn amesgnut<br>Sraw gerum denk new belut<br>Semayen yale meseso<br>medrnm yale meseret<br>Yatenaw Ersu new<br>srah denke new  belut<br>Egziabharn.................<br>Yebahrn telket yemetene<br>darcawan yewesene<br>Egziabharn amesgnu<br>srah denk new belut<br>Maebel nefasn yemigest<br>fetretu lesmu yemitazez<br>Tegu Erena dekam yelielebet<br>Egziabharn srah grum denke new belut<br>netuhan  bahri new hulun yemigeza<br>Yenegestat negus alfana omiega<br>Zelalem Ersu yemaylewt<br>Egziabharn serah denk new belut<br>Tebeben yemiglt tebebena<br>Ferde yemiyaderg Ewnetena dana<br>Ende ersu yale keto aygenem<br>Egziabhare gerum new zelealem |

## ሚያዚያ 16

### ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን/2/
አሠሮ ለሰይጣን አግአዞ ለአዳም
ሰላም ሰላም ሰላም እም ይእዜሰ ይኩን ሰላም/2/

**ትርጉም**

ክርስቶስ ተነሳ ከሙታን በታላቅ ኃይል በ ስልጣን/2/
ሰይጣንን አስሮ/2/ ነጻ አወጣው አዳምን/2/
ሰላም ሰላም ሰላም እንግዲ ሰላም ይሁን/2/

### ትንሳኤከ ለእለ

ትንሳኤከ ለእለ አመነ /2/
ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ/2/

**ትርጉም**

ትንሣኤን ለምናምን ለኛ /2/
ብርሃንህን ላክልን ወደኛ /2/

## ሚያዚያ 22

### መላከ ሰላምነ

መላከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ዑራኤል
ሰዓል ወጸልይ በእንቲአነ

### እውነት በእውነት

እውነት በእውነት ጌታ ተነስቷል
ተነስቷል በክብር **<u>ሞትን ድል አድርጓል</u>** (2)

በሞቱ አጥፍቶ ሙስና መቃብር
የሙታን በኩር ሆኖ ተነስቷል ጌታችን (2)

እውነት በእውነት...................
ሳጥን ቢደረደር አፈር ቢረበረብ
ድንጋት በድንጋይ ላይ ደሞም ቢደራረብ
ምድር አልቻለችም አምላኳን ለመቅበር

እውነት በእውነት...................
የንጉሶች ንጉሥሰማያዊ አንበሳ
ሞትን ድል አድርጎ በሰንበት ተነሳ (2)

እውነት በእውነት...................
ተቀድሰናል በጌታችን ደም
ፍቅሩንም የሰጠን እንደሱ የለም
ሕያው ነው የሚኖር ለዘላለም

እውነት በእውነት...................

## ሚያዚያ 29

## እምሐና ኢያቄም

ኢያቄም ወሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ
መና ከሰማያት የወረደልሽ
እጹብ ድንቅ የሆንሽ ማርያም አንቺ ነ

## አማን በአማን

አማን በአማን (4)
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ(2)
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጸው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በቀል ቢኖር ጌታ
ለኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ
----- አዝማች -----
በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
----- አዝማች -----
ምህረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ
አለም በኃጢአት እየሳበችኝ
በጽድቅ ደስታ መኖር አቃተኝ
----- አዝማች -----
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

## እም እቶነ እሳት

እም እቶነ እሳት ዘ ይነ ድድ አን ገ ፈነ /2/

ብርሃናተ ዘይትአጸፍ ተንሥአለነ /4/

ከሚነደው እሳት ከነ በልባሉ አውጣን/2/

ብርሃናትን ተጎናጽፎ ተነሳልን/4/

## ግንቦት 6

## ዝም አትበሉ

ዝም አትበሉ እግዚአብሔር አመስግኑ/2/

ቅዱስ ቅዱስ በሉ(5)

መላዕክትን ሁሉ ምስጋና ጀምሩ

ቅዱስ ቅዱስ በሉ

አዝ ……

የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን አንሺ

በምሥጋና መዝሙር እስራኤልን ጥሪው

አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ

ከኛ ጋር ይሆናል የሠራዊት ጌታ(2)

አዝ ……….

ፍጥረታትም ጨሁ ሰማያት ዘምሩ

ስለ ቅድስናው ሁላችሁ ዘምሩ

ዳዊት ሆይ ተነሣ ስለ ጽዮን ዘምር

ከበሮው ይመታ በገናው ይደርደር(2)

አዝ …………….

ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር

ውለታው ብዙ ነው ለኛ ያለው ፍቅር

ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ

ለጌታ ለእግዚአብሔር ለሠራዊት ጌታ(2)

አዝ ……………………

ባህሩን አቋርጦ እንደ ለሚያሻግራችሁ

ተራራውን ንዶ ለአቀለለላችሁ

በአውሎ ነፋስ መሐል መንገድ አለው ጌታ

ለንጉሥ ክርስቶስ እንዘምር በእልልታ(2)

## ኃይልየ ሥላሴ

ኃይልየ ሥላሴ ወጸወንየ ሥላሴ
በስመ ሥላሴ/2/ እቀጠቅት ከይሴ

## ሥላሴ ትትረመም

ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር
ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር

## ማርያም ድንግል

ማርያም ድንግል ምክሆን ለደናግል ይእቲኬ
ቤተምሳል ዘሀስተሀጸቡ ታቀልል /2/
እምኩሉ ፍጥረት ትተነብል በአክናፈ መላእክት
ትትኬለል ይህቲ ተአቢ እምኪሩቤል ወትተነብል እምሱራፌል /2/

ማርያም ድንግል መመኪያቸው የደናግል
እርሷም እኮ የምልጃቤት ናት የሚያስጨንቀውን የምታቃልል /2/
ለፍጥረት ሁሉ ትማልዳለች በመላእክት
ክንፎችም ትጋረዳለች እርሷ ትበልጣለች
ከኪሩቤል ደግሞም ትለቃለች ከሱራፌል /2/

## ግንቦት13

## ያሬድ ፈልፈለ

ያሬድ ፈልፈአ ማሄት ወቅኔያር ወባህረ ጥባት/2/

እመስኮንከ መርሀ መዘምሩ ለኢትዮጵያ ያሬድ ካህን ጥኡመ ልሳን /2/

## እውነት በእውነት ኃያል ኃያል

ኃያል ኃያል /4/

ሰዳዴ ሳጥናኤል/2/

ኃያል ገባሬ ኃይል

ባህራንን ያዳነው ተላፊኖስን የረዳው

መልአኩ ሚካኤል ነው/2/

የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው

ከእደ ረበናት/2/

ሶስናን የዳናት/2/

ሚካኤል መልአከ ምህረት

ዲያብሎስን የ ዋረድከው በእሳት ሠይፍ የ ቀጣኸው

ሚዛንህ ትክክል ነው/2/

ሚካኤል ክብርህ ድንቅ ነው

በሀዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና/2/

አፅናናኝ አረጋጋኝ/2/

ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

## መንክረ ግርማ

መንክረ ግርማ ሃይለ ልዑል ጸለላ /2/

አማን/2/ መላእክት ይኬልልዋ /2/

በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል ሃይል ጋረዳት /2/

በእውነት /2/

መላእክት አመሰገኗት አንትሙሰ

## አንትሙሰ

ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም/2/

እስክትለብሱ ኀይለ እምአርያም/2/

እናንተ ግን ቆዩ በኢየሩሳሌም ሀገር /2/

እስከምታገኙ ኃይል ከሰማይ/2/

## ሰኔ 4

### ቀዳሚሁ ቃል

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል/2/

ቃል ስጋ ኮነ ይቤ ዮሐንስ/2/

### ጸሀይኑ ንብለከ

ጸሀይኑ ንብለከ/2/

አልደ ማርያም ንብለከ/2/

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለከ /2/

የማርያም ልጅ አምላክ/2/ ጸሀይ ነህ እንበልህ /2/

በምን በማን አምሳል እንመስልህ /2/

## ሰኔ 15

እቴ ሙሽራዬ

ያልጠፋነው

## ሰኔ 25

### ደስ ይበለን

ደስ ይበለን ደስ ይበለን /2/
አምላክ አለ መሀላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምህረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን እድሜ የጨመረልን
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን
ሃጢያትህን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ አጥዕ የጽድቅ ሕይወት
እልል በሉ የጎበኛችሁ
በምህረት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን
ሁሉ አመስግኑ ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትጸልያለች
ሃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንድ እንዲያደርገን

### ያከብርዋ ለሰንበት

ያከብርዋ ለሰንበት መላክት በሰማያት ጻድቃን በውስት ገነት /2/
ወኵሉ ፍጥረት ዓሳት ወ አናብርት
እለ ውስተ ደይን ያዕረፉ ባቲ
እስመባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ /2/
ያከብሩአታል ሰንበትን መላእክት
በሰማያት ጻድቃንም በገነት
ፍጥረታት በሙሉ ዓሣዎችና አንበሪዎች
በመቃብር ያሉ ያከብሩአታል
አምላክ በርሷ እንዳረፈ ከስራው ሁሉ

## ሀምሌ 2

## ብርሃናተ አለም ጴጥሮስ

ወጳውሎስ/2/

ጻድቁ አባታችን/2/ ገብረመንፈስ

ቅዱስ

የመረጣቸው ፈጣሪያችን አምላካችን

እንድናገኝ ሰላም አማልዱን እኛን /2/ ከፈጣሪያችን

## ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ /2/

ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ከመ ጼና ስኂን /2/

አልባሲሁ ዘሜላት /2/ ዘወረደ ውስተ ገነት/2/

### ለሀገሪትነ ሰላማ

ለሀገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተሀቅብ/2/

አባ ኦ አባ /2/ በብረመንፈስ ቅዱስ /2/ አባ

## ሐምሌ 9

### እኔስ እዘምራለሁ

እኔስ እዘምራለሁ ለስላሴ /2/

ፈጥሮኛልና በሥጋ በነፍሴ

እኔስ እዘምራለሁ ለሥላሴ

ሥሉስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን

ሰውን ከመከራ ከሞት የሚታድን

ነፍሴ ትገዛልህ ትንበርከክልህ

ቅዱስ ፈጣሪዋን አንተን ታምልክህ

በመሀሪነትህ ጠብቀህ ያኖርከኝ

በማዳን ችሎታህ ለዚህ ያደረስከኝ

ለአንተ ለአምላኬ ምስጋና አቀርባለሁ

ስምህን ለዓለም ሁሌም እጠራለሁ

አብርሃም ለአምላኩ በቀና ቢታዘዝ

ሥላሴ ገቡና ቤቱን ባረኩለት

ሣራንም ጎበኟት በእርጅናዋ ጊዜ

ይስሐቅን ሰጧት ለዘለዓለም ሥላሴ

### እምኩሉ ይሄይስ

እምኩሉ ይሄይስ በስላሴ ስም ተዓምኖ/2/
ወላዲትከ/3/ወበ ወላዲትከ ተማህጸኖ/2/

## ሐምሌ 23

### ጸጋን የተመላሽ

ጸጋን የተመላሽ ሆይ ክብር ላንቺ ይገባል
የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናቱ ሆነሻል
ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ ተመርጠሻል

ሰላም ልበልሽ የጌታዬ እናት
ጽድቅ ያየንብሽ ምክንያተ ድህነት
ልባችን ያውጣ በጎ ነገር
ለዓለም እንመስክር ያንቺን ክብር

ጸጋን የተመላሽ...................
የምስራቅ ጸሀይ ኩራቴ ነሽ
እጅግ ልዩ ነው ደግነትሽ
ልቀኝ ለክብርሽ እንደ ያሬድ
የአበው ተስፋ ሰላም ወዳድ

ጸጋን የተመላሽ...................
የድል አክሊል ነሽ ሰላማዊት
ህብስተ መና ምግበ ሕይወት
ከልቤ ሆኜ እስቲ ላድንቅሽ
እንደ አባ ኤፍሬም በዝቶልኝ ፍቅርሽ

ጸጋን የተመላሽ...................
የመስቀሉ ስር ስጦታ ነሽ
ለዓለም መጽናኛ የተመረጥሽ
የሚያቃልሉ ክብርሽን ንቀው
ይማልላሉ ከፊትሽ ወድቀው ጸጋን
የተመላሽ...................

## ጋሻውን ይዞ በፈረስ

ጋሻውን ይዞ በፈረስ

አቤት ማማሩ ቅዱስ ጊዮርጊስ (2)

ቤሩታዊትን ያዳናት ዘንዶ እንዳይበላት ደራጎን

**<u>እኽ/ ቤሩታዊትን ያዳናት ዘንዶ እንዳይበላት ደራጎን፤</u>**

## ሐምሌ 30

### ማርቆስ ሐዋርያ

ማርቆስ ሐዋርያ ወንጌላዊ ሰማይት(2)
ሰበከ በሮም በመላው አለም
ሰበከ በእስክንድርያ በመላው ግብጽ(2)

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር
ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል/2/
መታመኛዬ እርሱ ነውና ይገባዋል ክብርና
አዝ........
ሕጉን እያሰብን እንቅረብ ወደእርሱ
ይምረናልና መሀሪ ነው እርሱ
በልባችን ይግባ ይንገስ በቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ አርሱ ነው ተስፋችን /2/
አዝ....
ከቶ አላገኝም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ሃይል
በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ
ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ /2/
አዝ...........
በለመለመ መስክ መሸሸጊያዬ ነው
በሰላም ወጥቼ ሰላም እገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይመራናልና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና/2/
አዝ...................
ለእኔስ የሻለኛል መቅረብ ወደጌታ
ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ
ስለዚህ ቀርባለሁ አልርቅም ከደጁ
ጠግቤ እኖራለሁ በበረከት እጁ/2/

## ነሐሴ 7

### አአትብ ወእትነሳእ

አአትብ ወእትነሳእ በስመ አብ ወወልድ
ወመነፈስ ቅዱስ አቲብየ አትነሳእ
በስመአብ ወወልድ
ሰለስተ አስማተ ነስእተ ነሲእየ
እትዌከል ቦቱ

**ይዌድስዋ መላእክት**

ይዌድስዋ መላእክት (2) ለማርያም /2/
በውስተ ውሳጤ መንጦላእት
ወይብልዋ
በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ

### እናት አለኝ

እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ /2/
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ የምታጽናናኝ
እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ
አዝ-----------------
የተቀኘላት እዝራ በመሰንቆ
እናትነቷን ንጽህናዋን አውቆ
ያመሰገናት ዳዊት በበገና
አትለየኝም እናቴ ናትና /2/
አዝ---------------
ሳዝን ስተክዝ ወድቄ ከፊቷ
አቅፋ አጽናናችኝ እኔን ከደረቷ
ታማልዳለች ዛሬም ለኃጥአን
ትማጸናለች በእንባ ዘውትር ልጇን /2/
አዝ-----------------
የአዳም ተስፋናት ድንግል እናታችን
መርጦ ያደረባት ክርስቶስ ጌታችን
ታማልዳለች ዛሬም ለዘለዓለም
የአምላክ እናት ናት የፍጥረታት ሰላም /2/

## ነሐሴ 14

### ሶበሰ ኪዳንኪ

ሶበሰ ኪዳንኪ ምክንያተ ድኂን ኢሀሎ /2/
ፈለገ እሳት ወደይን እም አስጠመ ኩሎ
ፈለገ እሳት ወደይን ወደይን እም አስጠመ ኩሎ /2/

### አሀደ ለከ

አሀደ ለከ ወአሀደ ለሙሴ
ወአሀደ ለኤልያስ ንግበር ማይደረ/2/
አንዱንም ላንተ አንዱንም ለሙሴ
አንዱንም ለኤልያስ እንስራ ቤትን/2/

### እንዲህ አለው

እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምሥጢር ገሃድ ሲሆን በዚያ ተራራ
ባንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንሥራ

አንዱን ላንተ አንዱንም ለሙሴ
አንዱን ለኤልያስ
ተለወጠ ገጹ ከመ ጽጌ ረዳ

ወርዶ ከለላቸው ደመና ጸአዳ
ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል

ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው
ስለ አስደነቃቸው ግሩም ተአምራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ

## ነሐሴ 21

## በምን በምን እንመስላት

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያም (2)
ምሳሌ የላትም (2) ክብሯን የሚመጥን (2)
የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላእከት እኅት የርህሩሃን እርግብ (2)
...........አዝ......
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር
ድንግል እናቴ ናት የጽድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር፡(2)
...........አዝ......
የቅዱሳን እናት የአርያም ንግሥት
ስለ ተሸከመች መለኮት እሳት
በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ (2)
...........አዝ......
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለሙን የዳነ በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምሥጋና (2)

## ዜኖኩ ጽድቅከ

ዜኖኩ ጽድቅከ ወነገርኩ አድኅኖትከ
ከሰትኩ ቃላቲከ ለህዝብከ ኢትዮጵያ /2/
በጸጋሁ በመንፈስ ቅዱስ ወመሀርክዎሙ
አነ ይቤ ተክለሃይማኖት /2/

**ትርጉም፡-**

ጽድቅህን ነገርኩ አዳኝነትህን አስተማርኩኝ ቃላትህንም ለኢትዮጵያ ህዝብ ነገርኩ /2/
እኔም በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አስተማርኳቸው አለ ተክለሃይማኖት /2/

## ማርያም አርጋች

ማርያም አርጋለች ወደ ገነት (፪X)
የሰማያት መላእክት እያረጋጓት
'ርሷም እንደ ልጇ ተነስታለች።
አዝ...
የአባቷን ዳዊት ትንቢት ለትፈጽም
ወርቁን ተጎናጽፋ ከጎኑ ልትቆም
ወደ አምላክ ማደሪያ ወደ ሰማያት
አረገች በእልልታ ማርያም የ'ኛ እናት
አርጋለች ማርያም ተነስታለች።
አዝ...
ሰማያት ይከፈት ደመናት ይዘርጋ
ዝምታም አይኖርም እመአምላክ አርጋ
አንደበት ይከፈት ማርያም ያመስግን
ከዘላለም ጥፋት በምልጃዋ እንድንድን
አርጋለች ማርያም ተነስታለች።
አዝ...
የአምላክ ማደሪያ ያ ቅዱስ ሥጋሽ
አምላክን ያቀፉ እነዚያ እጆችሽ
ሙስና መቃብር ይዞ አላስቀራቸው
ተነስተዋል በክብር በእምነት አየናቸው
አርጋለች ማርያም ተነስታለች።
አዝ...
ሐዋርያት አበው እንኳን ደስ አላችሁ
በክብር አረገች ማርያም ሞገሳችሁ
ዓለምም ውጡ ሰበኗን ይዛችሁ
የድንግል እርገቷን ንገሩ ተግታችሁ
አርጋለች ማርያም ተነስታለች።

## አማን በአማን

አማን በአማን:(4)

አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ:(2)

ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጸው:

ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው:

እንደ ሰው በቀል ቢኖር ጌታ:

ለኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ:

----- አዝማች -----

በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ:

ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ:

አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም:

በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም:

----- አዝማች -----

ምህረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ:

ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ:

አለም በኃጢአት እየሳበችኝ:

በጽድቅ ደስታ መኖር አቃተኝ:

----- አዝማች -----

የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም:

ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም:

እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ:

ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ:

## በሰላም ንዒ

በሰላም ንዒ ንዒ ማርያም/2/

አ.ዝ-------

ትናዝዘኒ /2/ ኃዘነ ልብየ

አ.ዝ-------

ምስለ ሚካኤል/2/ ወገብርኤል /2/

አ.ዝ-------

ምስለ ሱራፌል /2/ ወኪሩቤል/2/

አ.ዝ-------

ምስለ ዑራኤል/2/ ወሩፋኤል /2/

አ.ዝ-------

ምስለ ኲሎሙ/2/ ቅዱሳን /2/

አ.ዝ-------

ምስለ ወልድኪ/2/ አማኑኤል/2/

## ነሐሴ 30

የአዋጅ ነገሪ ቃል በበርሃ አየለ

የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ

ምስክርነቱን ዮሐንስ ከስረዳን

ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የድናግል መመኪያ የነብያት ገዳም።

ዐውደ አመቱን ባርኪልን ድንግል ማሪያም

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና

ካልተስተካከለ መንገድ የለም ና

የእግዚአብሔርን መንገድ እንጥረግ ሁላችን

ማለፊያ እንዲሆነን ለመጪው ሀብታችን

አዝ...

ክፋት ና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ

ጽድቅ ና ርኅራኄ በእኛ ላይ ይስፋፋ

ሥጋ ና ደምህን በክብር አግኝተናል

ህይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል

አዝ....

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን

ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን

ከበደላችን አንጻን አደራህን

በክፉ እንደንጠፋ እኛ ባሮችህ

አዝ......

## ጸልይ ሀበ

ጸልይ ሀበ አምላክ ሀበ አምላክ ራጉኤል መለአክ /2/
አውደ ዓመት ከመ ይትባረክ /2/

## መስከረም 7

### የዕለት የዓመት

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ (2)
አዝ---------------
ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት የደረሰን ለሁላችን
አዝ---------------
ሰው ልጆች ዕድሜ ጥንቱንም ሲጀምር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን ነውና አይሞላም እንዳንተ አቆጣጠር (2)
አዝ---------------
ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው
ወዳንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው Â ዕድሜ ከራበው (2)
አዝ---------------
እጅግ አደንቃለሁ የአምላክን ጥበብ
ምድርን በአበባ ሰማዩን በኮከብ
እንዳሸበረቃት Â አስተውዬ ሳስብ (2)
አዝ---------------
በከንቱ ጊዜያችን ፈጽሞ እንዳይጠፋ
በርትተን ከሠራን ያላአንዳች ነቀፋ
የሚሰጠን አለን ሙሉ ተስፋ (2)
አዝ---------------
ከንቱ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ
ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ
ደግሞም በጠቅላላው ዓለምን ብገዛ (2)
አዝ---------------
ወርኃ ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ
ምድር በልምላሜ ስታጌጥ በአበባ

እናምናለን ላንተ ምስጋና እንዲገባ (2)
የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ (2)
አዝ---------------
ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት የደረሰን ለሁላችን
አዝ---------------
ሰው ልጆች ዕድሜ ጥንቱንም ሲጀምር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን ነውና አይሞላም እንዳንተ አቆጣጠር (2)
አዝ---------------
ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው
ወዳንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው Â ዕድሜ ከራበው (2)
አዝ---------------
እጅግ አደንቃለሁ የአምላክን ጥበብ
ምድርን በአበባ ሰማዩን በኮከብ
እንዳሸበረቃት Â አስተውዬ ሳስብ (2)
አዝ---------------
በከንቱ ጊዚያችን ፈጽሞ እንዳይጠፋ
በርትተን ከሠራን ያላአንዳች ነቀፋ
አምላክ የሚሰጠን አለን ሙሉ ተስፋ (2)
አዝ---------------
ከንቱ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ
ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ
ደግሞም በጠቅላላው ዓለምን ብገዛ (2)
አዝ---------------
ወርኃ ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ
ምድር በልምላሜ ስታጌጥ በአበባ
እናምናለን ላንተ ምስጋና እንዲገባ (2)

## ንሴብሆ

==============

ንሴብሖ/2/ ለአምላከ እዝራ
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ
አ.ዝ----------------------//
ለምስጋና ቀሰቀሰኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ሰለፍቅርህ ልጀምር ማሕሌት
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ
አ.ዝ----------------------//
ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሐን
አስገረመኝ ከዋክብቱ ሲያወሩ ሥራህን
ንሴብሆ ለአመላከ እዝራ
አ.ዝ----------------------//
አዕዋፋት በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው ያንተን ክብር በምስጢር ሲያወሩ ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ
አ.ዝ----------------------//
ከበሮ ሆይ ጸናፅል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ
አ.ዝ----------------------//
ኑበእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ስለሁሉም ነገር
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

## መስከረም 14

### መስከረም ጠባ

መስከረም ጠባ ኢዮ አበባ
መስከረም ጠባ ለኛ ኢዮ አባባ
መስቀል አበራ ኢዮ አበባ
ለኛ ሊሆነን እድገት እና ልማት
ኢዮ/2/ አበባዬ ኢዮ መስከረም ጠባ ለኛ
ኢዮ አበባ
በተዋሕዶ የከበረች እናታችንን
የጥበብ ልጆቿ እናከብራታለን
ሀይማኖት ከምግባር ወንጌልን መግባ
ስላሳደገችን የድኅነት መሠረት
ቤተክርስቲያን እናታችን
ጥንትም መሪ እና አስተማሪ በመሆኗ
በዓለም ላይ ታውቋል ዜናዋ
እየተወሳ በዓለም ዜና ያኮራናል
መስቀላችን ኢዮ አበባ
መስከረም ጠባ ኢዮ አበባዬ/3/

## መስከረም 21

## መስከረም 28

## በልዎ ለእግዚአብሔር BELWO LEGZIEBHIER

| | |
|---|---|
| በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ | Belwo leEgziebhier grum gbrke |
| እግዚአብሔርን በሉት ሥራህ ግሩም | EgziebHiern belut srah grum dnke |
| ድንቅ ነው/2/ | new/2/ |
| ሰማያትን በስንዝር የምትለካቸው ሥራህ | |
| ግሩም ድንቅ ነው | Semayatn besnzr yemrlekacew |
| ቀላያትን በእፍኝ የምትሰፍራቸው ሥራህ | srah grum dnke new |
| ግሩም ድንቅ ነው | Kelayatn beEfn yemetsefraracew |
| ቃልን ብቻ ልከህ የምታሰማምር ሥራህ | srah grum dnke new |
| ግሩም ድንቅ ነው | Kaln beca lkeh yemtasemamr srah |
| በድንቅ አሰራርህ ግሩም ነህ እግዚአሔብር | grum dnke new |
| >> >> >> | Bedenk aserarh grum neh |
| | Egzieabhier srah grum dnke new |
| ለእኔ የዋልክልኝ መቼ የሚረሳነው ሥራህ | |
| ግሩም ድንቅ ነው | Lene yewalkln meche yemiresnew |
| ከሰው መቆጠሬ ጌታዬ በአንተነው ሥራህ | srah grum dnke new |
| ግሩም ድንቅ ነው | Kesew mekoterie getayie |
| በላዬ ዘርግተህ የክብር ደመና ሥራህ | beantenew srah grum dnke new |
| ግሩም ድንቅ ነው | Belayie zergteh yekbr demean |
| ቅጥሩን አዘለለልከኝ ድጋፍ ሆንከኝና | srah grum dnke new |
| ሥራህ ግሩም ድንቅነው | Ketrun ezellelken dgafe honkena |
| | srah grum dnke new |
| ስለሀጥያቴ ብዛት ሊወግሩኝ ሲነሱ ሥራህ | Slehatyati bzat liwegrun sinesu |
| ግሩም ድንቅ ነው | srah grum dnke new |
| በፊቱ አቁመውኝ ሲከሱኝ በብዙ ሥራህ | Befitu akumewn siksun bebzu srah |
| ግሩም ድንቅ ነው | grum dnke new |
| ጥፋቴን አይሻም እርሱ መች ፈረደ ሥራህ | Tfatien aysham Ersu mech ferde |
| ግሩም ድንቅ ነው | srah grum dnke new |
| ውለታው ግሩም ነው ሊምረኝ ወደደ | Wletaw grum new limren wedede |

| | |
|---|---|
| ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው<br><br>እሰግድልሀለሁ ፊትህ ተንበርክኬ ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው<br>ውለታህ ማርኮኛል እግዚአብሔር አምላኬ ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው<br>ከአንተ ጋራ ሆኜ ምን ይጎልብኛል ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው<br>በምሕረትህ ጎብኘኝ ጸጋህ ይበቃኛል ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው | srah grum dnke new<br><br>Esegdlhelehu fith tenberkeka srah grum dnke new<br>Wletah markonal Egziabhier amlakie srah grum dnke new<br>Keante gara hone men ygolbnal srah grum dnke new<br>Bemhret gobnn tegah yebekanal srah grum dnke new |